# ጠቢብ ሁን


ጸሐፊ - በዋረን ዌርዝቢ

ትርጉም - በፈቃዱ ገብሬ

እርማት-በጌቱ ግዛው



BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የኤስ. አይ. ኤም. ሥነ ጽሑፍ ክፍል

የፖ.ሣ.ቁጥር 127

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

ስልክ - 71 11 73 ፖ.ሣ.ቁ. 127

Tel. 51 29 73 P.o. Box 127

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

Addis Ababa, Ethiopia

የመጀመሪያ ዕትም - 1994 ዓ.ም

2ኛ ዕትም - 1995 ዓ.ም

First Printing - 2001

2nd Printing - 2003

**Copyright**

**© 2000 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE WISE. Copyright © 1983 by SP Publications, Inc, ChariotVictor Publishing, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs, C0 80918 USA. All rights reserved.**

**Publisher - BEBLE BASED BOOKS**

**SIM PUBLISHING**

አሳታሚ:- መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

# ማውጫ

መቅድም

በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን መሠረተ አቋም

ስለ. . . ጠቢብ ሁን


1. የክርስቲያን ጥሪ (1ኛ ቆሮ. 1)........1
2. ክርስቲያናዊ መልእክት (1ኛ ቆሮ. 2)........13
3. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን (1ኛ ቆሮ. 3)........25
4. ክርስቲያናዊ አገልግሎት (1ኛ ቆሮ. 4)........36
5. የቤተ ክርስቲያን የሥነሥርዓት እርምጃ (1ኛ ቆሮ. 5–6)........46
6. ክርስቲያናዊ ጋብቻ (1ኛ ቆሮ. 7)........56
7. ክርስቲያናዊ አርነት (1ኛ ቆሮ. 8፤ 10)........66
8. ግላዊ ቀዳሚ ጉዳዮች (1ኛ ቆሮ. 9)........77
9. የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት (1ኛ ቆሮ. 11)........87
10. የቤተ ክርስቲያን አካልነት (1ኛ ቆሮ. 12–13)........97
11. የመንፈሳዊ ስጦታዎች አጠቃቀም (1ኛ ቆሮ. 14)........109
12. ትንሣኤ (1ኛ ቆሮ. 15)........121
13. ክርስቲያናዊ መጋቢነት (1ኛ ቆሮ. 16)........131

# መቅድም

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ክርስቲያኖች በነበሩአቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች እና እውቀት ይታበዩ ነበር። እንዲህም ሆኖ በግል ሕይወታቸው ውስጥ እና በጉባኤያቸው መካከል ጉልህ ስሕተት ነበረባቸው።

ጳውሎስ የሚያስፈልጋቸው *እውነተኛ መንፈሳዊ ጥበብ* መሆኑን ደርሶበታል። ይህም የዓለም ጥበብ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ብቻ የሚፈልቅ ጥበብ ነው።

እኛም ዛሬ የሚያስፈልገን ይኸው ጥበብ ሲሆን የሚገኝበትን እንድናውቅ ይህ መልእክት ጥሩ መነሻ ይሆነናል። ሃይማኖታዊ መሪነታችን «ለቀዳሽ አወዳሾች» ወጥመድ እንዳያደርገን፥ ጳውሎስ ስለ ወንጌል መልእክት እና አገልግሎት እንዴት ልባም መሆን እንደሚገባን ይናገረናል። በአምልኮአችን ምን ዓይነት ሥርዓት ልንይዝ እንደሚገባና መንፈሳዊ ስጦታዎቻችንን እንዴት እንደምናውቃቸውና እንደምናዳብራቸው ይነግረናል። እግዚአብሔርን ለማክበርና ከዓለም እድፈት ለማምለጥ ይቻለን ዘንድ እንዴት ራሳችንን በንጽሕና መጠበቅ እንዳለብንም ይነግረናል።

በዚህ አጭር የገለጣ ጥናት፥ እንደኛ ቆሮንቶስን በመሰለ ሰፊ መልእክት ውስጥ ያሉትን ዝርዝር ጠጣር አሳቦች ሁሉ ማጠናቀቅ አንችልም። የእኔ ዓላማ የመልእክቱን አንኳር ትምህርቶች ማብራራት እና ለሕይወታችንና ለቤተ ክርስቲያኖቻችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። የእርሱን መንፈሳዊ ጥበብ እንድንቀበል እና በግል ሕይወታችንም ተግባራዊ ማድረግ እንድንችል ጌታ ይርዳን።

ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ

# በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን መሠረተ አቋም

ጳውሎስ በ 50 ዓ.ም መኸር ወቅት አካባቢ ወደ ቆሮንቶስ መጥቶ 18 ወራት በዚያው በመቆየት (የሐዋ. ሥራ 18፡1–17) ቤተ ክርስቲያኒቱን መሠረተ። ከዚያም ቀጥሎ ወደ ኤፌሶን ተጓዘ (ቁ. 18–19)።

በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ችግሮች አሉ በሚል የደረሰው ዜና ዛሬ በእጃችን ያልገባውን መልእክት እንዲጽፍ አነሣሣው (1ኛ ቆሮ. 5፡9)። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መካከል የከፉ ችግሮች ስለመኖራቸው ከቀሎዔ ቤተሰቦች የመጣው ተጨማሪ መልእክት (1ኛ ቆሮ. 1፡11) የሚያመለክተው፥ ይህ «የጠፋ ደብዳቤ» የጳውሎስን ፍላጎት እንዳልፈጸመለት ነበር። ከዚያ በኋላ ቤተክርስቲያኒቱ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ልምምድ እና ዶክትሪን ጥያቄዎችን ያዘለ ደብዳቤ አስይዛ አንድ ልዑክ ወደ ጳውሎስ ላከች (1ኛ ቆሮ. 7፡1፤ 16፡17–18)።

በዚህ ደብዳቤ ስለደረሰው የከፋ ዜና ምላሽ፥ ጳውሎስ፥ 1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት ሲባል የምናውቀውን ደብዳቤ ጻፈ። የጻፈውም በ57 ዓ.ም. አካባቢ በኤፌሶን ሆኖ ነበር።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጳውሎስን ሐዋሪያዊ ሥልጣን የማይቀበል ቡድን ተነሥቶ ነበር። በመሆኑም ሐዋርያው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ «አስቸኳይ ጉብኝት» አደረገ፥ ይሁን እንጂ ውጤቶቹ አርኪ አልነበሩም (2ኛ ቆሮ. 2፡1፤ 12፡14፤ 13፡1)። ከዚያ በኋላ «የሰላ ደብዳቤ» (2ኛ ቆሮ. 7፡8–12) ጽፎ በቲቶ አማካኝነት ላከባቸው።

ጳውሎስ ቲቶን በጢሮአዳ አግኝቶ (2ኛ ቆሮ. 2፡12–13፤ 7፡6–16) ቤተ ክርስቲያን የጳውሎስን ትእዛዝ ስለ መቀበሏና የተቃዋሚዎቹን መሪም እንደቀጣች መልካም ዜና ሰማ። ከዚያ በኋላ ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስን ጻፈ።

## የ 1ኛ ቆሮንቶስ አስተዋጽኦ

1. ሰላምታ– 1፡1–3

2. ግሣጼ፡– በቤተ ክርስቲያን ስለነበረው ኃጢአት ዘገባ– 1፡4–6፡20

   ሀ. መከፋፍል በቤተ ክርስቲያን – 1፡4–4፡21

   ለ. ፍርድ በቤተክርስቲያን ውስጥ– 5፡1–13

   ሐ. በችሎት ፊት መፋረድ (መካሰስ) – 6፡1–8

   መ. በዓለም ውስጥ መርከስ – 6፡9–20

3. መመሪያ፡– ለጥያቄዎቻቸው ምላሽ – 7፡1–16፡12

   ሀ. ጋብቻ 7፡1–40

   ለ. ለጣዖት ስለተሠዋ ምግብ– 8፡1–10፡33

   ሐ. የቤተ ክርስቲያን ሥልጣናዊ አመራር– 11፡1–34

   መ. መንፈሳዊ ስጦታዎች– 12፡1–14፡40

   ሠ. ትንሣኤ–15፡1–58

   ረ. የገንዘብ መዋጮ – 16፡1–12

4. መደምደሚያ – 16፡13–24

# ስለ ክርስቲያን ጥሪ. . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 1*

«ለኢየሱስ፥ እሺ! ለቤተ ክርስቲያን፥ እምቢ!»

በ1960ዎቹ ይህ መፈክር በወጣቶች ዘንድ ተወዳጅ የነበረበትን ጊዜ ታስታውሳለህን? በወቅቱ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በከፋ ችግር ውስጥ ስለነበረች፥ ይህን አባባል በ 56 ዓ.ም በቆሮንቶስ የነበሩት ያለ ጥርጥር በቅንነት በተጠቀሙት ነበር። የሚያሳዝነው፥ ችግሮቹ በቤተ ክርስቲያኒቱ ቤተሰቦች መካከል የቀሩ ሳይሆኑ፥ በውጭ ባሉ በማያምኑትም ዘንድ የታወቁ መሆናቸው ነበር።

በመጀመሪያ ደረጃ በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተክርስቲያን *የረከሰች* ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ከአባሎቿ አንዳንዶቹ በዝሙት ኃጢአት የወደቁ ነበሩ፤ ሌሎች ሰካራሞች ነበሩ፤ እንደዚሁም ሌሎቹ ለዓለማዊ አኗኗራቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደ ማመካኛ የሚጠቀሙ ነበሩ። ከዚህም ባሻገር ይህች ቤተ ክርስቲያን በአመራር ትንቅንቅ በገጠሙ (1፡12) በትንሹ አራት የተለያዩ ቡድኖች *የተከፋፈለች* ነበረች። ይህም *ጸጋዋ የተገፈፈ* ቤተ ክርስቲያን ነበረች ማለት ነው። እግዚአብሔርን በማስከበር ፈንታ፥ የወንጌልን ግሥጋሤ የምትገታ ነበረች።

ይህ ሊሆን የቻለው እንዴት ነበር? የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የከተማዪቱ ኃጢአት ወደ ጉባኤያቸው ሰርጎ እንዲገባ ስለፈቀዱ ነበር። ቆሮንቶስ ሁሉም ዓይነት ክፋትና ዓለማዊ ተድላ ያጨናነቃት የረከሰች ከተማ ነበረች። በዚያን ዘመን የመጨረሻው ቀላል ክስ አንድን ሰው «ቆሮንቶሳዊ» ብሎ በመወንጀል ሊመሠረት ይችል ነበር። በአባባሉ ምን ለማለት እንደፈለገ ሰዎች ወዲያው ይገባቸዋል።

በተጨማሪም ቆሮንቶስ ንድፈ አሳባቸውን የሚያራምዱ በርካታ ተዘዋዋሪ አስተማሪዎች የነበሩባት፥ በትዕቢቷ የተወጠረች የፍልስፍና ከተማ ነበረች። የሚያሳዝነው፥ ይህ ፍልስፍናዊ አካሄድ በወንጌል ላይም እንዲተገበር በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት አማካኝነት በመደረጉ ክፍፍሉን አባብሶአል። ምእመናኑ ከወንጌል መልእክት በስተጀርባ በኅብረት ከመሰለፍ ይልቅ የተለያዩ «የአመለካከት ጎራዎች» ባሉአቸው ቡድኖች የተዋቀሩ ነበሩ።

ቆሮንቶስ ምን ዓይነት እንደነበረች ለማወቅ ከፈለግህ ሮሜ 1፡18-32ን አንብብ። ጳውሎስ የሮሜን መልእክት በሚጽፍበት ጊዜ በቆሮንቶስ ነበር። በመሆኑም የዘረዘራቸውን ኃጢአቶች ሁሉ በመስኮቱ አሻግሮ በዓይኑ ሊያያቸው ይችል ነበር!

በእርግጥ በሰብአዊ ጥበብ የሚመኩ፥ ዓለማዊ አኗኗርን የተላበሱ ዕቡያን ሰዎች ሲኖሩ ችግሮች እንደሚከሰቱ የታወቀ ነው። ችግሮቻቸውን ለመፍታት እንዲችሉ ለመርዳት ጳውሎስ *በክርስቶስ የተደረገላቸውን ጥሪ* በማሳሰብ መልእክቱን አሃዱ በማለት የዚህን ጥሪ ሦስት ጠቃሚ ገጽታዎች አመለከተ።

## ቅዱሳን ለመሆን እንደተጠሩ (1ኛ ቆሮ. 1፡1-9)

ጳውሎስ በመጀመሪያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የርኩሰትን ጽኑ ችግር አጥብቆ ተቃወመ፥ ሆኖም ግን ስለ ችግሩ የተናገረው ምንም ነገር አልነበረም። በዚህ ፈንታ አዎንታዊ አቀራረብ ተጠቀመና አማኞች በክርስቶስ ስላላቸው የከበረና የተቀደሰ ስፍራ አሳሰባቸው። ከቁጥር 1-9 ባለው ውስጥ እግዚአብሔር ስለሚያያት ቤተ ክርስቲያን ገለጸ፥ ከቁጥር 10-31 ባለው ውስጥ ደግሞ ሰዎች ስለሚያዩአት ቤተክርስቲያን አብራራ። በኢየሱስ ክርስቶስ *የያዝነው ስፍራ* በዕለታዊ ኑሮአችን ተተግብሮ መታየት ያለበት መሆን ሲገባው፥ ብዙ ጊዜ ግን ይህን አናደርግም።

በኢየሱስ ክርስቶስ ከተደረገልን ቅዱስ ጥሪ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን የሚኖሩአትን ባሕርያት ልብ በል።

*በእግዚአብሔር የተለየች* (1፡1-3)። በግሪክ ቋንቋ *ቤተክርስቲያን* ማለት «ተጠርተው የወጡ ሰዎች» ማለት ነው። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሁለት አድራሻዎች አሉአት። መልክዓ ምድራዊ አድራሻ ("በቆሮንቶስ") እና መንፈሳዊ አድራሻ ("በክርስቶስ ኢየሱስ ዘንድ")። ቤተ ክርስቲያን የተዋቀረችው ከቅዱሳን፥ ማለትም በእግዚአብሔር «ከተቀደሱ» ወይም «ከተለዩ» ሰዎች ነው። ቅዱስ ማለት ከኖረው የተቀደሰ ሕይወት የተነሣ ሰዎች የሚያከብሩት የሞተ ሰው ማለት አይደለም። የለም፥ ጳውሎስ የጻፈው *ሕያው* ለሆኑ ቅዱሳን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ካላቸው እምነት የተነሣ ለእግዚአብሔር ልዩ ፍስሐ እና ግልጋሎት ለተለዩ ሰዎች ነው።

በሌላ አባባል፥ ማንኛውም እውነተኛ አማኝ በእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ስለሆነ፥ ሁሉም አማኝ ቅዱስ ነው ማለት ነው።

አንድ ክርስቲያን ፎቶ አንሺ ጓደኛዬ «ስላነሣው» አንድ ቆንጆ ሠርግ አጫውቶኝ ነበር። ሙሽራዪቱና ሙሽራው ከቤተክርስቲያን

ተያይዘው ወጥተው፥ ወደ ተዘጋጀላቸው የሙሽራ መኪናቸው በማምራት ላይ እያሉ ድንገት ሳይታሰብ ሙሽራዪቱ ባሏን ጥላ በመንገድ ዳር ቆሞ ወደነበረ መኪና ከነፈች! ሞተሩ እየሠራ ሰውየውም መሪውን እንደ ጨበጠ ነበርና ምስኪኑን ባል ባለበት «የጨው -ዓምድ» አድርገውት ተያይዘው ፈረጠጡ። «የፈርጣጩ መኪና» ነጂ ለካስ «በፈለገው ማንኛውም ጊዜ ሊያገኛት እንደሚችል ይፎክር የነበረ» የቀድሞ የወንድ ጓደኛዋ ኖሯል። በዚህም ሊገመት እንደሚቻለው ባል ጋብቻው ውድቅ ሆኖበት ቀረ።

ወንድና ሴት ተጋቢዎች እርስ በርስ የፍቅር ቃል ኪዳን ከተለዋወጡ በኋላ አንዳቸው ለሌላቸው የተለዩ ይሆናሉ፥ በመሆኑም ከጋብቻ ውጭ የሆነ ማንኛውም ግንኙነት ኃጢአት የሞላበት ተግባር ነው። ልክ እንደዚሁ ክርስቲያን ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም የተሰጠ ነው፤ ለእርሱ እና ለእርሱ ብቻ የተለየ ነው። ከዚህም በላይ «የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ሁሉ ከሚጠሩት ጋር» (ቁ.2)። የዓለም አቀፍ ኅብረት ማለትም የቤተ ክርስቲያን አካልም ነው፥ የረከሰ እና ታማኝ ያልሆነ አማኝ ኃጢአት የሚሠራው በጌታ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በክርስቲያን ወገኖቹም ላይ ነው።

*በእግዚአብሔር ጸጋ ባለጠጎች የሆነች* (1:4-6)። ደኅንነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጸጋ ስጦታ ነው፤ ይሁንና ስትድን ወዲያው መንፈሳዊ ስጦታዎችም ታድለውሃል። (ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ በምዕራፍ 12-14 በዝርዝር ያስረዳል)። የግሪኩ ቃል ባለጠጎች እንድትሆኑ የተደረጋችሁ የሚለውን በጣም ሀብታም ሰው ብሎ ይፈታዋል። በተለይ ቆሮንቶሳውያን በመንፈሳዊ ስጦታዎች ባለጠጋዎች ነበሩ (2ኛ ቆሮ. 8:7)፥ ሆኖም ግን እነዚህን ስጦታዎች በመንፈሳዊ መንገድ አይጠቀሙባቸውም ነበር። እግዚአብሔር እኛን የመጥራቱ፥ የመለየቱና ባለጠጋ የማድረጉ እውነት የተቀደሰ አኗኗር እንድንኖር ሊያበረታታን ይገባል።

*የኢየሱስን መገለጥ የምትጠባበቅ (1:7)።* ጳውሎስ ስለዚህ እውነት በምዕራፍ 15 የሚለው ብዙ አለው። አዳኛቸውን የሚጠባበቁ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን ከነቀፋ በላይ አድርገው መያዝ ይፈልጋሉ (1ኛ ዮሐ. 2:28-3:3)።

*በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ የምትደገፍ (1:8-9)።* የእግዚአብሔር ሥራ በእነርሱ ውስጥ የጸና (ቁ.6)፥ ደግሞም በቃሉ በኩል ለእነርሱ የጸና ነበር። ይህ ቃል የንግድ ልውውጥ ዋስትና ለመስጠት የሚያገለግል የሕግ ቃልን ያመለክታል። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የገባውን «ውል» እንደሚጠብቅና እስከ ፍጻሜው እንደሚያድነን

ዋስትና የሚሰጥ የመንፈስ ምስክርነት በውስጣችን፥ የቃሉ ምስክርነት ደግሞ በፊታችን አለን። ይህ ዋስትና ያለ ጥርጥር ለኃጢአት ማመካኛ አይደለም! ይልቁኑ ለሚያድግ የፍቅር፥ የመተማመን እና የታዛዥነት ግንኙነት መሠረት ነው።

ታዲያ፥ እነዚህ ታላላቅ እውነቶች በገሃድ እየታዩ፥ የቆሮንቶስ ጉባኤ እንዴት አድርጎ በዓለም እና በሥጋ ሊጠመድ ቻለ? ቆሮንቶሳውያን የተመረጡ፥ ባለጠጎች የተደረጉ እና የተደላደሉ ሰዎች ነበሩ። ለእግዚአብሔር ክብር የተለዩ ቅዱሳን ነበሩ! ያሳዝናል፥ ተግባራቸው ከይዞታቸው የተለየ ሆነ።

ጳውሎስ *ኅብረት* የሚለውን ቃል በቁጥር 9 ላይ በመጥቀስ ሁለተኛውን የክርስቲያን ጥሪ ገጽታ አስተዋወቀ።

## ወደ ኅብረት የተጠራችሁ (1ኛ ቆሮ. 1፡10-25)

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የርኩሰት ችግር ከጠቀሰ በኋላ ወደ ክፍፍሉ ጉዳይ ተመለሰ። ክፍፍል በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል ሁልጊዜ የነበረ ችግር ነው። ስለሆነም ሁሉም የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ማለት ይቻላል ይህን ርእስ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ይነኩታል ወይም ይጠቅሱታል። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም እንኳ እርስ በርስ ሁልጊዜ የተስማሙበት ወቅት አልነበረም።

ከምንወዳቸው ቅዱሳን በከፍታ መኖር፥

ይህ በእርግጥም ነው ክብር!

በዝቅታ መኖር ከምናውቃቸው ቅዱሳን፥

ያ ደግሞ ሌላ ታሪክ ነው የሚከነክን!

በቁጥር 13፥ ጳውሎስ አንባቢዎቹን ሦስት አስፈላጊ ጥያቄዎችን ጠየቃቸው፥ ታዲያ እነዚህ ጥያቄዎች ለዚህ ረጅም አንቀጽ ቁልፍ ናቸው።

*ክርስቶስ ተከፋፍሎአልን?* (1፡10-13) የግሡ ትርጉም፥ «ክርስቶስ ተከፋፍሎ የተለያዩ ክፍሎቹ ለተለያዩ ሰዎች ታድለዋልን?» የሚል ነው። ይህ አሳብ ራሱ አስጠሊታ ስለሆነ መጣል የሚገባው ነው። ጳውሎስ አንድ ክርስቶስን፥ አጵሎስ ደግሞ የተለየ ክርስቶስን፥ ጴጥሮስም እንዲሁ ሌላ ክርስቶስን አልሰበኩም። ያለው አንድ ወንጌል እና አንድ አዳኝ ብቻ ነው (ገላ. 1፡6-9)። ታዲያ ቆሮንቶሳውያን ይህን የአራት አቅጣጫ ክፍፍል እንዴት ፈጠሩት? በመካከላቸው ለምን ጠብ ("ውድድር") ሆነ?

አንደኛው መልስ ወንጌልን ይመለከቱት የነበረው ከፍልስፍና አቅጣጫ ስለሆነ ነው። ቆሮንቶስ «ጥበባቸውን» በማስራጨት በሚሽቀዳደሙ አስተማሪዎች እና ፈላስፋዎች የተሞላች ነበረች።

ሌላኛው መልስ ሰብአዊ ተፈጥሮ ሰብአዊ መሪዎችን በመከተል የመርካቱ ጉዳይ ነው። ከሚረዱን፤ አገልግሎታቸው ከሚገባን እና ከሚያስደስተን መንፈሳውያን መሪዎች ራሳችንን የበለጠ ወደ ማዛመዱ እናዘነብላለን። እነርሱ አጽንኦት የሰጡት ከቃሉ *መልእክት* ይልቅ *ለመልእክተኛው* ነበር፤ ዓይኖቻቸውን ከጌታ ላይ አንሥተው በጌታ ባሪያ ላይ አደረጉ፤ ይህ ደግሞ ወደ ውድድር መራቸው።

ጳውሎስ በምዕራፍ 3 ላይ በእውነተኛ የእግዚአብሔር ባሪያዎች መካከል ውድድር ወይም እሽቅድምድም ሊኖር እንደማይችል ያመለክታል። ለቤተ ክርስቲያን አባላት መጋቢያንን ማወዳደር ኃጢአት ነው፥ ወይም አማኞች እንደ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሆናቸው ቀርቶ እንደ ሰዎች ደቀ መዛሙርት በመሆን ሰብአዊ መሪዎችን ከተከተሉአቸው ይህም ኃጢአት ነው። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ «ሰው አድናቂ ክፍሎች» ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ግንባር ለግንባር በሚጋጭ ዓመፅ ላይ ናቸው። ከፍተኛውን ስፍራ መያዝ ያለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ቆላ. 1፡18)።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ቅዱሳን በክርስቶስ ስላላቸው አንድነት አጽንኦት ለመስጠት በርካታ ቁልፍ ቃላትን ተጠቅሞአል። የአንድ ቤተሰብ አባላት መሆናቸውን ለአንባቢዎቹ ለማሳሰብ *ወንድሞች* ብሎ ጠራቸው። «የተባበራችሁ» የሚለው ቃል *የተሳሰረውን* የሰው አካል የሚገልጽ የሕክምና ቃል ነው። ስለዚህ፥ የአካሉ ብልቶች እንደመሆናቸው *የፍቅር* አንድነት ነበራቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም የታወቁ ነበሩ። ይህ ምናልባት ጥምቀታቸውን የሚያመለክት ነበር።

«የቀሎዔ ቤተሰቦች» አባላት እነማን እንደነበሩ አናውቅም፥ ሆኖም ግን ለጽናታቸውና ለመሰጠታቸው እናደንቃቸዋለን። ችግሮችን ለመሸሸግ አልሞከሩም። ተጨንቀውባቸው ስለነበር ከችግሮቻቸው ጋር ወደ ትክክለኛው ሰው ቀረቡ፤ እንዲሁም ጳውሎስ ስለ እነርሱ መጥቀሱ አላሸማቀቃቸውም። ይህ በእነርሱ ዘንድ ብዙ ጊዜ በየቤተክርስቲያኑ እንደምናያቸው -ችግሩን የባሰ እንጂ ምንም የተሻለ እንደማያደርጉ ድርጊቶች «ምሥጢራዊ ጉዳይ» አልነበረም።

ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን የመሠረተ አገልጋይ ነበር፤ በመሆኑም አብዛኛዎቹ ምእመናን በእርሱ አገልግሎት የተለወጡ ሊሆኑ ይችላሉ። አጵሎስ ጳውሎስን የተከተለ ሲሆን (የሐዋ. 18፡24-28)፥ ውጤታማ

አገልግሎትም ነበረው። ጴጥሮስ (ኬፋ) 1ኛ ቆሮ. 9፡5 ከሚዘግበው በቀር ቆሮንቶስን ስለመጎብኘቱ ምንም መረጃ የለንም። እነዚህ ሰዎች እያንዳንዳቸው የተለያዩ ባሕርያት እና ቃሉን የሚያገለግሉበትም የተለያዩ አቀራረቦች ነበሩአቸው፤ *እንዲሁም ሆኖ ግን አንድ ነበሩ* (3፡3–8፤ 4፡6)።

*ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?* (1፡13–17) በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ጥምቀት አስፈላጊ ነገር እንደነበር ልብ በል። አንድ ኃጢአተኛ ክርስቶስን አምኖ በሚጠመቅበት ጊዜ፥ ራሱን ከቀድሞ ሕይወቱ ስለሚለይ ብዙ ጊዜ በቤተሰቡ እና በጓደኞቹ ዘንድ ተቀባይነት ያጣ ነበር። በዚያን ዘመን መጠመቅ አንድን ነገር (ዋጋ) ያስከፍል ነበር።

ኢየሱስ ሰዎችን እንዳላጠመቀ ሁሉ (ዮሐ. 4፡1–2)፥ ጴጥሮስ (የሐዋ. 10፡48) እና ጳውሎስም እንዲሁ አዳዲስ አማኞችን እንዲያጠምቁ ለሥራ ተባባሪዎቻቸው ተዉላቸው። በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እስከምታድግ ድረስ፥ ጳውሎስ ጥቂት የማጥመቅ ሥራ ሠርቶ ነበር፤ ሆኖም ያ የእርሱ ዋነኛ አገልግሎት አልነበረም። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚታየው ጳውሎስ ጥምቀትን ማሳነሱ ሳይሆን፥ ይልቁንም በተገቢ ስፍራው ማስቀመጡ ነበር። ምክንያቱም ቆሮንቶሳውያን የጥምቀትን ተግባር በጣም ያዋድዱት ስለነበር ነው። «እኔ በአጵሎስ ተጠምቄአለሁ!» በማለት አንዱ ሲመጻደቅ፥ ሌላው ደግሞ «የለም እኔስ በጳውሎስ ነው የተጠመቅሁት!» ይል ነበር።

ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር የማንንም ስም ከጥምቀትህ ጋር ማዛመዱ አግባብ አይደለም። ይህን ማድረግ ክፍፍልን መፍጠር ነው። ድርጊቱ ሁሉ በጣም አስፈላጊ ይመስል፥ ለጥምቀታቸው የተለየ ሰባኪ፥ የተለየ ውኃ (ብዙውን ጊዜ ከዮርዳኖስ ወንዝ የመጣ)፥ የተለየ ቀን የሚጠቀሙ ሰዎች ስለመኖራቸው የተጻፈ ነገር አንብቤአለሁ! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማክበርና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በማዳበር ፈንታ፥ እነዚህ ሰዎች ግለሰቦችን ከፍ ከፍ በማድረግ ክፍፍልን ይፈጥራሉ።

ቀርስጶስ በቆሮንቶስ ለነበረው ምኵራብ አለቃ ነበር (የሐዋ. 18፡8)፤ ጋይዮስ ደግሞ ምናልባት ጳውሎስ የሮሜን መልእክት በሚጽፍበት ጊዜ አብሮት የኖረ ሰው ሳይሆን አይቀርም (ሮሜ 16፡23)። ስለ «የእስጢፋኖስ ቤተሰዎች» (1ኛ ቆሮ. 1፡16) ምናልባት በ 1ኛ ቆሮ. 16፡15–18 በከፊል ተገልጾአል። በእግዚአብሔር መጽሐፍ መጻፋቸው በቂ ስለነበር፥ ጳውሎስ ያጠመቃቸውን ሰዎች ስም ሁሉ በመዝገብ የያዘ አይመስልም።

*ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን?* (1፡18–25) በቁጥር 17 የተጠቀሰው መስቀል ከሰው ጥበብ ደካማነት አንፃር የወንጌል ኃይል የተገለጸበትን ይህን ረጅም ክፍል አስተዋወቀ። በቤተ ክርስቲያን የተከሰተውን ይህን የክፍፍል ችግር ጳውሎስ እንዴት እንዳስተናገደው ማየቱ በጣም አጓጊ ነው። በመጀመሪያ፥ አንድ አዳኝና አንድ አካል በማለት ወደ ክርስቶስ አንድነት አመለከተ። ቀጥሎ ስለ ጥምቀታቸው አሳሰባቸው፤ ይህም በክርስቶስ አካል የመጠመቃቸው አምሳል ነበረ (12፡13)። እንዲህ አድርጎ፥ ወደ መስቀል አደረሳቸው።

ስቅለት ዘግናኝ ሞት ብቻ አልነበረም፤ የውርደት ሞትም እንጂ። ሮማዊ ዜጋን መስቀል ሕገወጥ ነበር። እኛ ዛሬ እራት እየበላን፥ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የጀርመኑ ሂትለር አይሁዳውያንን ስለፈጀበት ስለ መርዝ ጋዝ ክፍል ወይም በአሜሪካን የሞት ቅጣት ስለሚፈጸምበት ስለ ኤሌክትሪክ ወንበር እንደማንነጋገር ሁሉ፥ በጨዋ ማኅበረሰብ ውስጥ ስቅለት ተጠቅሶ አይታወቅም።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ቁልፍ ቃል *ጥበብ* ሲሆን፤ ስምንት ጊዜ ተጠቅሶአል። ጳውሎስ የሚናገረው ቁልፍ አሳብ ሰብአዊውን ጥበብ ከተገለጠው የእግዚአብሔር መልእክት ጋር ለመቀየጥ እንዳንዳፈር ነው። ስለ ጥበብ የሚናገረው መላው ክፍል (1፡17–2፡16) በተገለጠው የእግዚአብሔር ቃልና በሰዎች ጥበብ መካከል በርከት ያሉ ንጽጽሮችን ይሰጣል።

የእግዚአብሔር ጥበብ በመጀመሪያ የተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነው፤ ይሁንና ይህን ሁሉም ሰው አያየውም። ጳውሎስ መስቀልን በተመለከተ ሦስት የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉ አመልክቶአል።

*አንዳንዶች በመስቀል ይሰናከላሉ።* ይህ የአይሁዶች አመለካከት ነበር፤ ምክንያቱም አጽንኦታቸው በተአምራታዊ ምልክቶች ላይ ስለሆነ መስቀል ደግሞ ደካማነት ሆነባቸው። ከግብፅ መውጣታቸው አንሥቶ እስከ ኤልያስና ኤልሳዕ ዘመን ድረስ የአይሁድ ታሪክ በተአምራት የተሞላ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሚያገለግልበት ወቅት፥ የአይሁድ መሪዎች በተደጋጋሚ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠይቀውት ነበር፤ እርሱ ግን እምቢ አለ።

የአይሁድ ሕዝብ የራሳቸውን የተቀደሱ መጻሕፍት አላስተዋሉአቸውም ነበር። ጽኑ ኃይል ተላብሶ የሚመጣ እና ጠላቶቻቸውን በሞላ ድባቅ የሚመታ መሢሕ ይጠባበቁ ነበር። ይህ ሰው መንግሥትን አቋቁሞ ለእስራኤል ክብርን የሚመልስ መሆን

ነበረበት። በሐዋርያት ሥራ 1:6 ላይ የተነሣው የሐዋርያት ጥያቄ ይህ ተስፋ በአይሁድ መካከል ምን ያክል ጠንካራ እንደነበረ ያሳያል።

በተመሳሳይ ጊዜ፥ ጸሐፊዎቻቸው መሢሑ እንደሚሠቃይ እና እንደሚሞትም ከብሉይ ኪዳን ያውቁ ነበር። እንደ መዝሙረ ዳዊት 22 እና ኢሳይያስ 53 ያሉ ምንባቦች ያመለከቱት ወደተለየ ዓይነት መሢሕ ነበር፥ ጠበብቱም እነዚህን ሁለት ተጻራሪ መሰል ገጽታዎች ሊያስታርቁ አልቻሉም። መሢሓቸው ወደ ክብሩ ከመግባቱ በፊት መሠቃየት እና መሞት እንደነበረበት (ሉቃ. 24:13–35ን ተመልከት)፥ እንዲሁም የሚመጣውን የመሢሑ መንግሥት የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንደሚቀድመው አልተረዱም ነበር።

አይሁዶች ኃይልን እና ታላቅ ክብርን ይፈልጉ ስለነበር የመስቀል ደካማነት ዕንቅፋት ሆነባቸው። የተራ ወንጀለኛን የውርደት ሞት በሞተ የናዝሬቱ ሥራአጥ አናጢ ላይ ሰው እንዴት እምነቱን መጣል ይቻል? ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል «የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው» (ሮሜ 1:16)። መስቀል የድካም ምስክርነት ከመሆን ይልቅ ከፍተኛ የኃይል መሣሪያ ነው! ለነገሩ፥ «የእግዚአብሔር ድካም [በመስቀል] ከሰው ይልቅ ይበረታልና» (1ኛ ቆሮ. 1:25)።

አንዳንዶች በመስቀል ይስቃሉ። ይህ የግሪኮች ምላሽ ነበር። ለእነርሱ መስቀሉ ሞኝነት ነበር። ግሪኮች ጥበብን ያጠብቃሉ፤ ዛሬም እንኳ የግሪክ ፈላስፋዎችን ጥልቅ ጽሑፎች እናጠናለን። ሆኖም ግን እነርሱ በመስቀል ውስጥ ምንም ጥበብ አላዩበትም፥ ምክንያቱም መስቀልን የተመለከቱት በሥጋዊ ዓይን ነበር። ከእግዚአብሔር አቅጣጫ ተመልክተውት ቢሆን ኖሮ፥ ታላቅ የእግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅድ የተገለጠበትን ጥበብ ባወቁት ነበር።

ጳውሎስ ሦስት ሰዎች ምስክርነት እንዲሰጡ ጠየቀ። ጠቢቡ (ሊቁ)፥ ጸሐፊው (ተርጓሚው እና ዘጋቢው)፥ እና ተቀናቃኙ (ፈላስፋው እና ተከራካሪው)። ሁላቸውንም አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው፥ በሰብአዊ ጥበብ ባካሄዳችሁት ጥናት እግዚአብሔርን በግል ወደ ማወቅ ደርሳችኋልን? ሁላቸውም አይደለም ብለው መመለስ አለባቸው! መስቀሉን እንደ ሞኝነት መቁጠራቸው እና በእርሱም ላይ መሳቃቸው ራሱ እየጠፉ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ነው።

እግዚአብሔር ለሰዎች ጥበብ ትልቅ «ዜሮ–ክስረት» መስጠቱን ለማረጋገጥ ጳውሎስ በቁጥር 19 ላይ ኢሳይያስ 29:14 ን ይጠቅሳል። በማርስ ኮረብታ (አርዮስፋጎስ) ንግግሩ ጳውሎስ የግሪክ እና የሮማውያን ታሪክ «ያለማወቅ ዘመን» እንደነበር ለፈላስፋዎች ለመንገር ደፍሮአል (የሐዋ. 17:30)። ምንም አያውቁም ማለቱ

አልነበረም፤ ምክንያቱም የግሪክ ተመራማሪዎች አንዳንድ ውጤቶችን ማስመዝገባቸውን በሚገባ ያውቅ ነበርና። ይሁንና ጥበባቸው እግዚአብሔርን እንዲያገኙት እና ደኅንነትንም እንዲለማመዱ አላስቻላቸውም።

*አንዳንዶች የመስቀሉን ኃይል እና ጥበብ የሚያምኑ እና የሚለማመዱ ናቸው።* ጳውሎስ ከአይሁድ አድማጭ ወደ ግሪክ አድማጭ በሚመለስበት ጊዜ መልእክቱን አልቀየረም። የተሰቀለውን ክርስቶስን ሰበከ እንጂ። «የስብከት ሞኝነት» (1ኛ ቆሮ. 1:21) ማለት የስብከት *ተግባር* ሞኝነት ነው ማለት አይደለም፤ ይልቅ የመልእክቱ ይዘት ማለት እንጂ። አዲሱ ዓለም አቀፍ እትም (NIV) «በተሰበከው ነገር ሞኝነት ምክንያት» በማለት ያስቀምጠዋል፤ ይህ ደግሞ እውነት ነው።

በእግዚአብሔር ጸጋ የተጠሩ፥ እና በእምነት ምላሽ የሰጡ (2ኛ ተሰ. 2:13−14ን ተመልከት)፥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ መሆኑን ያውቁታል። ይህ የክብሮች በረቱ፥ ወይም የቤተ መቅደሱ፥ ወይም የገበያ ስፍራው ክርስቶስ ሳይሆን− ነገር ግን የመስቀሉ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር የሰውን ጥበብ ሞኝነት እና የሰውን ኃይል ደካማነት የገለጠው በክርስቶስ ሞት ነው።

ወደ ኅብረቱ የተጠራነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለን አንድነት ነው። እርሱ ለእኛ ሞተ፤ በስሙ ተጠመቅን፤ ከእርሱ መስቀል ጋር ራሳችንን አንድ አደረግን። ይህ ለመንፈሳዊ ኅብረት እንዴት ያለ ድንቅ መሠረት ነው!

## እግዚአብሔርን ለማክበር የተጠራችሁ (1ኛ ቆሮ. 1:26−31)

ቆሮንቶሳውያን በትዕቢት «የመነፋት» አዝማሚያ ነበራቸው (4:6፥18−19፤ 5:2)። ነገር ግን የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል ራስን በትምክህት ለመሙላት ምንም ስፍራ አይሰጥም። መልካችን፥ ማኅበራዊ አቋማችን፥ ደረጃችን፥ የተፈጥሮ ቅርሳችን፥ ወይም የገንዘብ ዓቅማችን የእግዚአብሔርን አድናቆት ወይም አክብሮት አያተርፍልንም። ጳውሎስ *ለማንም* ሳይሆን *ለብዙዎች* እንደ ጻፈ ልብ በል። በአዲስ ኪዳን «ከፍተኛ ማኅበራዊ አቋም» ያላቸውን ጥቂት አማኞች እናገኛለን፤ ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነቶቹ ብዙ አይደሉም። ለአዲስ አማኞች ጳውሎስ የሰጠው አገላለጽ በእርግጥ የበለጠ አልነበረም (6:9−11)።

*ጳውሎስ ምን እንደነበሩ አስታወሳቸው* (1:26)። ጥበበኞች፥ ኃያል፥ ወይም የተከበሩ አልነበሩም። እግዚአብሔር የጠራቸው የነበራቸውን መነሻ *ምክንያት* አድርጎ ሳይሆን *ያንን ከቁጥር ሳያስገባ* ነበር!

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በመሠረቱ የተውጣጣችው በጣም የከፉ ኃጢአተኞች ከነበሩ ተራ ሰዎች ነበር። ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት በጣም ተመጻዳቂ ሰው ነበር፤ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ሃይማኖቱን መተው ግድ ሆነበት! ቆሮንቶሳውያን በሌላኛው ጽንፍ ነበሩ፤ ቢሆንም ቅሉ እግዚአብሔር ደርሶ ማዳን እስከሚያዳግተው ድረስ በጣም ኃጢአተኞች አልነበሩም።

ሮበርት ሙሬይ ማክቼይን የተባለ ብፁዕ የእስኮቲሽ መጋቢ አንድ ቀን ለአንዲት ሴት የወንጌል ትራክት በሰጣት ጊዜ ሴቲቱ በጣም ተቀየመችው። በዚሁ ስሜት ሆና «ማን እንደሆንሁ አላወቅህም!» አለችው። ማክቼይንም መለሰና፥ «እሜቴ፥ የፍርድ ቀን እየመጣ ነው፥ በዚያ ቀን የእርስዎ ማንነት የሚፈይድ አይሆንም» አላት።

*ጳውሎስ ቆሮንቶሳውያንን እግዚአብሔር ለምን እንደጠራቻው አስታወሳቸው* (1:27-29)። እግዚአብሔር ለሚታበየው ዓለም ጉድለታቸውን እና የእርሱን ጸጋ ያሳይ ዘንድ ሞኙን፥ ደካማውን፥ ምናምንቴውን («ከዝቅተኛ የተወለደውን») እና የተናቀውን መረጠ። ጠፊዋ ዓለም የዘር ሐረግን፥ ማኅበራዊ አቋምን፥ ጥሪታዊ ስኬትን፥ ኃይልን እና እውቅናን ታደንቃለች። ነገር ግን ከእነዚህ ውስጥ የትኛውም ለዘላለም ሕይወት ዋስትናን አይሰጥም።

መልእክቱ እና በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው የእግዚአብሔር የጸጋ ተአምር የዚህችን ዓለም ታላላቅ እና ኃያል ሰዎች ያጣጥላቸዋል (ያሳፍራቸዋል)። የዚህች ዓለም ጥበበኞች እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንዴት ቅዱሳን አድርጎ እንደሚለውጣቸው ሊገባቸው አይችልም። የዚህች ዓለም ኃያላንም ቢሆኑ ይህን ተአምሩን የመድገም ዓቅም የላቸውም። የእግዚአብሔር «ሞኝነት» ጥበበኛውን ያሳፍረዋል፤ የእግዚአብሔር «ድካም» ኃያሉን ያሳፍረዋል!

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መዛግብት ሕይወታቸው በወንጌል ኃይል በተለወጠ ታላላቅ ኃጢአተኞች ዝክረ-ነገር የተሞላ ነው። እንደ አብዛኛዎቹ መጋቢያን እና ሰባኪዎች አገልግሎት ሁሉ፥ በእኔ አገልግሎትም የሕግ እና የሥነ ልቡና ጠበብት መረዳት ያልቻሉት አስደናቂ ነገሮች ሲከሰቱ አይቻለሁ። ወጣት አጥፊዎች የተዋጣላቸው ተማሪዎች እና ጠቃሚ ዜጋዎች ሲሆኑ አይተናል። ፍርድ ቤቶች አፋቸውን እስኪይዙ ድረስ ትዳሮች ሕይወት ሲዘሩ እና ወና የቀሩ ቤቶችም ዳግም ሲሟሟቁ ተመልክተናል።

እግዚአብሔር የዚህን የዛሬውን ዓለም ሥርዓት፥ የፍልስፍናውን እና የሃይማኖቱንም ሞኝነት እና ደካማነት የሚገልጠው ለምንድን ነው? «ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ» (ቁ. 29) ነው።

ደኅንነት ሙሉ ለሙሉ በጸጋ መሆን አለበት፤ አለበለዚያ እግዚአብሔር ክብሩን አይቀዳጅም።

ጳውሎስ ለቆሮንቶሳውያን ለማስተላለፍ የሚሻው ይህን እውነት ነው፤ ምክንያቱም ጥፋታቸው በሰው የመመካት ነበር (3:21)። በሰዎች፥ እንደ ጴጥሮስ፥ ጳውሎስ እና አጵሎስ ባሉ የእግዚአብሔር ሰዎችም እንኳ የምንመካ ከሆነ– እግዚአብሔር ብቻውን ሊቀዳጅ የሚገባውን ክብር እየተናጠቅን ነን ማለት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርግ የነበረው ይህ ኃጢአታዊ የትምክህት አመለካከት ነው።

*በመጨረሻም፥ ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ የነበራቸውን ሁሉ አስታወሳቸው* (1:30–31)። እያንዳንዱ አማኝ «በክርስቶስ» ስለሆነ እና የሚያስፈልገው ሁሉ ስላለው እርስ በርስ መወዳደር ወይም ራስን ከሌላው ማነጻጸር ለምን ያስፈልጋል? ሁሉንም ያደረገው ጌታ ነው! «የሚመካ በጌታ ይመካ» (ቁጥር 31 ከኤርምያስ 9:24 የተወሰደ ሲሆን እንደገና በ 2ኛ ቆሮ. 10:17 ተጠቅሶአል)።

የሚያስፈልጉን መንፈሳዊ በረከቶች ከእጃችን የሚያፈተልኩ ረቂቅ ነገሮች አይደሉም፤ ሁሉም በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እርሱ ጥበባችን ነው (ቆላ. 2:3)፥ ጽድቃችን ነው (2ኛ ቆሮ. 5:21)፥ ቅድስናችን ነው (ዮሐ. 17:19)፥ እና ቤዛችን ነው (ሮሜ 3:24)።

በእርግጥ እዚህ ላይ እግዚአብሔር በክርስቶስ ባለን ጽድቅ፥ ቅድስና እና ቤዛነት ጥበቡን እንደሚያሳይ አጽንኦት ተደርጎበታል። እነዚህ *ሦስ* መለኮታዊ ቃላት እያንዳንዳቸው ለክርስቲያኖች ልዩ ትርጉም አላቸው። *ጽድቅ* በእግዚአብሔር ፊት ያለንን አቋም የሚመለከት ነው። ጸድቀናል። በኢየሱስ ክርስቶስ እንደጸደቅን እግዚአብሔር ይናገራል። ደግሞም *ተቀድሰናል*፥ የእግዚአብሔር ገንዘብ በመሆን እና እርሱን ለማገልገል ተለይተናል። *ቤዛነት* በአጽንኦት የሚያሳየው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ዋጋን በመክፈሉ አርነት መውጣታችንን ነው። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ወደሚጠናቀቀው ፍጹም ቤዛነት ይመራናል።

ስለዚህ በአንድ መልኩ፥ እዚህ ላይ ሦስት የደኅንነት ጊዜያት አሉን ከኃጢአት ቅጣት ድነናል (ጽድቅ)፤ ከኃጢአት ኃይል እየዳንን ነው (ቅድስና)፤ ከኃጢአት ህልውና እንድናለን (ቤዛነት)። በመሆኑም እያንዳንዱ አማኝ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እነዚህ ሁሉ በረከቶች አሉት!

እንግዲህ፥ ለምን በሰው እንመካለን? አንተ የሌለህ ጳውሎስ ያለው ምንድን ነው? ጴጥሮስ ከአንተ ይልቅ ክርስቶስን በብዙ ለራሱ

ያደርጋልን? (ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን በብዙ የራሱ አደረገ ማለት ከሆነ የሚመስል ነገር ነው፤ ያ ግን ሌላ ጉዳይ ነው!) መመካት የሚገባን በጌታ እንጂ በራሳችን ወይም በመንፈሳዊ መሪዎቻችን አይደለም።

ይህን ምዕራፍ በምትከልስበት ጊዜ፥ ቆሮንቶሳውያን ይፈጽሙአቸው የነበሩትን ስሕተቶች ማየት ትችላለህ፤ እነዚህ ስሕተቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች እንዲፈጠሩ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። የተቀደሰውን ጥሪያቸውን የሚመጥን አኗኗር አልነበራቸውም፤ ይልቁኑ ይከተሉት የነበረው የዓለምን ልኬቶች ነበር። ወደሚደነቀው የጌታ እና የእርስ በርስ መንፈሳዊ ኅብረት የመጠራታቸውን እውነታ ችላ አሉት። በዚህ ፈንታ ከሰብአዊ መሪዎች ጋር ያብሩና በዚህም ተግባራቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍልን ይፈጥሩ ነበር። እግዚአብሔርን ጸጋውን ከፍ ከፍ ከማድረግ ይልቅ እንደፈለጋቸው ያደርጉና ሰዎችን ያሞካሹ ነበር።

እነርሱ የረከሰች፥ የተከፋፈለችና ጸጋዋን የተገፈፈች ቤተ ክርስቲያን ነበሩ!

ሆኖም ግን፥ በእነርሱ ላይ ፍርድን ከማሳለፋችን በፊት የራሳችንን ቤተ ክርስቲያንና የግል ሕይወታችንን መመርመር ይገባናል። እኛም እንደ እነርሱ ቅዱስ ለመሆን፥ ወደ ኅብረቱና እግዚአብሔርን ለማክበር ተጠርተናል።

ለዚህ ጥሪ ብቁ ሆነን እየኖርን ነው ወይ?

# ስለ ክርስቲያናዊ መልእክት. . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 2*

ባለቤቴ መኪናችንን እየነዳች አጠገቧ ተቀምጬ ወደ ቺካጎ እየሄድን ሳለ አንድ አሳታሚ እንድገመግመው የሰጠኝን የአንድ ደራሲ መጽሐፍ አነብብ ነበር። አልፎ አልፎ የማጉተምተም ከዚያም ማጉረምረም አይሉት ማቃሰት የሚመስል ድምፅ አሰማ ነበር፤ በመጨረሻም ራሴን ነቀነቅሁና፥ «አ፥ ፍጹም! ይህን አላምንም!» አልኩኝ።

«መጽሐፉን ያልወደድህ መሰለኝ፥ የሆነ ችግር አለው?» አለችኝ።

«አላምሮ ነዋ!» አልኳት። «ሁሉም ነገር የተበላሸ ነው ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም ይህ ሰው የወንጌሉ መልእክት በእርግጥ ምን እንደሆነ አያውቅም!»

ይሁንና ደራሲው ለወንጌል ታማኝ የነበረበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን በዓመታት መካከል፥ ወንጌልን በፍልስፍናዊ (ይመስለኛል የፖለቲካ) አመለካከት ማየት ጀመረ። ውጤቱ ጭራሽኑ ወንጌል ያልሆነ ቅይጥ መልእክት ነበር።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ያገለግል በነበረ ጊዜ፥ ከጌታችን የተቀበለውን ተልእኮ ይታዘዝና ወንጌልንም ይሰብክ ነበር። በማቴዎስ 28፡18–20 እና በሐዋርያት ሥራ 18፡ 1–11 መካከል ቆንጆ መመሳሰል አለ።

| ክርስቶስ የሰጠው ሥራ (ማቴ. 28፡18–20) | የጳውሎስ አገልግሎት (የሐዋ. 18፡1–11) |
|---|---|
| «እንግዲህ ሂዱና» (ቁ. 19)<br>«ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» [አስተምሩ](ቁ.19)<br>«እያጠመቃችኋቸው»(ቁ.19)<br>«እያስተማራችኋቸው» (ቁ.20)<br>«እነሆም እኔ . . .ከእናንተ ጋር ነኝ» (ቁ. 20) | ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ መጣ (ቁ.1). . .<br>ብዙ በሰሙ ጊዜ አምነው (ቁ. 8)<br>ተጠመቁ (ቁ. 8)<br>በመካከላቸውም የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ ዓመት ከስድስት ወር ተቀመጠ (ቁ.11)<br>እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ (ቁ. 10) |

በቆሮንቶስ የሆነው ዛሬም በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየሆነ ነው። ሰዎች ፍልስፍናን (የሰውን ጥበብ) ከተገለጠው የእግዚአብሔር መልእክት ጋር እየቀየጡት ነው። ይህ ደግሞ ግራ መጋባትን እና ክፍፍልን እየፈጠረ ነው። የተለያዩ ሰባኪያን ለእግዚአብሔር ቃል የተለየ አቀራረብ አላቸው። አንዳንዶቹማ የራሳቸውን ቃል እየፈለሰፉ ናቸው!

ጳውሎስ የወንጌል መልእክት ሦስት ፍሬ አሳቦችን ካብራራ በኋላ አንባቢዎቹ ወደ እነዚህ ፍሬ አሳቦች እንዲመለሱ ያበረታታቸዋል።

## ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት ማዕከል ያደርጋል (1ኛ ቆሮ. 2:1–5)።

*ጳውሎስ አቀራረቡን ለቆሮንቶሳውያን ያስታውሳቸዋል* (2:1–2)። «እኔም፥» የሚለው መክፈቻ ቃል ሊተረጎም የሚችለው በ 1:31 – በእግዚአብሔር ይመካ በሚለው መሠረት «እንዲስማማ» ሆኖ ነው። ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ የመጣው እግዚአብሔርን ለማክበር ወይም ከፍ ለማድረግ እንጂ ራሱን ከፍ ሊያደርግ (በእርሱ እንዲመኩበት) ወይም ሃይማኖታዊ «አምካሾችን» ሊመሠርት አልነበረም።

ተዘዋዋሪ ፈላስፋዎች እና አስተማሪዎች ተከታዮችን ለማፍራት በገዛ ጥበባቸው እና በማራኪ አነጋገራቸው ላይ ይመኩ ነበር። የቆሮንቶስ ከተማ እንዲህ ባሉ «ቀልብ ዘራፊዎች» የተሞላች ነበረች። ጳውሎስ ግን በማራኪ አነጋገር ወይም በቀልጣፋ ክርክሮች አልተመካም፤ እንዲሁ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ቃል አወጀ። እርሱ አምባሳደር እንጂ «ክርስቲያን ደላላ» አልነበረም።

ጳውሎስ አስደናቂ ንግግር እና ፍልስፍና ተጠቅሞ ቢሆን ኖሮ ራሱን ከፍ አድርጎ ለማወጅ ያቀደውን ክርስቶስን ይደብቀው ነበር! «የክርስቶስም መስቀል ከንቱ እንዳይሆን፥ በሰዎች የንግግር ጥበብ አልሰብክም» (1:17– አዲሱ መደበኛ ትርጉም)።

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ከምስባኩ በስተጀርባ በውብ ቀለማት ያሸበረቀ የመስተዋት መስኮት ነበር። ኢየሱስ በመስቀል እንደተሰቀለ ተሥሎበታል። አንድ እሑድ ዕለት ዘወትር ከሚያገለግለው መጋቢ በጣም አጠር የሚል እንግዳ ሰው አገለገለ። በዚህ ጊዜ አንዲት ትንሽ ልጃገረድ ያን እንግዳ ሰው ለጥቂት ጊዜ ሲናገር ከሰማችው በኋላ፥ ወደ እናቷ ዘወር ብላ እንዲህ ስትል ጠየቀቻት፤ «ብዙ ጊዜ እዚያ ላይ ቆሞ ኢየሱስን ማየት እንዳንችል የሚያደርገው ሰው ዛሬ የት ሄደ?»

በጣም ብዙ የሆኑ የቃሉ ሰባኪያን ራሳቸውን እና ስጦታቸውን ስለሚያጎሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ከመግለጥ ይጎድላሉ። ጳውሎስ

በክርስቶስ መስቀል ስለተመካ (ገላ. 6:14) የመልእክቱ ማዕከል አደረገው።

*ከዚያም ጳውሎስ ስለ ዝንባሌው ቆሮንቶሳውያንን አሳሰባቸው* (2:3–4)። ሐዋርያ ቢሆንም፥ ጳውሎስ ወደ እነርሱ የመጣው እንደ ትሑት አገልጋይ ነበር። በራሱ አልተመካም ነበር፥ ክርስቶስ ሁሉን ይሆን ዘንድ ራሱን ባዶ አደረገ። በተከታይ ዓመታት፥ ጳውሎስ ይህን ነገር እንደገና አንሥቶ ቆሮንቶስን ከወረሯት የሐሰት አስተማሪዎች (2ኛ ቆሮ. 10:1–12) ጋር ራሱን አነጻጽሮበታል። በሚደክምበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር እንደሚያበረታው ጳውሎስ ተምሮአል።

ጳውሎስ ይመካ የነበረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ላይ ነው። ለአገልግሎቱ ኃይልን የሰጠው ልምምዱ ወይም ችሎታው አልነበረም፤ ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነበር። የእርሱ ስብከት «ጭብጥ መግለጫ» እንጂ «የድርጊት ስኬት» አልነበረም። *ጭብጥ መግለጫ* የሚለው ሐረግ ሲተረጎም «በችሎት የቀረበን ሕጋዊ ማረጋገጫ» *ያመለክታል*። መንፈስ ቅዱስ የጳውሎስን ስብከት ሕይወትን ለመለወጥ ተጠቅሞበታል፤ ስለሆነም መልእክቱ ከእግዚአብሔር ለመሆኑ የሚፈለገው ማረጋገጫ ይኸው ነበር። በከፋት የተሞሉ ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር ኃይል ተለውጠዋል! (1ኛ ቆሮ. 6:9–11)።

ይሁን እንጂ፥ ጳውሎስ አገልጋዮች ሆን ብለው አድበስብሰው ይስበኩ፥ ወይም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስጦታዎች ይተዉ ማለቱ እንዳይደለ ልብ ልንል ይገባል። እንደነ ቻርልስ ስፐርጀን እና ጆርጅ ዋይትፊልድ ያሉ ሰዎች ኃይል የተላበሱ ቃላትን የሚያዥጎደጉዱ ተናጋሪዎች ነበሩ፤ *ሆኖም ግን በተፈጥሮአዊ ችሎታዎቻቸው አልተመኩም*። በአድማጮቻቸው ልብ መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራ ተማመኑ፤ እርሱም ደግሞ ሠራ። ቃሉን የሚያገለግሉ መዘጋጀትና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ማንኛውንም ስጦታ መጠቀም አለባቸው– ሆኖም ግን ትምክህትን በራሳቸው ላይ ማኖር የለባቸውም። (2ኛ ቆሮ. 3:5ን ተመልከት።)

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ *ስለ ዓላማው* አሳሰባቸው (2:5)። በእግዚአብሔር እንጂ እግዚአብሔር በላከው መልእክተኛ እንዳይተማመኑ ፍላጎቱ ነበር። በሰብአዊ ጥበብ ላይ ተመክቶ የደኅንነትን ዕቅድ እንደ አንድ ሥርዓተ ፍልስፍና አቅርቦት ቢሆን ኖሮ፥ ያኔ ቆሮንቶሳውያን እምነታቸውን *በገለጻ* ላይ ባደረጉ ነበር። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በእግዚአብሔር ኃይል ስላወጀ፥ በእርሱ አማካኝነት *ያመኑት* እምነታቸውን *ያሳረፉት ጭብጥ መግለጫ*

ላይ ስለነበር እግዚአብሔር በሕይወታቸው መሥራቱን ተለማምደውታል።

ከዓመታት በፊት፥ አንድ ብልኅ ክርስቲያን እንዲህ አለኝ፥ «ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በምትመራበት ጊዜ፥ የዳናችሁት ይህን ወይም ያን ስላደረጋችሁ ነው ብለህ ከቶ አትንገራቸው። ለሰዎች እንደዳኑ መመስከር የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። እርሱ በሥራ ላይ ካልሆነ ደኅንነት ሊመጣ አይችልም።» እውነትም በሳል ምክር ነው!

በመጋቢነት አገለግል በነበርኩበት ቤተክርስቲያን በጣም ጥሩ የሆነ በታማኝነት የሚከታተል ባለሙያ ሰው ነበረ– ይህ ሰው ያልዳነ ሆኖም ግን ወንጌልን የማይቃወም ነበር። እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ማድመጡን ቀጥሎ ሳለ ብዙዎቻችን እንጸልይለት ነበር። አንድ ቀን የእርሱ ጓደኛ የሆነ ክርስቲያን ሰው ወደ ክርስቶስ እመልሰዋለሁ ወይ ይለይለታል ብሎ ወሰነ! ለበርካታ ሰዓታት የክርክር ውርጅብኝ አወረደበት እና ሰውየው በመጨረሻ «የኃጢአተኛ ሰው ጸሎት ጸለየ።» ከዚያም ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣቱን አቆመ! ለምን? ምክንያቱም እውነት ያልሆነን ነገር እንዲቀበል ስለነዘነዘው እና እስከ መጨረሻ ሊቀጥል አለመቻሉን ስለተገነዘበ ነበር። በኋላ ግን ክርስቶስን አመነ እና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፤ የደኅንነትን ማረጋገጫ አገኘ። እስከዚያ ድረስ፥ ድነሃል ወይ ብሎ ማንም ቢጠይቀው፥ «አዎ–ቶም ድነሃል! ብሎኛል» ይል ነበር። መንፈስ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ አቤት ያለው ልዩነት!

ወንጌል ዛሬም የሰዎችን ሕይወት የሚለውጥ ኃይል ነው (ሮሜ 1፡16)። የወንጌል ስርጭት ስኬታማነት በክርክራችን ወይም በአባባይ «ሽወዳችን» ላይ የሚመረኮዝ ሳይሆን፥ በሕይወታችን በሚሠራው የእግዚአብሔር መንፈስና በምናካፍለው ቃሉ ላይ የሚደገፍ ነው።

## ወንጌል የአብ ዘላለማዊ ዕቅድ ክፍል ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡6–9)

ደኅንነት የተገዛው በልጁ ሲሆን የታቀደው ግን በአብ ነው። ስለ «ቀላል ወንጌል» የሚናገሩ ሰዎች ትክክልም ስሕተትም ናቸው። አዎን፥ የወንጌል መልእክት ያልተማረ ሃይማኖት የለሽ ሰው አውቆት፥ አምኖ እስከሚድን ቀላል ነው። ነገር ግን በጣም የመጠቀ የሥነ መለኮት አዋቂ እንኳ እስከማይዘልቅበት ድረስ በጣም የጠለቀ ነው።

በጣም የረቀቀውን አእምሮ እንኳ የሚቋቋም «የእግዚአብሔር ጥበብ» በወንጌል ውስጥ ይገኛል። ይሁንና፥ ይህ ጥበብ ለጠፉ ብዙኃን ኃጢአተኞች ወይም ላልበሰሉ አማኞች አይደለም። በእግዚአብሔር ቃል እውቀታቸው እያደጉ ላሉ በሳል አማኞች ነው። (በቁጥር 6

«በበሰሉት» የሚለውን ከ 3፡1-4 ጋር አነጻጽር።) ምናልባት ጳውሎስ እዚህ ላይ ምላሽ የሚሰጠው ማራኪ ንግግርና በጥልቀት የማስተማር ክህሎት የነበረውን አጵሎስን (የሐዋ. 18፡24-28) ለሚደግፉ የቤተክርስቲያን ሰዎች ሳይሆን አይቀርም።

እስኪ የዚህን ጥበብ ባሕርያት እንወቅ።

*ይህ ጥበብ የሚመጣው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው* (2፡7)። ይህ ጥበብ እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለፍጥረቱ ስላለው ሰፊ ዘላለማዊ ዕቅድ ለበሳሉ ቅዱስ ሰው ይናገራል። «ከዚች ዓለም (የዘመኑ) ገዢዎች የላቁ ጠበብት የተባሉትም ይህን ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የተካፈለውን አስደናቂ ጥበብ ሊፈላሰፉት ወይም ሊደርሱበት አልቻሉም።

*ይህ ጥበብ የተሰወረ ነበር (2፡7)*። ስለዚህ ነው ምሥጢር የተባለው። በአዲስ ኪዳን ምሥጢር ማለት «የተቀደሰ ሕቡዕ ነገር» ማለት ነው። ይህ ባለፉት ዘመናት የተደበቀና አሁን በእግዚአብሔር ሕዝብ የተገለጠ እውነት ነው። ከወንጌል ጋር የሚዛመዱትን ልዩ ልዩ ምሥጢራት ለማካፈል እግዚአብሔር በልዩ መንገድ የተጠቀመው ጳውሎስን ነበር (ኤፌ. 3 ተመልከት)፤ ነገር ግን «እኛ» የሚለውን የተውላጠ ስም ድግግሞሽ አስተውል። ጳውሎስ ሌሎችን ሐዋርያት ከዚህ ሁኔታ አላገለላቸውም።

*ይህ ጥበብ የእግዚአብሔርን ቅድሚያ ውሳኔ ያካትታል* (2፡7)። ይህ ማለት እግዚአብሔር ዕቅዱን ሠራው፤ በእንቅስቃሴ ላይ አደረገው፤ ከዚያም ፍጻሜ ማግኘቱን ይከታተለዋል ማለት ነው። ታላቁ የቤዛነት ዕቅድ እግዚአብሔር ሰው ያደረገውን ከተመለከተ በኋላ ያመጣው የችኮላ ረፋድ አሳብ አይደለም። ምንም እንኳ ይህ አእምሮአችንን ቢያሽብረውም፥ የመለኮታዊ ምርጫንና የቅድሚያ ውሳኔን (የሚሆነው ሁሉ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነና ሰውም የማይቀይረው መሆኑ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ መቀበል አለብን። ምንም እንኳ ለክፋት ድርጊታቸው ሰዎች በኃላፊነት ቢጠየቁበትም፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትም አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነበር (የሐዋ. 2፡22-23፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18-20)። የውጤታማ የጸሎት ሕይወት ምሥጢራት አንዱ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች በእምነት መጨበጥ ነው (የሐዋ. 4፡23-31)።

*ይህ ጥበብ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መክበር ያስከትላል* (2፡7)። የዚህ «የዘመናት ዕቅድ» ከፍተኛ ገለጣዎች አንዱ በኤፌሶን 1 የሚገኘው ነው። በዚያ ምንባብ ውስጥ ጳውሎስ ሦስት ጊዜ፥ ይህ ሁሉ የተደረገው ለእግዚአብሔር ክብር ነው ይላል (ቁ. 6፥12፥ 14)።

ይህንኑ የእግዚአብሔር ክብር እኛም አንድ ቀን የምንካፈል መሆኑ በጣም የሚያስደንቅ አሳብ ነው! (ዮሐ. 17፡22-24፤ ሮሜ 8፡28-30ን ተመልከት።)

*ይህ ጥበብ ካልዳነው ዓለም የተሰወረ ነው* (2፡8)። የዚህ ዓለም [የዘመኑ] ገዢዎች ብሎ ጳውሎስ የሚጠቅሳቸው እነማን ናቸው? ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት በመንግሥት ሥልጣን የነበሩት ያለጥርጥር እርሱ ማን እንደነበር አላወቁትም (የሐዋ. 3፡17፤ 4፡25-28)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» (ሉቃ. 23፡34) ብሎ ሲጸልይ ይህን እውነት እያስተጋባ ነበር። በእርግጥ አለማወቃቸው ለኃጢአታቸው ይቅርታን ሊያስገኝላቸው አልቻለም፤ ምክንያቱም ተፈላጊውን ማረጋገጫ ጌታ ሰጥቶአቸው ስለነበር ማመን ነበረባቸው።

ነገር ግን ሌላም አማራጭ ነበር። ጳውሎስ ያጣቅስ የነበረው *የዚህን የአሁን ዘመን መንፈሳውያንና አጋንንታዊ ገዢዎችን ሊሆን* ይችላል። (ሮሜ 8፡38፤ ቆላ. 2፡15፤ ኤፌ. 6፡12)። ይህ በተለይ በቁጥር 6 ላይ የበለጠ ትርጉም አለው፤ ምክንያቱም በእርግጥ ጲላጦስ፥ ሄሮድስ እና ሌሎች የዘመኑ ገዢዎች የሚታወቁበት ምንም የተለየ ጥበብ አልነበራቸውም። የዘመኑ ጥበብ ምንጩ ከሰይጣን አለቅነት ሥር የነበሩ የዘመኑ ገዢዎች ናቸው (ዮሐ. 12፡31፤ 14፡30፤ 16፡11)። እርግጥ ነው፥ መንፈሳውያን ገዢዎች የሚሠሩት በሰብአዊ ገዢዎች ውስጥ እና አማካኝነት ነው። በመሆኑም ልዩነቱን እጅግም ልናጠብቀው አያስፈልግ ይሆናል (ዮሐ. 13፡2፥27)።

ነገር ግን ይህ ትርጉም እውነት ከሆነ፥ ጠጣር የእሳቤ አቅጣጫዎችን ይከፍታል። ሰይጣናዊ ኃይላት፥ ሰይጣን ራሱን ጨምሮ የእግዚአብሔርን ታላቅ ዘላለማዊ ዕቅድ አላወቁትም ነበር! የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚወለድና እንደሚሞት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሊያውቁት ችለዋል። የመስቀልን አስፈላጊነት ግን ሊረዱት አልቻሉም ነበር። ምክንያቱም እነዚህ እውነቶች በእግዚአብሔር የተሰወሩ ነበሩ። እንዲያውም እነዚህ እውነቶች አሁን ለአለቆች እና ሥልጣናት እየተገለጠ ያለው በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ነው (ኤፌ. 3፡10)።

ሰይጣን ቀራኒዮ የእግዚአብሔር ታላቅ ሽንፈት መስሎት ነበር፤ ነገር ግን በተገላቢጦሽ ለእግዚአብሔር ታላቅ ድል *ለሰይጣን ደግሞ ሽንፈት* ሆነ! (ቆላ. 2፡15)። ጌታችን ተወልዶ ወደዚህ ዓለም ከመጣ ጊዜ ጀምሮ፥ ሰይጣን ሊገድለው ጥረት አድርጓል። ምክንያቱም ሰይጣን የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ሰፊ ውጤት አልተረዳም ነበር። አጋንንታዊ አለቆች

አውቀውት ቢሆን ኖሮ የክርስቶስን ሞት አያቀነባብሩትም ነበር። (በእርግጥ፥ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አካል ነበር። የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን አልነበረም።)

*በመጨረሻም፥ ይህ ጥበብ ዛሬም በአማኙ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ የሚሆን ነው* (2፡9)። ይህ ቁጥር ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው በቀብር *ሥነ ሥርዓት* ወቅት እና *መንግሥተ ሰማያትን* በተመለከተ ነው። ነገር ግን *መሠረታዊ* ተዛምዶው *ለዛሬው* ክርስቲያን ሕይወት ነው። የሚቀጥለው ቁጥር እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች የሚገልጠው እዚሁ እና አሁኑኑ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል።

ይህ ቁጥር በኢሳይያስ 64፡4 (በማዛመድ) የተወሰደ ጥቅስ ነው። ዓውዱ በቀጥታ በምርኮ ከነበረችውና የእግዚአብሔርን ነፃ ማውጣት ከምትጠባበቀው ከእስራኤል ጋር ያዛምደዋል። የእስራኤል ሕዝብ ስለበደለ ለቅጣት ወደ ምድረ ባቢሎን ተሰድዶ ነበር። እግዚአብሔር ወርዶ ነፃ እንዲያወጣቸው ጮኹ፤ እርሱም ከ 70 ዓመታት የስደት ዘመናቸው በኋላ ጸሎታቸውን መለሰ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ዕቅድ ስለነበረው መፍራት አልነበረባቸውም (ኤር. 29፡11)።

ጳውሎስ ይህን መርህ ለቤተክርስቲያን ተጠቅሟል። ያለንበት ሁኔታ የፈለገውን ይሁን የወደፊታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠበቀ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ገንዘቡ ላደረጋቸው ያሉት ዕቅዶች ፍጹም ድንቅ ስለሆኑ አእምሮአችን ሊያስበው ወይም ሊያስተውለው ይሳነዋል! እግዚአብሔር ይህንን አስቀድሞ ለክብራችን እንዲሆን ወስኖታል (ቁ. 7)። ከምድር እስከ መንግሥተ ሰማይ ድረስ መንገዱ ሁሉ ክብር ነው!

እግዚአብሔርን ለሚወዱት እያንዳንዱ ቀን መልካም ቀን ነው (ሮሜ 8፡28)። መልካም ቀን መስሎ ላይታይ ወይም ላይሰማ ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ዕቅዱን በሚሠራበት ጊዜ የላቀ እንደሚሆንልን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። እርሱን ከመተማመን ስንጎደል፥ ወይም ሳንታዘዘው ስንቀር፥ ለእርሱ ያለን ፍቅር ሲቀዘቅዝ ያኔ ሕይወት የጽልመት ጭጋግ ትላበሳለች። በእግዚአብሔር ጥበብ ከተመላለስን፥ የእርሱን በረከቶች እናጣጥማለን።

ሁለት የወንጌል እውነቶችን አይተናል። እነዚህም ይህ መልእክት የክርስቶስን ሞት ማዕከል ማድረጉን እና የአብ ሰፊ ዕቅድ አካል መሆኑ ናቸው። በቆሮንቶስ የነበሩ አማኞች የደኅንነታቸውን ዋጋ ዘንግተው ነበር፤ ዓይኖቻቸውን ከመስቀሉ ላይ አንሥተው ነበር። በተጨማሪ በጥቃቅን ነገሮች– (የሕፃናት አሻንጉሊት በሚመስሉ) ተይዘው ነበር– ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእነርሱ ለነበረው ዕቅድ

ታላቅነት አድናቆት አጥተው ነው። ወደ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መመለስ አስፈላጊያቸው ነበር። በመሆኑም የጳውሎስ ቀጣዩ ነጥብ ይህን የሚመለከት ይሆናል።

## ወንጌል በመንፈስ አማካኝነት በቃሉ በኩል ተገልጧል (1ኛ ቆሮ. 2፡10–16)።

ደኅንነታችን በመለኮት የተጠቃለሉትን ሦስቱንም አካላት ይመለከታል (1ኛ ጴጥ. 1፡2፤ ኤፌ. 1፡3–14)። የአብ የጸጋ ምርጫ፥ የወልድ የፍቅር መሥዋዕት፥ እና የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ እና የማደስ አገልግሎት ሳይኖር ልትድን አትችልም። «በእግዚአብሔር አምናለሁ» ማለቱ በቂ አይደለም። ምን ዓይነት እግዚአብሔር ነው? የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ «አምላክ እና አባት» (ኤፌ. 1፡3) ካልሆነ በቀር ደኅንነት ሊኖር አይችልም።

ይህ የደኅንነታችን አሀዱ ሥሉሳዊ ገጽታ የደኅንነታችንን አንዳንድ ምሥጢራት የበለጠ እንድንረዳ ያደርገናል። ስለ መለኮታዊ ምርጫ እና ቅድሚያ ውሳኔን በተመለከተ ሲሰሙ ብዙ ሰዎች ግራ ይገባቸዋል (ወይም ይደነግጣሉ)። አብን በተመለከተ ዓለም ከመመሥረቱ አስቀድሞ በክርስቶስ ሲመርጠኝ ድኛለሁ (ኤፌ. 1፡4)፤ ነገር ግን በዳንኩበት ምሽት ስለዚህ የማውቀው ምንም ነገር አልነበረም! ይህ የእግዚአብሔር ድንቅ ዘላለማዊ ዕቅድ ስውሩ ክፍል ነበር።

እግዚአብሔር ወልድን በተመለከተ ደግሞ፥ ስለ እኔ በመስቀል ላይ ሲሞት ድኛለሁ። እርሱ የሞተው ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ነው፤ ሆኖም ግን ዓለም በሙሉ አልዳነም። መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው። መንፈስን በተመለከተ እኔ የዳንኩት ግንቦት 12 ቀን 1945 ዓ.ም. በወጣት ለክርስቶስ ጉባኤ ላይ ቢል ግሬሃም (ያኔ ወጣት ወንጌላዊ ነበሩ) ወንጌልን ሲሰብኩ በሰማሁ ጊዜ ነበር። ያኔ ነበር መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ከልቤ ውስጥ ሲያዋህደው፥ ያመንሁትና እግዚአብሔርም ያዳነኝ።

ጳውሎስ የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ አራት ዐበይት አገልግሎቶች አመልክቶአል።

*መንፈስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል* (2፡12)። ኢየሱስ ክርስቶስን ባመንህበት በዚያች ቅጽበት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ አካልህ ውስጥ በመግባት ቤተ መቅደሱ አድርጎታል (1ኛ ቆሮ. 6፡19–20)። እርሱም ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ አጠመቀህ (አንድ አደረገህ) (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። አትሞሃል (ኤፌ. 1፡13–14) ደግሞም ከአንተ ጋር ይኖራል (ዮሐ. 14፡16)። እርሱ ለአንተ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

*መንፈስ ቅዱስ የአርነት መንፈስ ነው* (2ኛ ቆሮ. 3:17)። ከዚህ ዓለም ተጠርተን ስለተለየን እና የዓለም ንብረት መሆናችን ስላከተመ (ዮሐ. 17:14÷16) «የዓለምን መንፈስ» አልተቀበልንም። ከሰይጣን ሥልጣን እና ከእርሱ ሥርዓተ ዓለም ሥር መሆናችን አብቅቷል።

«እንደገና ለፍርሃት የባርነት መንፈስን አልተቀበልንም» (ሮሜ 8:15)። መንፈስ ቅዱስ በፍቅር ያገለግለናል እናም አብን ለእኛ እውን ያደርግልናል። ይህ ከ 2ኛ ጢሞቴዎስ 1:7 ጋር ይያያዛል– «እግዚአብሔር የኃይል እና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና» (2ኛ ጢሞ. 1:7)። መንፈስ በውስጣችን ስለሚኖር ምን ዓይነት መንፈሳዊ ሀብት ነው የያዝነው!

*መንፈስ ይመረምራል* (2:10–11)። በአንተ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ እኔ ላውቅ አልችልም፤ ነገር ግን በአንተ ውስጥ ያለው የሰው (ሰብአዊ) መንፈስ ያውቃል። በሆነ ሁኔታ ወደ እግዚአብሔር ማንነት ውስጥ እስካልገባሁ ድረስ «የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች» ማወቅ አልችልም። ይህን እኔ ማድረግ አልችልም እግዚአብሔር ግን በመንፈሱ ወደ ስብዕናዬ ገብቷል። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር ሕይወት ተካፋይ ይሆናል።

*መንፈስ ቅዱስ* «የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች» ያውቃል፤ ደግሞም ለእኛ ይገልጽልናል። ቁጥር 10 ላይ «የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገሮች» የሚለው «እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ያዘጋጀው» (ቁ. 9) በሚል የተገለጸ ሌላኛው አባባል ነው። እግዚአብሔር በእኛ ያቀደውን የጸጋውን በረከት ሁሉ *ዛሬውኑ* እንድናውቅ ይፈልጋል።

*መንፈስ ያስተምራል* (2:13)። ኢየሱስ መንፈስ እንደሚያስተምረን (ዮሐ. 14:26) እና ወደ እውነት እንደሚመራን (16:13) ተስፋ ሰጥቶአል። ነገር ግን እዚህ ላይ ያለውን ቅደም ተከተል በጥንቃቄ ልብ ልንል ይገባል። መንፈስ ጳውሎስን ከቃሉ አስተማረው፤ ከዚያም ጳውሎስ አማኞችን አስተማራቸው። የእግዚአብሔር እውነት የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው። እነዚህ መንፈሳዊ እውነቶች ደግሞ ልዩ በሆኑ *ቃላት* ውስጥ እንደተሰጡ ማስተዋሉ በጣም ተፈላጊ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ካረፈባቸው አሳቦች በላይም የእግዚአብሔር መንፈስ ያረፈባቸውን *ቃላትም* እናገኛለን። «የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና» (ዮሐ. 17:8)።

አራቱ ልጆቻችን እያንዳንዳቸው የተለያዩ ሙያዎች አሉአቸው። መጋቢ፥ ነርስ፥ ኤሌክትሮኒክ ዲዛይነር እና በአንድ የንግድ ድርጅት ውስጥ ጸሐፊ። እያንዳንዳቸው ስኬታማ ለመሆን የተለዩ ቃላትን መማር ነበረባቸው። በደንብ የምረዳው መጋቢውን ብቻ ነው።

ስኬታማ ክርስቲያን የመንፈስን ቃላት በመማር ይጠቀምባቸዋል። መጽደቅን፥ መቀደስን፥ ልጅ መሆንን፥ ሞገስ ማግኘትን፥ መመረጥን፥ በኃይል መሞላትን እና የመሳሰሉትን ትርጓሜአቸውን ያውቃል። የእግዚአብሔርን ቃላት በማወቅ የእግዚአብሔርን ቃል እና ለሕይወታችን ያለውን ፈቃዱን ወደ ማወቅ እንሸጋገራለን። የምሕንድስና ተማሪ የኬሚስትሪ፥ የፊዚክስ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ቴክኒካዊ ቃላትን የሚያውቅ ከሆነ፥ በመንፈስ የተማሩ ክርስቲያኖች የክርስቲያናዊ እውነትን ቃላት ለመያዝ ለምን ይከብዳቸዋል?

እንዲህም ሆኖ የቤተ ክርስቲያን አባላት፥ «ዶክትሪን አታስተምር። የሚያበረታቱንን ልብ አሟሟቂ ስብከቶችን ብቻ ስጠን!» ሲሉ እሰማለሁ። በምን ላይ የተመሠረቱ ስብከቶችን? በዶክትሪን ላይ ካልተመሠረቱ ምንም ፋይዳ አይሰጡም! «ዶክትሪን እኮ ድንዛዜ ነው» በማለት ሰዎች ያማርራሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ ሆኖ ከቀረበ ይህ አይከሰትም። ለእኔ ዶክትሪን አስደሳች ነው! መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት መቻል እና «የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች» (1ኛ ቆሮ. 2:10) መንፈስ እንዲያስተምረን መፍቀድ ምንኛ አርኪ ነው!

መንፈስ አማኙን የሚያስተምረው እንዴት ነው? «መንፈሳዊ ነገሮችን ከመንፈሳዊው ጋር» ያነጻጽራል። ምን እንዳስተማረን ያስታውሰናል (ዮሐ. 14:26)፥ ያንን እውነት ከአዲስ ነገር ጋር ያነጻጽራል፤ ከዚያም ወደ አዲስ እውነት እና የአሮጌው እውነት አዲስ አጠቃቀም ይመራናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ፊት ቁጭ ብሎ መንፈስ የእግዚአብሔርን እውነት እንዲገልጥ ማድረግ ምንኛ ደስ ይላል? ችግሩ ብዙ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለውን ፀጥተኛ ጥሞና ለማድረግ በጣም ሥራ ይበዛባቸዋል። እንዴት ያለ ብልጽግና ነው የሚያጡት!

መንፈስ ቅዱስ «ከመዝገቡ አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል» (ማቴ. 13:52)። አዲሱ ሁልጊዜ የሚወጣው ከአሮጌው ሲሆን አሮጌውን የበለጠ እንድንረዳ ያግዘናል። አንደኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከሌላው ጋር በምናነጻጽርበት ጊዜ እግዚአብሔር አሮጌዎቹን ጠልቀን የምንገባበትን አዲስ ብልጭታ ይሰጠናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱን የመሠረተው በብሉይ ኪዳን ላይ ነበር፤ ሆኖም ግን ያስተማረው ነገር በጣም ወቅታዊና አስደሳች በመሆኑ ሕዝቡ በትምህርቱ በጣም ተደነቁ።

በየዕለቱ ቃል ለማንበብና ጥሞና ለማድረግ ጊዜ እንድትመድብ ላሳስብህ እወዳለሁ። በንባብህ የማይዛባ መርሐ ግብርን በመከተል ለመጸለይ፥ ለማሰብ እና ጥሞና ለማድረግ ጊዜ ውሰድ። የእግዚአብሔር

መንፈስ ቃሉን እንዲመረምርና እንዲያስተምርህ ፍቀድለት። መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪን ጥናትና ተዛምዶ ሕይወትህን ሊለውጥ ይችላል።

*መንፈስ አማኙን ያጎለምሰዋል* (2:14–16)። እዚህ ላይ የቀረበው ንጽጽር በዳነ ሰው («መንፈሳዊ» በተባለው ምክንያቱም መንፈስ በውስጡ ስለሚኖር) ና ባልዳነ ሰው («ተፈጥሮአዊ» በተባለው– ምክንያቱም መንፈስ በውስጡ ስለሌለ) መካከል ነው። በ 3:1–4 ላይ፥ ጳውሎስ ሦስተኛ ዓይነት ሰውን ያስተዋውቃል፤ «ሥጋዊ ሰው»። ይህ ያላደገ ክርስቲያን ነው፤ ይህ ሰው በሕፃንነት ደረጃ የሚኖር ነው ምክንያቱም ቃሉን ስለማይመገብ አያድግም።

በአንድ ወቅት፥ እያንዳንዱ ክርስቲያን የተፈጥሮ ነገሮችን ብቻ የሚያደርግ «ተፈጥሮአዊ ሰው» ነበር። አዳኙን ባመንን ጊዜ፥ መንፈስ ሲገባብን ወደ መንፈሳዊነት ተሸጋገርን። ከዚህም የተነሣ በመንፈስ ዓለም መኖርን ቻልን። *ከዚያ በኋላ ማደግ ነበረብን!* ያልዳነ ሰው ስለማያምናቸው ና ስለማይረዳቸው የመንፈስን ነገሮች ሊቀበል አይችልም። ነገር ግን ክርስቲያን ዕለት ተዕለት የመንፈስን ነገሮች ስለሚቀበል፥ ያድጋል ይጎለምሳልም።

ከብስለት ምልክቶች አንዱ የመመርመር ብቃት ነው– ይህም ከገጸዊው ሕይወት ወደ ውስጥ በመዝለቅ ነገሮችን ባሉበት ደረጃ በትክክል የማየት ችሎታ ነው። ያልዳኑ ሰዎች የሚኳዙት በማየት ስለሆነ ምንም የሚታይ ነገር ያጣሉ። በመንፈሳዊ ነገር የታወሩ ናቸው። በሳሉ ክርስቲያን በመንፈሳዊ እውቀቱ ያድጋል እናም (በመንፈስ እርዳታ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ና አሳብ በበለጠ የማወቅን ችሎታ ያዳብራል። ቆሮንቶሳውያን ይህ እውቀት ይጎድላቸው ነበር። በመንፈሳዊ ነገር ምንም እውቀት አልነበራቸውም።

«የክርስቶስ ልብ አለን» ማለት የማንሳሳት ና በሌሎች ሰዎች ሕይወት የእግዚአብሔርን ቦታ እንተካለን ማለት አይደለም። ማንም እግዚአብሔርን አያዝዝም! (ጳውሎስ ኢሳይያስ 40፡13ን ጠቅሷል። ሮሜ 11፡33–36 በተጨማሪ ተመልከት።) «የክርስቶስ ልብ አለን» ማለት ሕይወትን ከአዳኙ እይታ አቅጣጫ መመልከት፥ የእርሱን ፍላጎቶችና እሴቶች በልብ ማኖር ማለት ነው። እንደ ዓለም ሳይሆን እግዚአብሔር እንደሚያስብ ማሰብ ማለት ነው።

ያልዳነው ሰው ክርስቲያኑን ሊረዳ አይችልም፤ የሚኖሩት በሁለት በተለያዩ ዓለማት ነው። ነገር ግን ክርስቲያኑ ያልዳነውን ሰው ይረዳዋል። ቁጥር 15 ያልዳኑ ሰዎች በአማኙ ሕይወት ውስጥ ነቀፋን አያዩም ማለትን አያመለክትም (ብዙ ጊዜ ያዩታል)። ነገር ግን ያልዳነው

ሰው የክርስቲያኑ ሕይወት ምን እንደሆነ ወደ ሙሉ መረዳት ሊዘልቅ አይችልም ማለት ነው። እኔ አዲሱን የአሜሪካን ስታንዳርድ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እወዳለሁ፡- «ነገር ግን መንፈሳዊ የሆነ ሰው የሁሉንም ነገር ዋጋ ይተምናል፥ እርሱ ራሱ ግን በማንም አይታመንም»። «በማንም» የሚለው ቃል ሌሎች ክርስቲያኖችንም የሚጠቀልል ነው። በእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ላይ መንፈሳዊ አምባገነን እንዳንሆን በጣም መጠንቀቅ አለብን (2ኛ ቆሮ. 1፡24)።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመንፈስ ተአምራዊ ስጦታዎች ስለተሸፈኑ መሠረታዊውን የመንፈስ አገልግሎት ችላ ይሉት ነበር። በመንፈስ ላይ በነበራቸው አጽንኦት ምክንያትም አብን ና ወልድን ችላ ይሉአቸው ነበር።

ሁሉንም መጥነው የሚይዙ የተባረኩ ናቸው! ደግሞም «የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ» የሚረዱ ና የሚያካፍሉት የተባረኩ ናቸው (የሐዋ. 20፡27)።

# ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን. . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 3*

ብሪታኒያዊው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ዶክተር ጂ. ካምቤል ሞርጋን አራት ወንድ ልጆች ነበሯቸው፤ አራቱም ወንጌል አገልጋዮች ሆኑ። አንዱ ሰው ከልጅ ልጆቻቸው አንዱን እርሱም የወንጌል አገልጋይ ይሆን እንደሆነ ሲጠይቀው፥ «የለም፥ እኔ ለኑሮዬ ለመሥራት ነው ዕቅዴ» በማለት መለሰለት።

አንድ መጋቢ ማድረግ የሚጠበቅበት ምንድን ነው? «የወንጌል አገልግሎት ሥራ በእርግጥ ምንድን ነው»? ይህን ካላወቅን የወንጌል አገልጋዩን ሥራ ከቶውንም መገምገም አንችልም። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ የበለጠ በርካታ ችግሮችን የሚፈጥር ሌላ ጉዳይ ምናልባት አይኖርም፥ መጋቢውና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእርግጥ ሥራቸውን እየሠሩ እንዳሉ የምናውቀው እንዴት ነው?

ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ሦስት የቤተ ክርስቲያን ምስሎችን ይሥላል። እነዚህኑ ምስሎች በመጠቀም የወንጌል አገልግሎት ምን መፈጸም እንደሚገባው አመልክቶአል። ቤተ ክርስቲያን *ቤተሰብ* ናት እናም ዓላማዋ *እድገት* ነው (3:1-4)። ቤተ ክርስቲያን *ማሣ* ናት እናም ዓላማዋ *ብዛት* ነው (3:5-9)። ቤተ ክርስቲያን *ቤተ መቅደስ* ናት እናም ዓላማዋ *ጥራት* ነው (3:9-23)።

## ቤተሰብ –በብስለት ማደግ (1ኛ ቆሮ. 3:1-4)

ጳውሎስ በዓለም ላይ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ቀደም ሲል ገልጾአል– ተፈጥሮአዊ (ያልዳነ) እና መንፈሳዊ (የዳነ)። አሁን ደግሞ ሁለት ዓይነት የዳኑ ሰዎች እንዳሉ ያብራራል – በሳልና ጨቅላ (ሥጋዊ)። ክርስቲያን የሚያድገው መንፈስ ቃሉን በመመገብ እንዲያስተምረው ሲፈቅድ ነው። ጨቅላው ክርስቲያን የሚኖረው ለሥጋዊ ነገሮች ስለሆነ ለመንፈሳዊ ነገሮች ያለው ፍላጎት አነስተኛ ነው። በእርግጥ አንዳንድ ክርስቲያኖች የዳኑት ቅርብ ጊዜ ስለሆነ ጨቅላ ናቸው። ነገር ግን ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ስለ እነዚህ አይደለም።

ጳውሎስ ይህንን ቤተሰብ ወደ ሕልውና ያመጣ «መንፈሳዊ አባት» ነው (4:15)። በቆሮንቶስ ባገለገለባቸው 18 ወራት፥ ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጆቹን በመመገብና በእምነት እንዲያድጉ በመርዳት ጥሮአል። በሰብአዊ ቤተሰብ ውስጥ ያለ አዲስ ሕፃን እንዲያድግ እና እንዲጠነከር ሁሉም ሰው እንደሚያግዝ ሁሉ –በእግዚአብሔር ቤተሰብ መንፈሳዊ ብስለት እንዲመጣ ማበረታታት ይገባናል።

የብስለት ምልክቶች ምንድን ናቸው? አንደኛው መንገድ፥ በሳል ሰውን በሚመገበው ምግብ ማወቅ ትችላለህ። ይህን ምዕራፍ በምንጽፍበት ጊዜ ወንድ የልጅ ልጃችንና ሴት የልጅ ልጃችን ሲያድጉ እየተከታተልን ነበር። ቤኪን ገና እናቷ እያጠገበቻት ናት፥ ዮናታን ግን አሁን በጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጦ ትንሿን መጠጫውን እና የመመገቢያ መሣሪያዎቹን ይዞ በመውተርተር ይሞካከራል። ልጆች እያደጉ በሄዱ ቁጥር፥ የተለያዩ ምግቦች መመገብ ይማራሉ። ከወተት ወደ ሥጋ (የጳውሎስን ቃላት ልጠቀምና) ይሸጋገራሉ።

ልዩነቱ ምንድን ነው? ተለምዶአዊ ምላሽ «ወተት» በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀላል ነገሮች ሲወክል፥ «ሥጋ» ደግሞ ጠንካራ ዶክትሪንን ይወክላል። እኔ ግን በዚህ ተለምዶአዊ አገላለጽ አልስማማም፤ ማስረጃዬ ደግሞ ዕብራውያን 5:10–14 ነው። ምንባቡ «ወተት» ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር እያለ ያደረጋቸውን እንደሚወክል፥ «ሥጋ» ደግሞ አሁን በመንግሥተ ሰማይ ሆኖ የሚያደርገውን እንደሚወክል የሚያስተምር ይመስላል። የዕብራውያን ጸሐፊ የአሁኑን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማያዊ ክህነት ለማስተማር የፈለገ ሲሆን አንባቢያኑ ግን በጣም ጨቅላ ከመሆናቸው የተነሣ ሊያደርገው አልቻለም (ዕብ. 6:1–4ን ተመልከት)።

የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ምግባችን ነው – ወተት (1ኛ ጴጥ. 2:2)፥ እንጀራ (ማቴ. 4:4)፥ ሥጋ (ዕብ. 5:11–14) እና ማርም ጭምር [መዝ. (118):103] ነው። የውጪኛው ሰው በሰውነቱ ጤናማ እንዲሆን የተመጣጠነ ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ የውስጠኛውም ሰው የተመጣጠነ መንፈሳዊ ምግብ ያስፈልገዋል። ሕፃን በወተት ይጀምራል፤ ነገር ግን ባደገና ጥርሶቹም በጎለበቱ መጠን ጠንካራ ምግብ ያስፈልገዋል።

የአንድ አማኝን መንፈሳዊ ብስለት ወይም ጨቅላነት ለማወቅ አስቸጋሪ አይደለም፤ የሚጠይቀው ምን ዓይነት «ምግብ» እንደሚወድ ማወቅን ነው። ጨቅላው አማኝ ክርስቶስ አሁን በሰማይ ስላለው አገልግሎት የሚያውቀው ጥቂት ነው። በምድር ስለነበረው የጌታችን ሕይወት እና አገልግሎት ሐቆችን ያውቃል፤ ነገር ግን አሁን በሰማይ

ስላለው አገልግሎት *ጭብጦችን* አያውቅም። የሚኖረው «በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች» እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪኖች አይደለም። የ 1ኛ ቆሮ. 2፥6-7 አስተውሎት የለውም።

በዝውውር አገልግሎቴ በመቶዎች ለሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት እና ኮንፈረንሶች ሰብኬአለሁ። በእነዚህ ጊዜያት ለመዝናናት ሳይሆን አብርሆትን ለማግኘት ና ለመታነጽ ፍላጎት ለነበራቸው ምእመናን ምስጋናዬ ሁሌም ከፍ ያለ ነበር። ለጠፉት ወንጌልን መስበካችን አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን ለዳኑትም ደግሞ ወንጌልን *መተርጎማችን* እኩል አስፈላጊ ነው። አዲስ ኪዳን እንዳለ የወንጌል ትርጉም ና ተዛምዶ ነው። ለምሳሌ ጳውሎስ የሮሜን መልእክት የጻፈው ሮማውያን እንዴት መዳን እንዳለባቸው ለመንገር አልነበረም- ምክንያቱም እነርሱ የዳኑ ቅዱሳን ነበሩ። ደኅንነታቸው በመሠረቱ ምን እንደሚያካትት ለመግለጽ ጻፈላቸው። ይህ «የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገሮች» በዕለታዊ ኑሮም እንዴት እንደሚተገበሩ ማብራሪያ ነበር።

ብስለትን ማወቂያ ሌላም መንገድ አለ፤ በሳል ክርስቲያን ፍቅርን ይለማመዳል፤ ከሌሎችም ጋር መግባባትን ይፈልጋል። ጨቅላዎች ግን አለመስማማትና ኩርፊያ ይቀናቸዋል፤ በተራ ነገርም ስሜታዊነት ያጠቃቸዋል። ጨቅላዎች ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ከጀግኖች፥ የስፖርት ጀግኖችም ይሁኑ የፊልም ጀግኖች፥ ጋር ማዛመድ ያምራቸዋል። በቆሮንቶስ የነበሩ «ጨቅላዎችም»፥ ታላቁ ሰባኪ የትኛው ነው- ጳውሎስ፥አጵሎስ፥ ወይስ ጴጥሮስ በማለት ይፋተጉ ነበር። በመጫወቻ ስፍራ ያሉ ሕፃናት ሥራ ይመስል ነበር – «አባቴ አባትህን ያሸንፋል! አባቴ ከአባትህ ይበልጥ ሀብታም ነው!»

መንፈሳዊ እውቀት የሌላቸው ጨቅላ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን የመሪነትን ስፍራ ሲቆናጠጡ አደጋ ይከሰታል። ከአንድ በላይ የሆኑ ልባቸው የተሰበረባቸው መጋቢዎች፥ ንግግራቸው ተራራ ኑሮአቸው (ሕይወታቸው) ግን ተራ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ምን እናድርጋቸው! ሲሉ በጽሑፍ ወይም በስልክ ይጠይቃሉ። (እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንዴ ያልበሰለ መጋቢ ሲያጋጥም፥ ምን እናድርግ ብለው የሚጠይቁት *ሽማግሌዎች [የቤተ ክርስቲያን ሹማምንት]* ናቸው ማለት አለብኝ!)

የመጋቢ ሥራ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ነገር እንድታድግ በጌታም እንድትጠነክር መርዳት ነው። ይህ ደግሞ የሚሆነው በማያቋርጥ፥ በተመጣጠነ የቃሉ አገልግሎት ነው። ኤፌሶን 4፥1-16 ይህ ጉዳይ እንዴት እንደሚከናወን ያብራራል። ይኸውም እያንዳንዱ የአካል ክፍል የራሱን ድርሻ ማበርከት አስፈላጊው ስለመሆኑ ነው።

እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለሕዝቡ ያድላል፤ ከዚያም እነዚህን በስጦታ የበለጸጉ ሰዎች ቅዱሳንን እንዲያንጹ ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ይሰጣል። አማኞች በሚያድጉበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ያንጹአታል።

ጳውሎስ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች በ 1ኛ ቆሮ. 12–14 ብዙ ይናገራል፤ ይሁን እንጂ የሚከተለው አሁን እዚሁ መነገር ይገባዋል። የበሰለ ክርስቲያን ስጦታዎቹን የማነጫ መሣሪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል፤ ጨቅላው አማኝ ግን ስጦታዎቹን እንደ መጫወቻ አሻንጉሊቶች ወይም እንደ መመጻደቂያ ሽልማት አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። አብዛኛዎቹ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በስጦታዎቻቸው «መመጻደቅ» ይወድዱ ነበር፤ ነገር ግን አንዳቸው ሌላውን ለማገልገል ና ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ፍላጎት አልነበራቸውም።

የወንጌል አገልግሎት ዓላማው ምንድን ነው? ልጆቹ በእምነት እንዲጠነክሩ ና የበለጠ ኢየሱስን እንዲመስሉ፥ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ማፍቀር፥ መመገብ፥ እና መግራትን ያካትታል።

## ማሣው –ብዛት (1ኛ ቆሮ. 3፡5–9)

ጳውሎስ የእርሻ ምሳሌዎችን ይወድድ ነበር እናም ብዙ ጊዜ በደብዳቤዎቹ ይጠቀምባቸዋል። «እናንተ የእግዚአብሔር እርሻዎች ናችሁ» ማለት፥ «እናንተ የእግዚአብሔር የተዘጋጀ ማሣ ናችሁ፥ የእግዚአብሔር የአትክልት ስፍራ ናችሁ» ማለት ነው። በዘሪው ምሳሌ ላይ፥ ኢየሱስ የሰውን ልብ ከመሬት፥ ዘሩን ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አነጻጽሮታል (ማቴ. 13፡1–9፥ 18–23)። ጳውሎስ ይህን *ግላዊ* ምሳሌ ወስዶ *የጋራ* አደረገው፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ ማፍራት የሚገባት ማሣ ናት። የወንጌል አገልግሎት *ሥራ* መሬቱን ማዘጋጀት፥ ዘርን መዝራት፥ ቡቃያውን ውኃ ማጠጣት፥ እና ፍሬውን መሰብሰብ ነው።

ይህ የ «ማሣነት» የቤተ ክርስቲያን ምስል ለቆሮንቶስ ልዩ ችግር ተግባራዊ የሚሆነው እንዴት ነው? በመጀመሪያ ደረጃ አጽንኦቱ መደረግ ያለበት በሠራተኞቹ ላይ ሳይሆን *በእግዚአብሔር* ላይ ነው። ጳውሎስ ና አጵሎስ የተመደበላቸውን *ሥራ* የሚሠሩ አገልጋዮች ብቻ ነበሩ። ለልፋታቸው ሕይወትን የሰጠው እግዚአብሔር ነበር። የአማኞቹ እምነትም እንኳ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ቁ. 5)። አትኩሮትን በአገልጋዮቹ ላይ ማድረግ ስሕተት ነበር። ይልቅ የበረከት ሁሉ ምንጭ ወደሆነው ወደ መከሩ ጌታ ተመልከት።

በዚህ አንቀጽ ብዛት ወይም እድገት ላይ የተደረገውን አጽንኦት ልብ በል። ለምን ሰባኪያንን ወይም ስታቲስቲኮችን እናወዳድራለን? የእድገቱ መንስኤ እግዚአብሔር ነው፤ ለዚህ ማንም ክብርን ሊቀበል አይችልም። በተጨማሪም፥ ማንም ሁሉንም ተፈላጊ ሥራዎች መሥራት አይችልም። ጳውሎስ ዘሩን ዘራው፥ አጵሎስ ውኃ አጠጣው፥ ነገር ግን ያሳደገው እግዚአብሔር ብቻ ነበር (ቁ. 6)።

ከዚህ ምሳሌ ሦስት ዐበይት ትምህርቶች ይመነጫሉ።

*የመጀመሪያው፥ የወንጌል አገልግሎት ፈርጀ ብዙነት።* አንዱ ሠራተኛ መሬቱን ያርሳል፥ ሌላኛው ዘሩን ይዘራል፥ ሦስተኛው ዘሩን ውኃ ያጠጣዋል። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፥ ቡቃያው ያድጋል፥ ፍሬው ይደርሳል፥ ሌሎች ሠራተኞች ደግሞ መከሩን በመሰብሰብ ይደሰቱበታል። ይህ በፈርጀ ብዙነት ላይ የተደረገው አጽንኦት ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ብዙ ብልቶች ካሉት አካል ጋር በሚያነጻጽርበት ጊዜ ይነሣል።

*ሁለተኛ፥ የዓላማ አንድነት።* አንድ ሰው ምንም ዓይነት ሥራ ለጌታ ይሥራ፥ የመከሩ ተካፋይ ነው። «የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው» (ቁ.8)። ጳውሎስ፥ አጵሎስና ጴጥሮስ እርስ በርስ አይወዳደሩም ነበር። በዚህ ፈንታ እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ሥር የተመደበለትን ሥራ ይሠራ ነበር። ምንም እንኳ የአገልግሎት ፈርጀ ብዙነት ቢኖርም፥ የዓላማ አንድነት አለ፤ ደግሞም የመንፈስ አንድነትም ሊኖር ይገባል።

*ሦስተኛ፥ የትሕትና አስፈላጊነት።* መከሩ እንዲደርስ የሚያደርጉት ሰብአዊ ሠራተኞች ሳይሆኑ የመከሩ ጌታ ነው። «እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር. . . የሚያሳድግ እግዚአብሔር» (ቁ. 6–7)። እግዚአብሔር ሰዎች በምድር የእርሱ አገልጋዮች እንዲሆኑ መወሰኑ የተረጋገጠ ነው፤ ሆኖም ግን የእነርሱ ጥረት ያለ እግዚአብሔር በረከት ውድቀት ነው። ቆሮንቶሳውያን በቤተ ክርስቲያናቸው ይኮሩ ነበር፤ በጉባኤው ያሉ ልዩ ልዩ ቡድኖች በመሪዎቻቸው ይመኩ ነበር። ይህ በትዕቢት «የመነፋት» ዝንባሌ እግዚአብሔር ክብርን እንዳይቀዳጅ ይከላከል ስለነበር ቤተ ክርስቲያንን ከፋፍሎአታል።

ኢየሱስም በዮሐንስ 4፡34–38 በተዘገበው ይኸንኑ አሳብ ተናግሮአል። ዘሪና መከር ሰብሳቢ አንድ ላይ የሚሠሩ ብቻ ሳይሆኑ፥ ነገር ግን በአንድነት የሚደሰቱ እና የየድርሻቸውን ዋጋ የሚቀበሉ ናቸው። የብቻ አገልግሎት የሚባል ነገር የለም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ሠራተኛ በሌሎቹ ሥራ ውስጥ መግባቱ ስለማይቀር ነው። እኔ ፍጹም እንግዶች የሆኑ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመምራት ዕድል

ገጥሞኝ ያውቃል፤ ነገር ግን ሌሎች ዘሩን ዘርተው በፍቅራቸውና በጸሎታቸው አጠጥተውታል።

«እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል» (1ኛ ቆሮ. 3፡8)። ሰዎች አላስፈላጊ አድርገው የሚቆጥሩትን አገልግሎታችንን እግዚአብሔር ታላቅ አድርጎ ይቆጥረዋል። ዋጋችን የሰዎች ውዳሴ ሳይሆን የመከሩ ጌታ «ጎሽታ» ሊሆን ይገባዋል።

እግዚአብሔር ማሣው እንዲያድግ ይፈልጋል። እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ፍሬ (ገላ. 5፡22–23)፥ ቅድስና (ሮሜ 6፡22)፥ ድሆችን መርዳት (ሮሜ 15፡26)፥ በጎ ሥራ (ቆላ. 1፡10)፥ ለእግዚአብሔር ምስጋና መሠዋት (ዕብ. 13፡15)፥ እና ነፍሳትን ማፍራት (ሮሜ 1፡13) እንዲኖራት እግዚአብሔር ይፈልጋል። ከመንፈሳዊ እድገት ጋር አብሮ የሚቆጠር አኃዛዊ እድገት መኖር አለበት። *አንድ ፍሬ በውስጡ ለብዙ ፍሬዎች የሚሆን ዘር ይይዛል።* የአገልግሎታችን ፍሬ እውነተኛ ከሆነ፥ በመጨረሻ ለእግዚአብሔር ክብር «ብዙ ፍሬ...» ያፈራል (ዮሐ. 15፡1–8)።

በአገልግሎት የተሰማሩ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን «መሬት» የማያቋርጥ ክብካቤ ማድረግ አለባቸው። አንድን መከር ለማግኘት በርትቶ መሥራትን ይጠይቃል። ሰነፉ ሰባኪ ወይም የሰንበት አስተማሪ ሰሎሞን በምሳሌ 24፡30–34 የጻፈውን ታካች ገበሬ ይመስላል። ሰይጣን አለመስማማትን፥ ውሸትን፥ እና ኃጢአትን ለመዝራት በመጣደፍ ላይ ነው፤ በመሆኑም መሬቱን በማዘጋጀት ና መልካሙን የእግዚአብሔር ቃል በመዝራት ሥራ የሚበዛብን መሆን አለብን።

## ቤተ መቅደሱ– ጥራት (1ኛ ቆሮ. 3፡9–23)

የዚህ ምንባብ ተለምዶአዊ ገለጻ የክርስቲያን ሕይወትን ስለሚያንጽ ነገር ማውሳቱ ነው። ሁላችንም በክርስቶስ ላይ እናንጻለን፥ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች መልካም የሆኑ ቁሳቁሶችን፥ ሌሎች ደግሞ መናኛ ቁሳቁሶችን ለእነጻው ይጠቀማሉ። የምትጠቀመው ቁሳቁስ የምታገኘውን ዋጋ ይወስናል።

ይህ የዚህ ምንባብ ትክክለኛው *ተዛምዶ* ቢሆንም፥ መሠረታዊው *ትርጓሜ* ግን አይደለም። ጳውሎስ ያወሳ የነበረው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነችውን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስለማነጽ ነው። (ከ 6፡19–20 ባለው እንደተመለከተው እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው፤ እዚህ ላይ ግን የሚታየው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው። በኤፌ. 2፡19–22፥ እንዳለች ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ጋር ተነጻጽራለች።) ጳውሎስ የሚያመለክተው አንድ ቀን

እግዚአብሔር ሥራችንን ከአጥቢያ ጉባኤ ጋር በማገናዘብ እንደሚፈርድ ነው። «የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል» (1ኛ ቆር. 3፡13)።

እግዚአብሔር በጥራት እንድናንጽ ተቆርቋሪነቱን ይገልጻል። ቤተ ክርስቲያን የሰባኪው ወይም የምእመናኑ አይደለችም። እርሷ የእግዚአብሔር ናት። «እናንተ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ» (ቁ.9)። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ማነጽ ከፈለግን፥ የተወሰኑ ሁኔታዎችን ማሟላት አለብን።

*በመጀመሪያ፥ በትክክለኛው መሠረት ላይ ማነጽ አለብን (3፡10–11)።* ያ መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ የተሰቀለውን ክርስቶስን ብቻ ለመስበክ ወሰነ (2፡1–2)። ዘለቄታ ያለውን ብቸኛ መሠረት ጣለ። ከ30 ዓመታት በሚያልፈው አገልግሎቴ፥ «አብያተ ክርስቲያናት» በታወቀ ሰባኪ፥ ወይም ልዩ በሆነ ዘዴ፥ ወይም ትክክል ነው ብለው ዓይናቸውን በጣሉበት ዶክትሪን ላይ ለማነጽ ሲጥሩ ተመልክቼአለሁ። ነገር ግን እነዚህ አገልግሎቶች አልዘለቁም። ቆሮንቶሳውያን ክርስቶስን ማክበር ሲገባቸው በግለሰቦች– በጳውሎስ፥ በጴጥሮስና በአጵሎስ ላይ ዓይናቸውን ጣሉ።

መሠረቱ የሚጣለው የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማወጅ ነው። መሠረት የሕንፃው በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው፥ ምክንያቱም ከላይ ለሚታነጸው አካል መጠኑን፥ ቅርጹንና ጥንካሬውን የሚወስነው እርሱ ስለሆነ ነው። አንድ አገልግሎት ለጊዜው የተሳካ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን በክርስቶስ ላይ ካልተመሠረተ በመጨረሻ ይፍረከረክና ይጠፋል።

አሁን እያሰብሁ ያለሁት ስለ አንድ መጋቢ ነው። ይህ ሰው ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ሲል ከመጽሐፍ ቅዱስ አገኘሁ ያለውን (እውነቱ ግን ከሌሎች መጻሕፍት ያነበበውን ነው) «አንድ ታላቅ እውነት» ለማራመድ ወሰነ። ለዚህ ላገኘው «እውነት የተሰጡትን» የያዘ አንድ ቡድን ከቤተ ክርስቲያን ገምሶ ይዞ ወጣ። ነገር ግን ይህ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም መጽናት አልቻለም። አሁን ቡድኑ ብትንትኑ ስለ ወጣ መጋቢው ለዓላማው አማኝ የሆኑትን ለመሰብሰብ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይንከራተታል። የገነባው በተሳሳተ መሠረት ላይ ነበረ!

| ብር፥ ወርቅ፥ የከበሩ ድንጋዮች | እንጨት፥ ሣር፥ አገዳ |
|---|---|
| ዘላቂ | አላፊ፥ ጊዜያዊ |
| ውብ | ተራ፥ እንዲያውም አስቀያሚ |
| የከበረ/ውድ | ርካሽ |
| ለማግኘት ከባድ | በቀላሉ የሚገኝ |

*ሁለተኛ፥ በትክክለኞቹ ቁሳቁሶች ማነጽ አለብን (3፡12-17)።* ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው ጳውሎስ ሁለት ዓይነት ተቃራኒ ቁሳቁሶችን ይገልጻል።

ጳውሎስ በእነዚህ የቁሳቁሶች አመራረጡ ለማመልከት የፈለገው ምንድን ነው? ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤት መቅደስ ለመሆን የሚገጣጠሙ «ሕያዋን ድንጋዮች» ስለሆኑ የሚናገረው ስለ *ሰዎች* አይደለም (1ኛ ጴጥ. 2፡5)። በግሌ እንደማምነው ጳውሎስ የሚያመለክተው ወደ *እግዚአብሔር ቃል ዶክትሪን* ነው። በዚህ ምዕራፍ እያንዳንዱ ክፍል፥ ቃሉ ለምልክትነት የተቀመጠው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ምስል በሚስማማ መልኩ ነው። ቃሉ ለቤተሰብ ምግብ፥ ለማሣ ዘር፥ ለሕንፃ ደግሞ የማነጫ ቁሳቁስ ነው።

የምሳሌ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ጥበብን ሊፈለግ፥ ሊጠበቅ፥ እና በዕለታዊ ሕይወት *ሥራ* ላይ ሊውል እንደሚገባ ገንዘብ ያስቀምጠዋል። እነዚህን ምንባቦች አጢን፡-

> «ጥበብን የሚያገኝ ሰው ምስጉን ነው፥ ማስተዋልንም ገንዘቡ የሚያደርግ፤ በወርቅና በብር ከመነገድ ይልቅ በእርስዋ መነገድ ይሻላልና። ከቀይ ዕንቍም ትከብራለች» (3፡13-15)።

> «ልጄ ሆይ፥ ቃሌን ብትቀበል፥ ትእዛዜንም በአንተ ዘንድ ሸሽገህ ብትይዛት፥ ጆሮህ ጥበብን እንዲያደምጥ ታደርጋለህ፥ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ። ረቂቅ እውቀትን ብትጠራት፥ ለማስተዋልም ድምፅህን ብታነሣ፥ እርስዋንም እንደ ብር ብትፈላልጋት፥ እርስዋንም እንደ ተቀበረ ገንዘብ ብትሻት፤ የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት ታውቃለህ፥ የአምላክንም እውቀት ታገኛለህ» (2፡1-5)።

«ተግሣጼን እንጂ ብርን አትቀበሉ፥ ከምዝምዝ ወርቅም ይልቅ እውቀትን ተቀበሉ። ጥበብ ከቀይ ዕንቊ ትበልጣለችና፤ የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም» (8፡10–11)።

ጳውሎስ በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ስለ *ጥበብ* ያስተምር እንደነበር በምታስታውስበት ጊዜ፥ በቀላሉ ግንኙነቱን ማየት ትችላለህ። ቆሮንቶሳውያን በቃሉ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ጥበብ ላይ መመካት ሲገባቸው ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመገንባት ይሞክሩ የነበሩት በሰው ጥበብ፥ በዓለም ጥበብ አማካኝነት ነበር።

ይህ ለእኔ የሚገባኝ የቃሉ አገልጋዮች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በጥልቀት ምሰው በመግባት ውድ የሆኑ ወርቅ፥ ብር እና ዕንቁዎችን በማውጣት እነዚህን እውነቶች በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ መገንባት እንደሚገባቸው ነው። ዲ. ኤል. ሙዲ አማኞች ተገቢው አክብሮትና ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል የሚል አባባል ነበራቸው። እግዚአብሔር *ጥራትንም* ሆነ *ብዛትን* ይፈልጋል። ጳውሎስ ደግሞ ሁለቱንም መያዝ እንደሚቻል ግልጽ አድርጎአል። ታማኙ አገልጋይ በማሣው በመሥራት እድገቱን ማየት ይችላል። እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል በማነጽ ውበትን እና ዘላቂ በረከትን ማየት ይችላል።

የእግዚአብሔር ሕንጻ አንዱ ክፍል መሆን ጽኑ ነገር ነው። ርካሽ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ «ካረከስን»፥ እግዚአብሔር እንደሚያፈርሰን ቁ. 16–17 ያስጠነቅቀናል! ይህ ደግሞ የዘላለም ፍርድ ማለት አይደለም። ምክንያቱም ቁ. 15 እያንዳንዱ ሠራተኛ ምንም እንኳ ሽልማት ቢያጣም እንደሚድን ያረጋግጥልናል። ለእኔ እንደሚመስለኝ ጳውሎስ የሚለው እያንዳንዳችን *በገዛ ራሳችን ሕይወት የምንገነባውን* በቤተ ክርስቲያን ውስጥም እንደ ምንገነባ ነው። በሕንድ አገር ብዙ የሠራ ሚሲዮናዊ ኤሚ ካርማይክል «እኛ ከጠለቅነው ይበልጥ *ሥራው* የጠለቀ ሊሆን አይችልም» ይሉ ነበር። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘላቂ የሆኑ እሴቶችን የማንገነባ ከሆነ መጨረሻችን ሕይወታችንን ማፈራረስ ነው። ለሰዎች በጣም ስኬታማ የሆንን ብንመስልም፥ ነገር ግን «ቀኑ ይገልጠዋል»፥ በመሆኑም በዚያን ዕለት አንዳንድ አገልጋዮች ከጭስ ጋር በንነው ይቀራሉ።

አገልግሎቶችን ማወዳደር አላዋቂነት ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በቁጥር 4፡5 ላይ «ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ» በማለት ያስጠነቅቃል።

ወጣት አገልጋዮች ዶክተር ካምቤል ሞርጋንን የመድረክ አገልግሎታቸውን ስኬታማነት ምሥጢር ብዙ ጊዜ ጠይቀዋቸው ነበር። ሞርጋን እንዲህ ሲሉ መለሱ፥ «ሁል ጊዜም አንድ ነገር

እነግራቸዋለሁ– *ሥራ* በርትተህ *ሥራ*፤ እና እንደገና *ሥራ!*» ሞርጋን ከማለዳው 12 ሰዓት ጀምሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሀብትን ለመማስ በጥናት ላይ ይሆን ነበር። እንጨት፥ ሣር እና አገዳን ከጓሮህ ስለምታገኝ ለመልቀም ብዙ ልፋት አይኖርብህም። ነገር ግን ወርቅን ብርን እና ዕንቁን ከፈለግህ *መማስ አለብህ*። ሰነፍ ሰባኪዎች እና የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ምላሽ የሚሰጡበት ብዙ ነገር አላቸው– እንደዚሁም ለራሳቸው ከማጥናት ና የግላቸው ከማድረግ ይልቅ የሌሎችን *ሥራ የሚሰርቁ* ሰባኪዎች ና አስተማሪዎች የሚጠብቃቸው አንድ ዓይነት ዕጣ ነው።

*ሦስተኛ፥ ትክክለኛውን ዕቅድ ይዘን ማነጽ አለብን (3:18–20)*። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አንድን የንግድ ድርጅት እንደምታንቀሳቅስ አትመራውም ሲባል መስማት ለአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት አስደንጋጭ ነው። ይህ ማለት ጥሩ የሆኑ የንግድ መርሆዎችን አንጠቀምም ማለት ሳይሆን፥ ነገር ግን አሠራሩ ፍጹም የተለየ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ለዓለም የሚሠራ የዚህ ዓለም ጥበብ አለ፤ ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን አይሠራም።

ዓለም የምትመካው በማስታወቂያ፥ በክብር፥ በገንዘብ ና በታዋቂ ሰዎች አማካኝነት ጫና በመፍጠር ነው። ቤተ ክርስቲያን ግን በጸሎት፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፥ በትሕትና እና በመሥዋዕትነት ተደግፋ ትሠራለች። ዓለምን የምትኮርጅ ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው ስኬታማ ልትመስል ትችላለች፤ ነገር ግን በዘላለማዊው የምታተርፈው አመድን ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተገለጸችው ቤተ ክርስቲያን ለዛሬ ዘመን አስፈላጊ የሚመስሉ «የስኬታማነት ምሥጢራት» አንዱም ንብረት አልነበራቸውም፤ በመንግሥት በኩል የሚያደርጉት ተጽዕኖ አልነበረም፤ ገንዘብ አልነበራቸውም («ብርና ወርቅ የለኝም» ብሏል ጴጥሮስ)፤ መሪዎቻቸው በታወቁ ትምህርት ቤቶች ያገኙት ልዩ ትምህርት ያልነበራቸው ተራ ሰዎች ነበሩ፤ ተሳታፊ ለማግኘት ያካሄዱት ውድድር አልነበራቸውም፤ ታዋቂ ሰዎችን አማካሪ አላደረጉም፤ ይህ ሁሉ ሆኖ ዓለምን ገለባበጧት!

እግዚአብሔር ለእያንዳንዲቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ዕቅድ አለው (ፊልጵ. 2:12–13)። እያንዳንዱ መጋቢ እና የቤተ ክርስቲያን መሪ ለሚያስፈልገው ጥበብ የእግዚአብሔርን ልብ መሻት አለበት። ቁጥር 19 የሰው ጥበብ ባለቤቱን እንደሚያጠምድ (ከኢዮብ 5 .3 የተወሰደ ጥቅስ) ያስጠነቅቃል፤ ቁጥር 20 ደግሞ የሰዎች ጥበብ ወደ ከንቱነትና ወደ ድካም ብቻ እንደሚመራ [ከመዝ. (94):11 የተወሰደ ጥቅስ] ያስጠነቅቃል። ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ የዓለምን ችግሮች ብትጋራም፥ የዓለምን *ጥበብ* መኮረጅ የለባትም።

*በመጨረሻም፥ በትክክለኛው አቋመ ልቡና ማነጽ አለብን (3፡21-23)።* ያ አቋመ ልቡና የእግዚአብሔር ክብር ነው። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በሰዎች ላይ ይመኩ ነበር፤ ይህ ደግሞ ስሕተት ነበር። ሰዎችን ያወዳድሩ (4፡6) ነበር፤ በዚህ ሥጋዊ ተግባራቸውም ቤተ ክርስቲያንን ይከፋፍሉአት ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ብቻ መመካት የሚሹ ቢሆኑ ኖሮ በጉባኤያቸው መስማማት በሰፈነ ነበር።

ጳውሎስ እያንዳንዱ አማኝ በክርስቶስ ሁሉ ነገር እንዳለው በማመልከት ይህን ጥያቄ ይዘጋዋል። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለእያንዳንዱ አማኝ የተሰጠ ነው። ማንም የቤተ ክርስቲያን አባል «እኔ የጳውሎስ ነኝ!» ወይም «እኔ ጴጥሮስን እወዳለሁ!» ማለት አይገባውም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ አገልጋይ እኩል የእያንዳንዱ ምእመን ነው። የተለያዩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ተከትለን የግል ምርጫ ከመያዝ ልንታቀብ እንችል ይሆናል። ነገር ግን እነዚህ የግል ምርጫዎቻችን ከፋፋይ የሆኑ ዝንባሌዎችን እንዲይዙ መልቀቅ የለብንም። እንዲያውም፥ በአነስተኛው የሚያረካኝ ሰባኪ እጅግ የሚያስፈልገኝ እርሱ ሊሆን ይችላል!

«ሁሉም የእናንተው ነው»- ዓለምም ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን! በክርስቶስ ምንኛ ባለጠጋዎች ነን! ሁሉም ነገር ለሁሉም አማኞች የተሰጠ ከሆነ ውድድር እና ፉክክር የሚሆኑት ለምንድን ነው? «ዓይኖቻችሁን ከሰዎች ላይ አንሡ! በማለት ጳውሎስ ይገሥጻል። «ዓይኖቻችሁን በክርስቶስ ላይ አድርጉ፥ ቤተ ክርስቲያንን በማነጽም ከእርሱ ጋር አብራችሁ ሥሩ!»

«እናንተ የክርስቶስ ናችሁ» -ይህ ነገሮችን በልክ ያደርጋል። ሁሉም ነገር በክርስቶስ አለኝ፥ ነገር ግን ግድየለሽ መሆን ወይም አርነቴን ያለጥበብ መጠቀም አይገባኝም። «ሁሉ የእናንተ ነው» -ይህ የክርስቲያን *አርነት* ነው። «እናንተም የክርስቶስ ናችሁ»- ይህ የክርስቲያን *ኃላፊነት* ነው። እሳት ሲወድቅበት ወደ አመድ የማይለወጥ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ካለብን ሁለቱም ያስፈልጉናል።

ለቃሉ አገልጋዮች እንዴት መጸለይ ይገባናል! ቤተሰብን መመገብ ና ልጆችንም ወደ ብስለት ማሸጋገር አለባቸው። ዘሩን በማሣ ላይ መዝራት ና እንዲበዛም መጸለይ አለባቸው። የቃሉን መዝገብ መማስ እና እነዚህኑ መዝገቦችም ቤተመቅደስ አድርገው ማነጽ አለባቸው። «ለእነዚህ ነገሮች የሚበቃ ማን ነው?» ብሎ ጳውሎስ ማስተጋባቱ የሚያስደንቅ አይደለም። ነገር ግን ምላሹን ራሱ ሰጠ- «ብቃታችን በእግዚአብሔር ነው» (2ኛ ቆሮ. 2፡16፤ 3፡5)።

# 4

# ስለ ክርስቲያናዊ አገልግሎት. . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 4*

በምዕራፍ 3፥ ጳውሎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሦስት ምስሎች አሳይቶአል። አሁን ደግሞ የአገልጋይን ሦስት ምስሎች ያቀርባል። እነርሱም መጋቢ (ቁ. 1-6)፥ መጫወቻ (ቁ. 7-13)። እና አባት (ቁ. 14-21) ናቸው። አንባቢያኑ የአንድን ክርስቲያን አገልግሎት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመዝን ና እንደሚገመግም እንዲገባቸው ፈለገ። ቁጥር 6 የጳውሎስን ዓላማ ይገልጻል። «ስለ አንዱ በአንዱ ላይ እንዳችሁም እንዳይታበዩ።»

ሰዎችን ና አገልግሎታቸውን በምንገመግበት ጊዜ ጽንፎችን ማስወገድ አለብን። በአንድ ወገን፥ ያጋጠመንን ማንኛውንም በመቀበል ግድየለሽ ልንሆን እንችላለን። ሌላው ጽንፍ ደግሞ ጳውሎስም እንኳ ምዘናውን እስከማያልፍ ከመጠን ያለፈ ሒሰኛ መሆኑ ነው። መናፍስትን መመርመራችን አስፈላጊ ነው (1ኛ ዮሐ. 4፡1-6፤ 2ኛ ዮሐ. ልብ በል)፥ ነገር ግን በምናደርግበት ጊዜ መንፈስን እንዳናሳዝን መጠንቀቅ አለብን።

በእነዚህ ሦስት የአገልግሎት ምስሎች፥ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አገልጋይን ሦስት ባሕርያት ያቀርባል።

### *ታማኝነት- መጋቢው (1ኛ ቆሮ. 4፡1-6)*

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ለነበሩ ልዩ ልዩ አንጃዎች ለመሪዎች መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ራሱን፥ ጴጥሮስን ና አጵሎስን «የክርስቶስ አገልጋዮች» ብሎ ይጠራቸዋል። *አገልጋይ* የሚለው ቃል፥ ቃል በቃል ሲተረጎም «ቀዛፊዎች» ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው በነፋስ የሚነዱ ሰፋፊ ጥንታዊ የሮማውያን መርከቦችን የሚቀዝፉ ባሪያዎችን ነው። ጳውሎስ፥ «እኛ የመርከቡ ካፒቴን አይደለንም፥ ነገር ግን ከትእዛዝ በታች የሆንን የመርከብ ላይ ባሪያዎች ነን። እንግዲህ አንዱ ባሪያ ከሌላው ይልቃልን?» ይላል።

ቀጥሎ ጳውሎስ *የመጋቢን* ምስል ይገልጻል። መጋቢ ለጌታው ሁሉንም ነገር ያከናውናል፤ ነገር ግን የራሱ ምንም የለውም። ዮሴፍ ለጲጢፋራ ቤተሰብ ዋና መጋቢ ነበር (ዘፍ. 39)። ቤተ ክርስቲያን

የእምነት ቤተሰብ ናት (ገላ. 6:10)። እንደዚሁ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ብልጽግና ከቤተሰቡ ጋር የሚካፈሉ መጋቢዎች ናቸው (ማቴ. 13:52)። ጳውሎስ ይህን መንፈሳዊ ብልጽግና «የእግዚአብሔር ምሥጢራት» ብሎ ይጠራዋል። ይህን *ምሥጢር* የሚለውን ተፈላጊ ቃል በ 2:7 ተመልክተነው ነበር፤ ስለዚህ እንደገና ወደኋላ ተመልሰህ ልትመለከተው ትችላለህ።

የመጋቢው *ኃላፊነት ለጌታው ታማኝ መሆን* ነው። መጋቢ የቤተሰቡን አባላት ላያስደስት ይችል ይሆናል። ምናልባት አብረውት የሚያገለግሉትን ሌሎች አገልጋዮችም ላያስደስት ይችላል። ነገር ግን፥ ጌታውን የሚያስደስት ከሆነ እርሱ መልካም መጋቢ ነው። ይኸው አሳብ ራሱ በሮሜ 14:4 ተገልጾአል።

ስለዚህ፥ ቁም ነገሩ «ጳውሎስ ተወዳጅ ነውን?» ወይም «አጵሎስ ከጳውሎስ የተሻለ ሰባኪ ነውን?» የሚለው አይደለም። ቁም ነገሩ «ጳውሎስ፥ አጵሎስ ና ጴጥሮስ እግዚአብሔር ላስቀመጣቸው ሥራ ታማኝ ነበሩን?» የሚል ነው። ኢየሱስም በሉቃስ 12:48 የተመዘገበውን ምሳሌ በተናገረ ጊዜ በአእምሮው የነበረው ይኸው መመዘኛ ነበር። የእግዚአብሔር አገልጋይ በገዛ ሕይወቱ፥ በቤቱ እና በቃል አገልግሎቱ ታማኝ ከሆነ፥ መልካም መጋቢ ነውና ተገቢ ዋጋውን ይቀበላል።

ነገር ግን አገልጋይ ያለ ማቋረጥ በፍርድ ውስጥ የሚያልፍ ነው። በሚያደርገው ነገር ላይ ሁልጊዜ ትችት የሚሰነዘርበት አለ። ጳውሎስ በመጋቢ ሕይወት ላይ የሚነጣጠሩ ሦስት ዓይነት ፍርዶች እንዳሉ አመልክቶአል።

*የሰው ፍርድ* አለበት (4:3)። ሰዎች በሚተቹት ጊዜ ጳውሎስ አልተበሳጨም። ምክንያቱም የጌታው ፍርድ የላቀ መሆኑን ስለሚያውቅ ነበር። *የሰው ፍርድ* የተሰኘው፥ ቃል በቃል «ያሳውቀን» ማለት ነው። ይህ ሊመጣ ካለው *የእግዚአብሔር* የፍርድ ቀን (1:8፤ 3:13) የሚነጻጸር ነው።

አገልጋዩ *በራሱ ላይም የሚያስተላልፈው* ፍርድ አለ (4:3)። ጳውሎስ በሕይወቱ እና በአገልግሎቱ ምንም ስሕተት እንደሌለበት ያውቅ ነበር፤ ነገር ግን ያም እንኳ ነፃ አላደረገውም። አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን በደንብ አናውቀውም። በንጹሕ ሕሊና ና በተመጻዳቂ አመለካከት መካከል ያለው መስመር በጣም ጠባብና የረቀቀ ስለሆነ መጠንቀቅ አለብን።

በጣም ተፈላጊው ፍርድ *የእግዚአብሔር* ፍርድ ነው (4:4)። በእርግጥ ዛሬ እግዚአብሔር በቃሉ (ዕብ. 4:12) እና በመንፈስ

አገልግሎት አማካኝነት በእኛ ላይ ይፈርዳል። አንዳንድ ጊዜ ኃጢአትን ተጋፍጠን ንስሐ እንድንገባ ለመርዳት የምንወደውን ጓደኞችንን አገልግሎት ይጠቀማል (ማቴ. 18፡15–17)። ነገር ግን እዚህ ላይ የቀረበው ዋና ማጣቀሻ ክርስቲያን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቆምበትን የመጨረሻ ግምገማ የሚመለከት ነው (ሮሜ 14፡10፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡10)። በዚያን ጊዜ እውነተኛዎቹ ነገሮች ይገለጡና ታማኝ አገልጋዮች ይሸለማሉ።

እነዚህ ቁጥሮች ለሰብአዊ ራስ አመጻዳቂ አርነት ማራመጃ መሣሪያዎች መደረግ የለባቸውም። አጥቢያ ቤተክርስቲያን ቤተሰብ ናት፤ የቤተሰቡ አባላት ደግሞ ለማደግ እርስ በርስ መተጋገዝ አለባቸው። ለትሕትናና በፍቅር ለተቀመመ ሒስ ምንጊዜም ስፍራ አለ። የሚተቸን ሰው ትክክል ከሆነ፥ እኛን ረዳን ማለት ነው። እርሱ ትክክል ካልሆነ ደግሞ እኛ ልንረዳው እንችላለን። በሁለት አቅጣጫም ቢሆን እውነት ይጎለብታል።

ጳውሎስ በቁጥር 5 ላይ «ስለዚህ» ሲል ቀደም ብለው የተነገሩትን እውነቶች ወደ ግል ተዛምዶ ሊያመጣቸው መሆኑን እንድንጠባበቅ ያነሣሣል። ይህን ክፍል ግን በሦስት ጣምራ ግሣጼዎች ይደመድመዋል።

*በመጀመሪያ፥ «ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ»* (4፡5)። ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን ጌታ የሚገመግመው በሚመለስበት ጊዜ ነው፤ ስለሆነም እስከዚያ ቀን ድረስ ጠብቁ። እንደ እውነቱ ከሆነማ፥ የሰዎችን ልብ ማየት አትችልም፤ ተነሥተህ አቋመ ልቡናቸውን ልትፈርድበት አትችልም። ያን ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። «ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል» (1ኛ ሳሙ. 16፡7)።

በጳውሎስ ላይ ፍርድን ያስተላልፉ የነበሩት ቆሮንቶሳውያን በመሠረቱ በእግዚአብሔር ቦታ ራሳቸውን ማስቀመጣቸው ና ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን መብት ለራሳቸው መናጠቃቸው ነበር። እኔም በራሴ አገልግሎት ይህን ስሕተት ስንት ጊዜ ፈጸምሁ! አንድን ሁኔታ ትክክል ባልሆነ መንገድ መገንዘብ ና ሰውንም ያለ አግባብ መፍረድ ምንኛ ቀላል ነው።

*ሁለተኛ፥ «የምትፈርዱት ትክክል ባልሆነ መለኪያ ነው»* (4፡6)። ቆሮንቶሳውያን የተለያዩ ሰዎችን ይመዝኑ የነበሩት በገዛ ራሳቸው ምርጫ ግላዊ ጥላቻ ላይ ተመርኩዘው ነበር። አገልጋዮችንም እንኳ አንዱን ከሌላው ያበላልጡ ነበር። ለግምገማ ብቸኛው ትክክለኛ መሠረት «የተጻፈው» የእግዚአብሔር ቃል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከአገልጋዮች የሚጠበቀው ሕይወትና አገልግሎት ምን ዓይነት እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። አዲስ መለኪያዎችን ማበጀት ለእኛ አስፈላጊያችን አይደለም። መጋቢን ከሚያፈላልጉ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ጊዜ ደብዳቤ ይደርሰኛል። እነርሱም ዕጩ የሚሆኑትን ልጠቁምላቸው እችል እንደሆነ ይጠይቁኛል። አብዛኛውን ጊዜ መስፈርቶቻቸው እግዚአብሔር በቃሉ ካስቀመጠው የራቁ ናቸው። እንደገና፥ ይህ ጳውሎስ በምዕራፍ 1 እና 2 ያነሣው–በሰዎች ና በእግዚአብሔር ጥበብ መካከል ያለ ችግር ነው።

*ሦስተኛ፥ «የተሳሳተ አቋመ ልቡና ይዛችሁ ትፈርዳላችሁ»* (4:6)። በቤተ ክርስቲያን የነበሩ እያንዳንዱ ቡድን የወደዱትን ሰው ለማነጽ ሌሎች ሰባኪዎችን ይበጣጥቁአቸው ነበር። አቋመ ልቡናቸው ፍጹም መንፈሳዊ አልነበረም። ለአንድ ሰው ወገናዊ መሆን ና ሌሎችን መቃወም በቤተ ክርስቲያን ክፍፍልን ያፋፍም ነበር። ልባቸውን መመርመርና ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሳት የነበረውን ትዕቢት መንግሎ መጣል ይገባቸው ነበር።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች የእርሱ እውነት መጋቢዎች ናቸው። ስለሆነም ቁልፍ መመዘኛቸው *የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ እና ለማስተማር ምን ያህል ታማኝ ናቸው?* የሚል ነው። እንዲያውም በታማኝነት *ማስተማር* ብቻ ሳይሆን በታማኝነት *በተግባር ማሳየትም* ነው። የሳሙኤል (1ኛ ሳሙ. 12:1–5) እና የጳውሎስ (የሐዋ. 20:17) ምስክርነት ለዚህ እውነት ማስረጃ ይሆናል።

## ትሕትና–መጫወቻ (1ኛ ቆሮ. 4:7–13)

ጳውሎስ ራሱን ና ሌሎች ሐዋርያትን «ለዓለም መጫወቻ ሆነናል» (ቁ.9) ሲል፥ በሮማውያን ግዛት የነበሩ ሰዎች አበክረው የሚያውቁትን ምሳሌ መጠቀሙ ነበር። የሮማ መንግሥት በተለያዩ ከተሞች መዝናኛዎችን በማዘጋጀት ሕዝቡን ዝም ያሰኙ ነበር። በጨዋታ የሚወዳደሩ ወንዶችን እና ከአራዊት ጋር የሚታገሉ እስረኞችን ለማየት በኋን ዜጎች የቲያትር ቤቶቻቸው ይጨናነቁ ነበር። (እንዲያውም መጫወቻ የሚለው የግሪክ ቃል ሲተረጎም «ቴአትር» የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይሰጣል።) በሮም የሚገኘው ኮሎሲየም የእነዚህ «መዝናኛዎች» ማዕከል ሆኖ ነበር።

ዋነኞቹ «ጨዋታዎች» ሲጠናቀቁ፥ ከዚያ ቀጥሎ ድሆች ና ደካሞች የሆኑ እስረኞች ከአራዊት ጋር እንዲታገሉ ይገባሉ። ከእነርሱ ብዙ የሚጠብቅ አልነበረም።

ይህ እንዴት ያለ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ትክክለኛ ሥዕል ነው! ይሁንና ጳውሎስ ቆሮንቶሳውያንን ትሑት በማድረግ ዓላማ

ለሚያካሄዳቸው ጥረቶች ለሚያገለግሉ ተከታታይ ንጽጽሮች ይህ መነሻ ነው።

*ነገሥታት–እስረኞች* (4:7–9)። በቁጥር 7 ላይ ያሉት ጥያቄዎች ቆም ብለን እንድናስብ ሊያደርጉን ይገባል። እኔ፥ ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ መጽሐፍ ቅዱስ (NASB) ለመጀመሪያው ጥያቄ የሰጠው ትርጓሜ ያስደስተኛል። «ማን ነው እንደ የበላይ የሚቆጥርህ?» አንድ ወጣት ሰባኪ ለጓደኛዬ፥ «ትሑት እንድሆን ጸልይልኝ» አለው። ጓደኛዬም መለሰና፥ «እስኪ ንገረኝ፥ ልትታበይበት የሚገባ ምን አለ?» አለው። ለምንድን ነው ሰው ራሱን ከፍ አድርጎ የሚያየው? ምናልባት እኮ ተፈላጊ ሰዎች እንደሆንን እንዲሰማን የሚያደርገው የተዛባው አስተያየታችን ሊሆን ይችላል። ለቁጥር 7 ከሁሉም የሚልቀው መግለጫ የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት ነው፥ «ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልም. . . እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» (ዮሐ. 3:27–30)።

ጳውሎስ በቁጥር 8 ላይ ቆሮንቶሳውያንን *ነገሥታት* ብሎ በሚገልጽበት ጊዜ መጠነኛ የተቀደሰ ምፀት ተጠቅሞአል። «እኛ ደግሞ ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ ብትነግሡ መልካም ይሆን ነበር!» በማለት ጻፈ። «ነገር ግን በዚህ ፈንታ፥ ወደ መጫወቻው መውጣት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ መሥቃየት አለብን። በሰው ፊት እናንተ ቀዳሚዎች ናችሁ፤ እኛ ሐዋርያት ግን መጨረሻዎች ነን» በእግዚአብሔር ፊት ሐዋርያት ቀዳሚዎች ነበሩ (12:28)፥ ነገር ግን በሰዎች ዓይን መጨረሻ ነበሩ።

በአገልግሎት ውስጥ ለትዕቢት ስፍራ የለም። እንደ ጳውሎስ ያለ ታላቅ መሪ ራሱን «በማሳያው ቦታ በፕሮግራሙ መጨረሻ» ካደረገ፥ ይህ የተቀረነውን የት ይከትተናል? እግዚአብሔር ከሰጠው መለኪያ በተለየ አገልጋዮችን የሚመዝኑ ከሆነ፥ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የተሳሳቱ ናቸው። ተወዳጅ ሰባኪዎቻቸውንም ማሞካሸታቸው ስሕተተኞች ያደርጋቸዋል። ይህ ማለት ታማኝ አገልጋዮች ሊታወቁ አይችሉም ወይም አይከበሩም ማለት አይደለም። ነገር ግን፥ በነገር ሁሉ እግዚአብሔር መከበር ይገባዋል (1ኛ ተሰ. 5:12–13)።

*ልባሞች–ሞኞች* (4:10)። ጳውሎስ በሰዎች መለኪያ አኳያ ሞኝ ነበር። የአይሁድ ሃይማኖታዊ መሪ በመሆኑ ጸንቶ ቢቀጥል ኖሮ በሃይማኖቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰ ነበር (ገላ. 1:14)። ወይም በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ከነበሩ የሕግ ሊቃውንት ወግኖ ለአሕዛብ ባያገለግል ኖሮ፥ አብዛኛው ስደት በቀረለት ነበር (የሐዋ. 15:21፥17)።

ነገር ግን ጳውሎስ «ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወድዳለህ?» (የሐዋ. 9:6) በማለት ጌታን በጠየቀበት ጊዜ፥ ክልቡ ማለቱ ነበር።

ቆሮንቶሳውያን በገዛ ዓይኖቻቸው ፊት ልባሞች ነበሩ፥ ነገር ግን እንደ እውነቱ ከሆነ በእግዚአብሔር ዓይን ሞኞች ነበሩ። በዓለም ጥበብ ና መለኪያ ላይ መመካታቸው፥ እንደ ሞኞች ማድረጋቸው ነበር። በመንፈሳዊ ረገድ ልባም ወይም ጥበበኛ መሆን በዓለም ፊት ሞኝ መሆን ነው (1ኛ ቆሮ. 3:18)። ራሴን ሁልጊዜ የሰማእቱን የጂም ኤሊዮትን ቃላት ስጠቅስ አገኘዋለሁ። «ሊያጣው የማይችለውን ለማግኘት ሲል ሊያቆየው የማይችለውን የሚሰጥ እርሱ ሞኝ አይደለም።»

*ኃይለኞች- ደካሞች* (4:10)። ጳውሎስ በኃይሉ የተመካባቸው ጊዜያት ነበሩ፤ ከዚያ በኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲገናኝ ገንዘቤ ናቸው ብሎ ያሰባቸው ዕዳ መሆናቸውን ደረሰበት (ፊልጵ. 3)። የእርሱ መንፈሳዊ ብርታት የደካማነቱ ውጤት መሆኑን ጳውሎስ የደረሰበት ራሱ ከገጠመው *ሥቃይ ተነሥቶ* ነበር (2ኛ ቆሮ. 12:7-10)። ብርቱ ነኝ ብሎ የሚያስብ ብርቱ፥ ደካማ ነው፤ ነገር ግን ደካማ መሆኑን የሚያውቅ ደካማ ብርቱ ይሆናል።

ቆሮንቶሳውያን በመንፈሳዊ ነገር ስለደረሱበት ደረጃ ይመኩ ነበር። በቤተ ክርስቲያን የነበሩ አንጃዎች በሰብአዊ መሪዎቻቸው እና በተወዳጅ ሰባኪዎቻቸው ይኮሩ ነበር። ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ደካማነት ነበር። ብርታት የሚመጣው እግዚአብሔር ክብርን ሲቀዳጅ ብቻ ነው። «ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና [ፍጹም ይሆናል] » (2ኛ ቆሮ. 12:9)።

*የተከበራችሁ- የተዋረድን* (4:10-13)። የነገሩ ሁሉ እምብርት ይህ ነው። በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰው የሚመጣውን ክብር ፈለጉ። ራሳቸውን «ከታላላቅ ሰዎች» ጋር አንድ በማድረግ ክብርን «ለመዋስ» ይሞክሩ ነበር። ጳውሎስ እንዲህ ብሎ መልሶአል፥ «ከእኛ ጋር ከሆናችሁ፥ ለመከራ ብትዘጋጁ ይሻላል። እኛ ሐዋርያት የተከበርን አይደለንም-የተናቅን ነን!»

ከዚህ ቀጠለና ጳውሎስ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይነቱ መታገሥ ያለበትን እጦት ና መከራ ገለጸ። ድንኳን ሰፊ ሆኖ በገዛ እጆቹ መሥራቱ በብዙዎች ዓይን ሳያስንቀው አልቀረም፤ ምክንያቱም ግሪኮች ዕደ ጥበብን ይንቁ ነበርና።

በተጨማሪም ጳውሎስ ሰዎች በእርሱ ላይ ለሚፈጽሙት ነገር እንዴት ምላሽ እንደሰጠም ገልጾአል፤ ይህ በራሱ ጳውሎስን ታላቅ በማድረጉ በኩል አስተዋጽኦ አበርክቶአል። ሕይወት ለእኛ

የሚያደርገው፥ ሕይወት በእኛ ውስጥ በሚያገኘው ይወሰናል። ጳውሎስ ሲረግሙት፥ መረቀ፥ ልክ ኢየሱስ እንዳዘዘው (ማቴ. 5፡44)። ሲሰደድ፥ በእግዚአብሔር ጸጋ ታገሠ፥ አጸፋውንም አልመለሰም። ክፉ ሲናገሩት፥ ጳውሎስ ለመማለድ ሞከረ። በሁሉም ነገሮች፥ በፍቅር ለመመለስ ተጣጣረ።

ውጤቱስ ምን ነበር? «ሰዎች እንደ ዓለም ጥራጊ. . . የሁሉም ነገር ጉድፍ» (1ኛ ቆሮ. 4፡13) አድርገው ቆጠሩት። እንደዚህ ያለውን ሰው ከምድር አስወግደው! በሕይወት ይኖር ዘንድ አይገባውምና! (የሐዋ. 22፡22) ጳውሎስና ሌሎች ሐዋርያት ልክ በጌታቸው ላይ እንደተደረገበት ነው የተደረገባቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ነቀፋቸውን ገፍፎ ለስሙ ክብርን አመጣ።

የአገልግሎት ታማኝነትና የልብ ትሕትና እነዚህ ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ ባሕርያት ናቸው። ለመሥራት ፈቃደኛ ለመሠቃየትም ፈቃደኛ መሆን ይገባዋል። ታማኝ መሆን አንድ ነገር ነው፥ ዝነኛ መሆን ደግሞ በጣም የተለየ ነገር ነው። ለሌሎቹ ሚዛን ለመስጠት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሦስተኛ ባሕርይ አለ።

## የውሃት– አባት (1ኛ ቆሮ. 4፡14–21)

ጳውሎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ከቤተሰብ ጋር ማነጻጸሩ የሚታወስ ነው (3፡1–4)። አሁን ግን የአጽንኦቱ ማዕከል አገልጋዩ እንደ «መንፈሳዊ አባት» መሆኑ ላይ ነው። በየትኛዎቹም መልእክቶቹ ጳውሎስ ራሱን «አባት» ብሎ አልጠራም። ጌታ በማቴ. 23፡8–12 ላለው ክፍል የሰጠውን ትምህርት ያውቅ ስለነበር ነው። ነገር ግን ራሱን ከአንድ «መንፈሳዊ አባት» ጋር በማነጻጸር፥ ጳውሎስ ስለ እነርሱ ሆኖ ስለፈጸማቸው ጠቃሚ አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያንን አስታወሳት።

*በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ ቤተሰብን መሥርቷል* (4፡14–15)። ቆሮንቶሳውያን በእምነት የጳውሎስ ተወዳጅ ልጆች ነበሩ። ወንጌልን ለአንድ ሰው ስናካፍል ና በክርስቶስ ወደሚገኝ እምነት በደስታ ስንመራው ለሕይወቱ «መንፈሳዊ ወላጅ» እንሆናለን። ይህ በግለሰቡ እምነት ላይ ምንም ዓይነት የተለየ ሥልጣን አያጎናጽፈንም (2ኛ ቆሮ. 1፡24)፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ለእድገቱ እንዲረዳው የሚጠቀምበትን ልዩ ግንኙነት ይፈጥራል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አዲስ የተወለዱ ክርስቲያኖች እንዲያድጉ የምትረዳ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናት።

በመለወጣቸው ጳውሎስ የወሰደው «ክብር» አለመኖሩን ልብ ማለት ጠቃሚ ነው። መንፈሳዊ ልደታቸው *በክርስቶስና በወንጌሉ*

አማካኝነት ነው። ኃጢአተኞች ዳግም የሚወለዱት በእግዚአብሔር መንፈስ ና በእግዚአብሔር ቃል (1ኛ ጴጥ. 1:23-25፤ ዮሐ. 3:6) ነው። ጳውሎስ በልደታቸው ወቅት ከአጠገባቸው የቆመና የረዳቸው «አባት» ነው።

አንድ ሕፃን ልጅ ብዙ ሞግዚቶች እና አስተማሪዎች ሊኖሩት ይችላል። ነገር ግን ሊኖረው የሚችለው አንድ አባት ብቻ ነው። በማንም ሊታገድ የማይገባ ልዩ ግንኙነት ከአባቱ ጋር አለው። ጳውሎስ ከመምጣቱ በፊት በቆሮንቶስ ምንም ቤተ ክርስቲያን አልነበረም፤ በመሆኑም ሁለተኛ ትውልድ አማኞች ቢሆኑም እንኳ የጳውሎስ ውጤታማ አገልግሎት ፍሬ ነበሩ።

ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲመሠርት አጵሎስ ተከተለውና ሕዝቡን አስተማረ። ጴጥሮስም በቆሮንቶስ አገልግሎ ነበር፤ ይህ ግን በቅዱሳት መጻሕፍት በአንዳንድ በኩል ግልጽ አልተደረገም። (ምናልባት ራሱ በግንባር የተገኘ ሳይሆን፥ ነገር ግን ሌሎች አገልጋዮች ከኢየሩሳሌም የጴጥሮስ «ወኪል» ሆነው በቆሮንቶስ ሳያገለግሉ አልቀሩም።) የእግዚአብሔር ልጆች የተለያዩ አስተማሪዎች አገልግሎቶች ያስፈልጉአቸዋል። ነገር ግን ወደ ክርስቶስ ያመጣቸውን «መንፈሳዊ አባት» መዘንጋት የለባቸውም።

*ሁለተኛ፥ ጳውሎስ ለቤተሰቡ ምሳሌ ነበር* (4:16-17)። ልጆች ወላጆቻቸውን ለበጎ ይሁን ለክፉ፥ የመኮረጅ ነገር አላቸው። ተመራማሪዎች እንደሚሉን ከሆነ ወጣቶች መጠጥን የሚለምዱት ከጓደኞቻቸው ሳይሆን ከቤት ነው። የእኔ ግምት ሌሎችም መጥፎ ልማዶች በዚሁ መንገድ እንደሚለመዱ ነው።

*ተከታዮች* የሚለው ቃል፥ በቀጥታ ሲተረጎም «ኮራጆች» ይሆናል። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 3:17 ራሱን እንደሚያመጻድቅ አድርገው እንዳያስቡት ይህን ተግሣጽ ሰጠ። ትንንሽ ልጆች በመጀመሪያ የሚማሩት በምሳሌ፥ ከዚያም በገለጻ ነው። ጳውሎስ በቆሮንቶስ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት ባገለገለበት ጊዜ በፍቅር፥ ለክርስቶስ በመስጠት፥ በመሥዋዕትነት እና በአገልግሎት በፊታቸው ራሱን ምሳሌ አድርጎ ተከለ። «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ. 11:1)። ጳውሎስ ጥሩ ምሳሌ ነበር፤ ምክንያቱም ይከተል የነበረው ከሁሉም ምሳሌዎች ታላቁን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለነበር ነው።

ደግሞም ጳውሎስ ጥሩ አስተማሪ ነበር። አንድን ልጅ ወደ ብስለት የሚያደርሱት፥ ምሳሌም መመሪያም ሁለቱም ናቸው። ጳውሎስ በቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ያስተማረውን ዶክትሪን እና ተግባራት

ለማስታወስ ከመንፈሳዊ ልጆቹ አንዱ የሆነውን ጢሞቴዎስን ላከው። ጢሞቴዎስ ደብዳቤውን ለቤተ ክርስቲያን ሳያደርስ (16፡10) ለደብዳቤው መንገድ ለመጥረግ ራሱ በቀጥታ ወደዚያው ሄደ።

እግዚአብሔር ለአንድ ቤተ ክርስቲያን አንድ መለኪያ፥ ለሌላ ቤተክርስቲያን ደግሞ የተለየ መለኪያ አያደርግም። ፈቃዱን በተለያዩ መንገዶች ያደርግ ይሆናል (ፊልጵ. 2፡12–13)፥ ነገር ግን መሠረታዊ ዶክትሪኖች እና መርሆዎች አንድ ናቸው። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጥበብ ስለራቁና የሰውን ጥበብ ስለተከሉ፥ በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጽኑ የሆኑ የዶክትሪን ልዩነቶች አሉን። ሰዎች «ከተጻፈው» (4፡6) ርቀው ስለሄዱ ይህ በቤተ ክርስቲያን ክፍፍልን አምጥቶአል።

*ሦስተኛ፥ ጳውሎስ ቤተሰቡን ለመግራት የታመንን ነበር* (4፡18–21)። የሕፃን ፈቃድ መገራት እንጂ መደምሰስ የለበትም። ድንጉላ ፈረስ እስኪገራ ድረስ አደገኛ እና ጥቅመ ቢስ ነው! ነገር ግን አንዴ መታዘዝን ከለመደ ገራም እና ጠቃሚ ይሆናል። ትዕቢት በክርስቲያን ሕይወት እና በቤተ ክርስቲያን በጣም አደገኛ ነው። የኃጢአት እርሾ (5፡6–8) ቆሮንቶሳውያን ጳውሎስ አይምጣብን ሰውነቱ ግን ሲታይ ደካማ ነው፥ ንግግሩም የተናቀ ነው!» (2ኛ ቆሮ. 10፡8–11) እስኪሉ ድረስ «በትዕቢት እንዲነፉ» አደረጋቸው።

*ጳውሎስ አለመታዘዛቸውን ታግሦ* ት ነበር፥ ነገር ግን ሥነ ሥርዓት ለመያዝ ጊዜው እንደደረሰ ያስጠነቅቃቸዋል። ጳውሎስ «ይህ ለመጨረሻ ጊዜ ነው የምነግርህ፥ ለመጨረሻ ጊዜ!» እያለች በባለጌ ልጇ ላይ እንደምታምባርቅ ሆደ ሰፊዋ ዘመናዊ እናት አይደለም።

*ታማኝ* ወላጅ ልጁን መግራት አለበት። ማስተማርና በፊታቸው ምሳሌ ሆኖ መገኘት ብቻ አይበቃም! ሲያምፁ እና ለመታዘዝ እምቢ ሲሉ መቅጣት አለበት። ጳውሎስ በገርነት በመምጣት ኃጢአታቸውን በተለሳለሰ ሁኔታ መያዝን በመረጠ ነበር። ነገር ግን የእነርሱ የራሳቸው አመለካከት እንዲህ እንዳይሆን አስቸገረው። በትዕቢት በጣም የተወጣጠሩ ነበሩ–እንዲያውም አለመታዘዛቸውንም እንኳ ይኮሩበት ነበር! (5፡1–2)።

በዚህ አንቀጽ ንጽጽሩ የሚካሄደው *በንግግር እና በኃይል*፥ በቃላት እና በተግባር መካከል ነው። አይበገሬዎቹ ቆሮንቶሳውያን «ትልቅ ነገር ሲናገሩ» ችግር አልነበራቸውም! ብዙ ጊዜ ልጆች እንደሚያደርጉት ማለት ነው! ነገር ግን ንግግራቸውን «በአካሄዳቸው» አያጸኑትም ነበር። ሃይማኖታቸው በቃላት ብቻ ነበር። ጳውሎስ ኃጢአታቸውን እና

የእግዚአብሔርን ቅድስና በሚገልጥ መንገድ የራሱን «ንግግር» በኃይል፥ በድርጊት ለማጠናከር ዝግጁ ነበር።

ይህ ክፍል በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስለሚኖረው ሥርዓት ለሚያወሱ ቀጣይ ሁለት ምዕራፎች መንገዱን ጠርጓል። በቆሮንቶሳውያን ጉባኤ ብዙ ኃጢአት ነበርና ጳውሎስ ይህን ለማስተካከል ተዘጋጀ። ስለ ጉዳዩ ቀደም አድርጎ ደብዳቤ ጽፎ ነበር (5:9)፤ ነገር ግን ጉባኤው ሊታዘዘው አልፈቀደም። ይኼኔ ነበር ከመንፈሳውያን ምእመናን መካከል አንዳንዶቹ ጳውሎስን በመገናኘት (1:11፤ 16–17) ችግሩን ያካፈሉት። ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዳንዶቹ እንዲያማክራቸው ለጳውሎስ ደብዳቤ ጽፈው ነበር (7:1)፥ ከዚያም የጻፈላቸውን ምክር እንዲታዘዙት ጳውሎስ ጸልዮአል።

ራሳቸውን መግዛት የማይችሉ በሥርዓት እንዲገዙ ማድረግ የሕይወት መርህ ነው። የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና የሕክምና ባለሥልጣናት አሽከሪካሪዎች በሚነዱበት ጊዜ የደኅንነት መጠበቂያ ቀበቶ እንዲያስሩ ይገፋፋሉ፤ ነገር ግን ብዙ አሽከርካሪዎች ይህን አይቀበሉትም። በመሆኑም መንግሥት አሽከርካሪዎች በሚነዱበት ጊዜ የደኅንነት መጠበቂያ ቀበቶ እንዲያስሩ ሕግ ማውጣት ግድ ይሆንበታል። ይህን የማትታዘዝ ከሆነ፥ ትቀጣለህ።

ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ቤታቸውን እንዲያስተካክሉ ዕድል ሰጥቶአቸዋል። በሚከተሉት ምዕራፎች፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዴት በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር መተዳደር እንዳለባት ጳውሎስ ይገልጻል። ምን ያደርጋል፥ ቤተ ክርስቲያን ወዲያው አልታዘዘችውም። ጳውሎስ አስቸኳይ ጉብኝት ወደ ቆሮንቶስ ማድረግ ነበረበት፤ በጉብኝት ወቅት ያለፈበት ሁኔታ በጣም የሚቆጠቁጥ ነበር (2ኛ ቆሮ. 2:1፤ 12:14፤ 13:1)። ከዚያ በኋላ በጣም ጠንከር ያለ መልእክት እንዲጽፍላቸው ተገደደ (7:8–12)፤ ይህ መልእክት የተወሰደው በቲቶ ሳይሆን አልቀረም።

በእግዚአብሔር ክብር እንደሚሆን ጉዳዮቹ በአብዛኛው ተስተካክለው ነበር። ጥቂት «የማጽዳት ሥራ» ይቀር ነበር (2ኛ ቆሮ. 12:20–13:5)፥ ይሁንና በዚህ ጊዜ ቀውሱ ተገባድዶ ነበር።

የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ መሆን ቀላል ነገር አይደለም። ሰዎች የፈለጉትን ቢናገሩህ ወይም ቢያደርጉህ፥ እንደ መጋቢነትህ ለጌታህ ባለህ ታማኝነት መጽናት አለብህ። በዓለም ሰዎች ተቀባይነት እንዳላገኘህ እንዲሁ በዚህም ተቀባይነት ታጣ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋዮች የእኛ ፍቅር፥ ክብር፥ ታዛዥነት ና የጸሎት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

## 5

# ስለ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ . . . ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 5–6*

በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የተከፋፈለች ብቻ ሳትሆን ጾጋዋን የተገፈፈችም ነበረች። በጉባኤው ውስጥ ኃጢአት ነበረ፥ የሚያሳዝነው ደግሞ ሁሉም ስለ ኃጢአቱ ያውቅ ነበር። ነገር ግን ማንም ስለዚህ ጉዳይ ምንም ለማድረግ የፈለገ አይመስልም።

የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ፍጹም አይደለም፥ ነገር ግን የሰው ፍጹም አለመሆን መታጣት ለኃጢአት ማመካኛ ሊሆን አይገባውም። ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅር መቅጣት እንዳለባቸው ሁሉ፥ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም በምእመናኖቻቸው ላይ የሥነ ሥርዓት እርምጃ መውሰድን መለማመድ አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ማለት ወንጀለኛን ለመያዝ የተሰማሩ «ትሕትና የጎደላቸው የፖሊሶች ቡድን» ተግባር ማለት አይደለም። ይልቁኑ ልባቸው የተሰበረባቸው የባዘነውን የቤተሰብ አባል ለመመለስ የሚሹ የወንድሞችና እኅቶች ቡድን ነው።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት አንዳንድ አባላት ሁኔታውን ተጋፍጠው ለመለወጥ ስላልፈለጉ፥ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሦስት ጠቃሚ እሳቤዎችን አቀረበ።

### ቤተ ክርስቲያኒቱን አስቡ (1ኛ ቆሮ. 5:1–13)

«ይህ ኃጢአት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ያስከትላል?» የሚለው በእርግጥ ጠቃሚ እሳቤ ነው። ክርስቲያኖች «ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩ» ናቸው (1:2) እናም ይህ ማለት ለእግዚአብሔር ክብር የተቀደሰ ሕይወት ማለት ነው። አንድ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያኑን የሚወድድ ከሆነ፥ ኃጢአት እንዲያደክማት እና ምስክርነቷን እንዲያበላሽባት ዳር ቆሞ አይመለከትም።

እንዴት ነው ምላሽ የምንሰጠው? ጳውሎስ ሦስት ወጥ መመሪያዎችን ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድትከተል ሰጣት።

*በኃጢአታቸው እንዲያዝኑ (5:1–2)።* ይህ ቃል የሚያገለግለው ለሞተ ሰው፥ ሰው ሊገልጸው የሚችለውን ምናልባትም በጣም ጥልቅ እና የሚጎዳ የግል ኃዘን ለማመልከት ነው። በማዘን ፈንታ በቆሮንቶስ

የነበሩ ሰዎች በትዕቢት ተነፉ። ቤተ ክርስቲያናቸው በጣም «ክፍት አቋም» ስለነበራት፥ ዘማውያን እንኳ በጥሩ ይዞታ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት መሆን መቻላቸውን ይመጻደቁበት ነበር!

የወቅቱ ኃጢአት በቤተሰብ መካከል የተፈጸመ ወሲብ ነበር። የታወቀ ክርስቲያን (የቤተ ክርስቲያን አባል የነበረ) በዘላቂ የወሲብ ኅብረት ከእንጀራ እናቱ ጋር ይኖር ነበር። ጳውሎስ በሴቲቱ ላይ ፍርድ ስለማያስተላልፍ (ቁ. 9–13)፥ ይህች ሴት የጉባኤው አባል፥ ምናልባትም ክርስቲያን እንኳ ያልነበረች እንደሆነ እንገምታለን። እንዲህ ዓይነቱ ኃጢአት በብሉይ ኪዳን (ዘሌ. 18:6–8፤ 20:11) እና በአሕዛብ ሕዝቦች ሕጎችም የተወገዘ ነው። ጳውሎስ «የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ የማይገኝ ነው!» በማለት ቤተ ክርስቲያንን አሳፈራት።

ክርስቲያናዊ ሕይወት ደስታ የሞላበት ግብዣ ዓይነት (ቁ. 8) መሆኑ እውነት ቢሆንም፥ ኃዘን የሚሆንበትም አንዳንድ ጊዜያት አሉ። ክርስቲያን ወንድም ወይም እኅት ኃጢአት በሚያደርጉበት ጊዜ፥ ወቅቱ ቤተሰቡ የሚያዝንበትና ለወደቀው አማኝ እርዳታን የሚሻበት ነው (ገላ. 6:1–2)። የጌታን ነገር በተመለከተ በቆሮንቶስ የነበረው ወንድም «ሞቶአል»። ከጌታ እና በቤተ ክርስቲያን የተቀደሰ ሕይወት ከሚኖሩት ሰዎች ኅብረት ተለይቶአል።

*በኃጢአት ላይ ፍረዱ* (5:3–5)። ክርስቲያኖች አንዳችን የሌላችንን አቋመ ልቡና (ማቴ. 7:1–5)፥ ወይም አገልግሎት (1ኛ ቆሮ. 4:5) እንድንፈርድበት የሚገባ ባይሆንም፥ ስለ እርስ በርሳችን ጠባይና ተግባር እውነተኞች እንድንሆን ይጠበቅብናል። በራሴ የመጋቢነት አገልግሎት፥ በቤተክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ እንዲደረግ ማነሣሣት ያስደሰተኝ ጊዜ ፈጽሞ የለም፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የታዘዘ ስለሆነ፥ እግዚአብሔርን መታዘዝ እና ግላዊ ስሜቶችን ወደ ጎን ማድረግ ይገባናል።

ጳውሎስ እዚህ ላይ የገለጸው ጥፋተኛው በመለኮታዊ ሕግ መሠረት የተዳኘበትን ኦፊሴላዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ነው። ግልጽ ኃጢአት በግልጽ ሊዳኝ እና ሊወገዝ ይገባዋል። (ጌታችን ስለ ቅጣት– የሥነ ሥርዓት እርምጃ የሰጠውን መመሪያ፥ ከማቴዎስ 18:15–20 አጥና።) ኃጢአቱ ከጉያ ውስጥ ተሸጉጦ የሚታለፍ አልነበረም፤ አገር ያወቀው እና ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በነበሩት ባልዳኑ ሰዎች መካከል እንኳ የተገኘ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን በአንድ ላይ ተሰብስባ ጥፋተኛውን ማስወገድ ነበረባት። ጳውሎስ ሲያዝዛቸው የተጠቀመውን ጠንካራ ቃል ልብ

በል። «የአባቱን ሚስት ያገባ» (ቁ. 2)፥ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት «ለሰይጣን እንዲሰጥ» (ቁ. 5)፥ «አስወግዱ» (ቁ.7)፥ «ከመካከላችሁ አውጡት» (ቁ.13)። ጳውሎስ ጥፋተኛውን በልስላሴ እንዲያስተናግዱት አላሳሰባቸውም። በእርግጥ አስቀድሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ መሪዎች ሰውየውን ለመመለስ በግል የጣሩ ይመስለናል።

ይህ መደረግ የነበረበት በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን – በስሙ – እንጂ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን አልነበረም። የቤተ ክርስቲያን አባልነት ከባድ ነገር ስለሆነ በቀላል ወይም በግድ የለሽነት የሚያዝ ጉዳይ አይደለም።

ክርስቲያንን «ለሰይጣን» መስጠት ማለት ምን ማለት ነው? ደኅንነቱን ማሳጣት ማለት አይደለም፤ ቀድሞ ነገር ደኅንነትን የምታድል ቤተ ክርስቲያን አይደለችም። አንድ ክርስቲያን ከጌታ እና ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ሲኖረው፥ ልዩ በሆነ ጥበቃ ከሰይጣን ይጋረዳል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ኅብረቱን ካቋረጠ እና ከቤተ ክርስቲያን ከተወገደ፥ የጠላት «መቀለጃ» ይሆናል። በኃጢአት የወደቀው አማኝ ንስሐ ገብቶ ወደ ጌታ እንዲመለስ፥ እግዚአብሔር የጥፋተኛውን ሰውነት ሰይጣን እንዲያጠቃ ሊፈቅድለት ይችላል።

*ኃጢአትን (አሮጌውን እርሾ) አስወግዱ* (5፡6–13)። እዚህ ላይ የቀረበው የፋሲካ እራት ምሳሌ ነው (ዘፀአ. 12)። እኛን ከኃጢአታችን እርነት ለማውጣት ደሙን ያፈሰሰው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ነው (ዮሐ. 1፡29፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18–25)። በግብጽ የነበሩት አይሁድ ከሞት ያመለጡት የጠቦቱን በግ ደም በመቀባት ነበር። ደሙን ከቀቡት በኋላ፥ የአይሁድ ቤተሰቦች የፋሲካውን እራት ተመገቡ። ከመስፈርቶቹ አንዱ በመኖሪያቸው ምንም ዓይነት እርሾ እንዳይገኝ የሚል ነበር። በበዓሉ ላይ የሚቀርበው ቂጣም እንኳ ያልቦካ ነበር።

እርሾ የኃጢአት ምሳሌ ነው። ትንሽ ሆኖ ነገር ግን ኃይለኛ ነው፤ የሚሠራው በስውር ነው፤ ከዚያም ሊጡን «ይነፋዋል»፤ ከዚያም ይሰራጫል። ኃጢአት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ያደርግ የነበረው እንደ ትንሽ እርሾ ነበር። መላውን እንጀራ (ጉባኤውን) ያረክስ ነበር። በቀዶ ሕክምና መወገድ እንደሚገባው በሰውነት ውስጥ እንዳለ አደገኛ ካንሰር ነበር።

ቤተ ክርስቲያን ከ«አሮጌው እርሾ» – ክርስቶስን ከማመናችን በፊት ከነበሩ የሕይወት ግሳንግሶች – ራሷን ማጽዳት አለባት። ምቀኝነትና ክፋትን (በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ብዙ ቅሬታዎች ነበሩ) አስወግደን በእነዚህ ቦታ ትሕትናን እና እውነትን

መተካት አለብን። እንደ እንጀራ (1ኛ ቆሮ. 10:17)፥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተቻለ መጠን ንጹሕ መሆን አለባት።

ይሁንና ቤተ ክርስቲያን በውጭ ባሉት መፍረድና መኮነን የለባትም። የዚህ ዓይነቱ ፍርድ ወደፊት የሚሆን ሲሆን ኃላፊነትን የሚወስደውም እግዚአብሔር ነው። በቁጥር 9-13 ከዓለም የመለየትን አስፈላጊነት ጳውሎስ እንደገና አጽንኦት ይሰጥበታል። ክርስቲያኖች ብቸኛ መሆን ሳይሆን መለየት ነው ያለባቸው። ከኃጢአተኞች ጋር ከመገናኘት ልንወገድ አንችልም፤ ነገር ግን በእነርሱ ኃጢአት መበከልን ልናስወግድ እንችላለን።

በዚህ ስፍራ በተጠቀሱት ዓይነት ኃጢአቶች ክርስቲያን ተብዬው ሰው ከተወነጀለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩን ከእርሱ ጋር ማስተካከል አለባት። እያንዳንዱ ምእመን ከእርሱ ጋር «መተባበር» የለባቸውም (ቁ. 9- «አትቀላቀሉ»፥ «በጥልቅ አትቀራረቡ»)። ከዚህ ሰው ጋር አብሮ መብላት አልነበረባቸውም፤ ይህም በግል የሚደረገውን ወይም በማኅበር የሚደረገውን የጌታን እራት የሚመለከት ሊሆን ይችላል (1ˢ:23-34ን ተመልከት)።

የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ቀላል ወይም ተወዳጅ አይደለም፤ ነገር ግን አስፈላጊ ነው። በአግባቡ ከተሠራበት እግዚአብሔር የባዘነውን አማኝ ለመውቀስ እና ለመመለስ ይጠቀምበታል። ሁለተኛ ቆሮንቶስ 2:1-11 እንደሚያሳየው ይህ ሰው ንስሐ ገብቶ ወደ ኅብረቱ ተመልሶአል።

## የጠፉ ኃጢአተኞችን አስቡ (1ኛ ቆሮ. 6:1-8)

በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት በከተማው ውስጥ ምስክርነቷን እያጣች ነበር። ያልዳኑት በጉባኤው መካከል ስላለው ዝሙት ማወቃቸው ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አባላት መካሰሳቸውንም ደርሰውበት ነበር። የሥጋ ኃጢአቶች ብቻ ሳይሆኑ የመንፈስ ኃጢአቶችም ነበሩ (2ኛ ቆሮ. 7:1)።

ግሪኮች በአጠቃላይ፥ ደግሞ አቴናውያን በተለይ የችሎት ሰዎች በመሆን የታወቁ ነበሩ። የግሪክ ቲአትር ደራሲ አሪስቶፋኒስ ከገጸባሕርያቱ አንዱን በካርታ ላይ ግሪክ የት እንዳለች እንዲጠየቅ አደረገ። በዚህ ጊዜ ፈልገው ሲያሳዩት፥ የለም ይኼ ነገር ስሕተት መሆን አለበት- ምክንያቱም ምንም የሙግት ሂደት ሲካሄድ አላይም! ብሎ መለሰ። ይሁንና አሜሪካንም ወደዚህ ዓይነቱ ስመጥርነት በፍጥነት እየተሸጋገረች ነው። በቅርቡ በአሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ከ200,000 በላይ የሚሆኑ ከወንጀል ውጭ የሆኑ ክሶች በፌደራሉ ፍርድ ቤቶች ፋይል ተከፍቶባቸው ነበር። ወደ 610,000

ጠበቃዎች (ቁጥራቸው እየጨመረ ነው) ጉዳዮቹን ይዘዋቸዋል። በ1977፥ ከ12 ሚሊዮን ክሶች በላይ በመንግሥት ፍርድ ቤቶች ፋይል ተከፍቶባቸዋል።

ጳውሎስ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሦስት አሳዛኝ ነገሮችን ደርሶባቸዋል። *በመጀመሪያ፥ አማኞች ላልዳኑ ሰዎች እያሳዩ የነበሩት ደካማ ምስክርነት ነበር።* የማያምኑ አይሁድ እንኳ ወንጀል-ነክ ያልሆኑ ጉዳዮቻቸውን የሚፈቱት በምኵራብ ችሎታቸው ላይ ነበር። የክርስቲያኖችን ችግር ወስዶ «ትክክለኛ ባልሆኑ» እና «በማያምኑ» ፊት መወያየት የወንጌልን ምስክርነት የሚያራክስ ነበር።

*ሁለተኛ፥ ምእመናኑ በክርስቶስ የሚጠበቅባቸውን ሙሉ አቋም ይዘው ለመገኘት አልበቁም።* ቅዱሳን አንድ ቀን በዓለም እና እንዲያውም በወደቁት መላእክትም ላይ በመፍረዱ ተግባር ስለሚሳተፉ፥ በዚህ በምድር ላይ ሆነው ልዩነቶቻቸውን መፍታት መቻል አለባቸው። ቆሮንቶሳውያን ስለ ታላላቅ ስጦታዎቻቸው በኩራት ይለፍፉ ነበር። ታዲያ ለምን ችግሮቻቸውን ለመፍታት አልተጠቀሙባቸውም?

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በቁጥር 4 ላይ ጳውሎስ ባስቀመጠው አባባል እርስ በርስ ይለያያሉ። አንዳንዶቹ መጠነኛ ምፀት የሚጠቀም ይመስላቸዋል። «ፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን? በሙያው በጣም ወደተካነ ነገር ግን ያልዳነ ዳኛ ዘንድ ከምትሄዱ፥ በቤተክርስቲያን ካሉት በጣም ደካማው ምእመን ጉዳዩን እንዲፈታ ብታደርጉ ይሻላችሁ ነበር!» ሌሎች ደግሞ «በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን» የሚለውን ሃይማኖት-የለሽ ዳኞችን የሚያመለክት አድርገው ይወስዱታል። ወይም የጳውሎስ አባባል እግዚአብሔር በጣም የተናቀውን የቤተክርስቲያን ምእምን ፈቃዱን ለማሳየት ሊጠቀምበት ይችላል ማለት ይሆናል። ውጤቱ ዞሮ ዞሮ አንድ ነው። ሙግታቸውን ወደ ፍርድ ቤት ማውጣት ለክርስቲያኖች ስሕተት ነው።

በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ጉዳዮችን ለማስፈጸም ሕግ የሚያስገድዳቸው «ጠቃሚ ክሶች» ይኖራሉ። ጳውሎስ የሚናገረው ስለ እነዚህ አይደለም። ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት ለማስፈጸም የቤተ ክርስቲያን አባላት «ጉሮሮ ለጉሮሮ የተናነቁ» ይመስላል። በየቤተ ክርስቲያኖቻችን ዛሬ ክርስቲያን ጠበቃዎች ወንጀል-ነክ ባልሆኑ ጉዳዮች እንደ ሽምጋይ ሆነው ጉዳዮቹን ከፍርድ ቤት ውጭ መፍታታቸውን ማየቴ ያስደስተኛል።

ሦስተኛ አሳዛኝ ክስተትም ነበር። እርስ በርስ የሚካሰሱት ከወዲሁ የተረቱ ናቸው። ምንም እንኳ አንዳንዶቻቸው የፍርድ ቤት ጉዳዮቻቸውን የረቱ ቢሆኑም፥ ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዘዛቸው የባሰ ኪሣራና ወይም ሽንፈት ገጥሞአቸው ነበር። «ፈጽሞ በእናንተ ጉድለት ነው» (ቁ. 7) የሚለው «ይህ ለእናንተ ፍጹም ሽንፈት ነው» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ጳውሎስ እዚህ ላይ በማቴዎስ 5፡39–42 ያለውን የጌታ ትምህርት ማመልከቱ መሆኑ ምንም የማያጠራጥር ነበር። ወንድምን አጥቶ ምስክርነትንም ከማጣት ገንዘብን ወይም ንብረትን ማጣት ይሻላል።

በራሴ የአገልግሎት ዓመታት ውስጥ፥ ቤተ ክርስቲያኖች እና የቤተ ክርስቲያን አባላት የየግል ችግሮቻቸውን በፍርድ ቤት ለመፍታት ሲሞክሩ የተከሰተውን አሳዛኝ ውጤት አይቻለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ማንም አያሸንፍም– ከሰይጣን በስተቀር! ወደ ፍርድ ቤት ይሄዱ የነበሩ ቆሮንቶሳውያን ልክ ከሥጋ ዘመዱ ጋር ዝሙት እንደፈጸመው ሰው በጌታ እና በቤተ ክርስቲያን ስም ላይ ውርደትን ያስከተሉ ስለሆነ መቀጣት ይገባቸዋል።

አንድ ለአገልጋይነት የሚማር ተማሪ ትምህርት ቤቱን እንደሚከስ ስልክ ደውሎ የነገረኝ ትዝ ይለኛል። ነገሩ አስተዳደሩ ለትምህርት በጣም አስፈላጊ መስሎ የታየውን ነገር እንደከለከለው ይመስላል። «ረጋ እንዲል»፥ የፋካልቲ አማካሪውን እንዲያናግር እና ይህን አሳብ ከአእምሮው እንዲያወጣ መከርሁት። እርሱም ምክሬን ተቀብሎ መጥፎ ምስክርነትን አራቀ። ከዚህም ሌላ በልምምዱ መንፈሳዊ እድገት አገኘበት።

## ጌታን አስቡ (1ኛ ቆሮ. 6፡9–20)

በቆሮንቶስ ከተማ ከፍተኛ ልቅ ወሲብ ነበር። የዛሬው ዓለም እንደተያያዘው ይህ ማኅበረሰብ ወሲብን ልቅ የሚያደርግ፡– ወሲብ ጤናማ አካላዊ ተግባር ነው፥ ታዲያ ለምንድን ነው እንደፈለግን የማንጠቀመው? የሚል ፍልስፍና ነበረው። እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ወንድና ሴት ሲያበጅ ወሲብን ፈጠረ፤ ስለሆነም እንዴት መጠቀም እንዳለብን ሊነግረን መብት ያለው እርሱ እንደሆነ ጳውሎስ ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስ «የባለ ንብረት መመሪያ» ስለሆነ ሰዎች ሊታዘዙት ይገባል።

እግዚአብሔር ወሲባዊ ኃጢአቶችን ያወግዛል፤ ጳውሎስ አንዳንዶቹን በቁጥር 9 ዘርዝሮአል። በዚያን ዘመን ጣዖት ማምለክ እና በሥጋ መደሰት የማይነጣጠሉ ነበሩ። በግብረ ሰዶማዊ ግንኙነት ወንድ እና ወንድ አንዱ እንደ ባል ሌላው እንደ ሚስት ይሆኑ ነበር።

(ጳውሎስ ይህንና ሴት ለሴት ስለሚተኙት በሮሜ 1፡26-27 አውስቶአል።) በቁጥር 10፥ ጳውሎስ የመንፈስ ኃጢአት ሰለባ በመሆን፥ በስግብግብ አመለካከታቸው እርስ በርስ በሚካሰሱ አባላት ላይ ጣቱን ቀሰረ።

ሆኖም ግን እግዚአብሔር የወሲብ ኃጢአትን በማንጻት ኃጢአተኞቹን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሊያደርጋቸው ይችላል። «ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል» (ቁ. 11)። የእነዚህ ግሦች ጊዜ የሚያመለክተው የተጠናቀቀ ሥራን ነው። እንግዲህ፥ እግዚአብሔር ለእነርሱ ካደረገላቸው ሁሉ የተነሣ፥ ሰውነታቸውን ለእርሱ አገልግሎት እና ክብር የመጠቀም ግዴታ ነበረባቸው።

*እግዚአብሔር አብን አስቡ (6፡12-14)።* ሰውነታችንን ፈጥሮአል እናም አንድ ቀን ለክብሩ ያስነሣዋል። (ስለ ትንሣኤ በምዕራፍ 15 በሰፊው ተወስቶአል።) ሰውነታችን እንዲህ ያለ ድንቅ መነሻ፥ ይልቁንም ደግሞ ድንቅ የሆነ የወደፊት ዕድል እንዳለው ስንመለከት እንዴት አድርገን እንዲህ ላለ ክፉ ዓላማ እናውለዋለን?

ቆሮንቶሳውያን በሥጋ መደሰታቸውን ለመከላከል ሁለት ክርክሮችን ያነሣሉ። አንደኛ፥ «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» (ቁ. 12)። ይህ ስለ ክርስቲያን አርነት የተሳሳተ አመለካከት በመያዝ የሚነገር ተወዳጅ የቆሮንቶስ አባባል ነው። አርነት የወጣነው ወደ አዲስ ዓይነት ባርነት ውስጥ ለመግባት አይደለም! እንደ ክርስቲያኖች፥ «ይህ ነገር ባሪያ ያደርገኛል ወይ? ይህ ተግባር ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ትርፋማ ነው ወይ?» ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን።

ሁለተኛ ክርክራቸው፥ «መብል ለሆድ፥ ሆድም ለመብል» የሚል ነበር (ቁ. 13)። ወሲብን የሚደሰቱበት እና በጥንቃቄ የሚጠቀሙበት ስጦታ አድርገው ሳይሆን የፍላጎት ጥማታቸውን እንደሚቆርጥላቸው ነገር አስተናገዱት። በሥጋ መደሰት ለወሲብ እንደሆነ ሁሉ ከመጠን በላይ መጠጣት ወይም መብላት ለሆድ ነው፤ ሁለቱም ኃጢአታዊ እና አደገኛ ውጤቶችን ያስከትላሉ። የተወሰኑ ከፍጥረት በእግዚአብሔር የተሰጡን ጤናማ ፍላጎቶች አሉን ማለት፥ ለእነርሱ እጅ ሰጥተን ሁልጊዜ እናርካቸው ማለት አይደለም። ከጋብቻ ውጪ የሆነ ወሲብ አጥፊ ነው፤ በጋብቻ ውስጥ የሆነ ወሲብ ግን የሚለመልም እና ውብ ነው።

ከጋብቻ ውጭ በሆነ ወሲብ በእርግጥ ደስታ ይገኛል፤ *ነገር ግን መታነጽ የለበትም።* ከጋብቻ ውጭ የሆነ ወሲብ ባንክን እንደሚዘርፍ ሰው ነው፤ የሆነ ነገር ያገኛል፥ ሆኖም ግን የእርሱ አይደለም፤ ደግሞም አንድ ቀን ይቀጣበታል። በጋብቻ ውስጥ የሚደረግ ወሲብ ገንዘቡን

በባንክ እንደሚያስቀምጥ ሰው ነው፤ በዚያ ደኅንነት፥ ዋስትና አለ፥ ትርፉን የሚካፈልበትም የለም። በጋብቻ ውስጥ የሚደረግ ወሲብ ለወደፊት ደስታን የሚያመጣ ግንኙነትን ይገነባል፤ ነገር ግን ማንኛውም የክርስቲያናዊ ጋብቻ አማካሪ እንደሚነግርህ ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ወሲብ የወደፊት ግንኙነቶችን የሚያዳክሙ አዝማሚያዎች አሉት።

*እግዚአብሔር ወልድን አስቡ (6፡15–18)።* የአማኝ ሰውነት የክርስቶስ አካል ነው (12፡12 *መጨረሻ ተመልከት።*) ከክርስቶስ እና ከኃጢአት ጋር በአንድ ጊዜ *መተባበር* እንዴት ይቻላል? እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ *ያስደንቃል።* አንዳንድ ቆሮንቶሳውያን የቤተ መቅደስ ዘማውያንን (በአፍሮዳይት ቤተ መቅደስ አንድ ሺህ ያህል ነበሩ) *መጎብኘት* እና በዝሙት *መገናኘት* ጉዳት እንደሌለው አድርገው ይመለከቱ ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዋጋ ገዝቶናል (ቁ. 20)፥ ስለሆነም ሰውነታችን የእርሱ ነው። ከጌታ ጋር አንድ መንፈስ ስለሆንን ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ልናቀርብለት ይገባል (ሮሜ 12፡1–2)። እያንዳንዱን ቀን ሰውነትህን ለክርስቶስ በማስረከብ ብትጀምር፥ ቀኑን ሙሉ በሰውነትህ በምታደርገው ነገር የምታመጣው ትልቅ ለውጥ አለ።

ጳውሎስ የወሲብ ኃጢአትን ከባድነት ለመግለጽ ወደ ዝክረ ፍጥረት (ዘፍ. 2፡24) ያመለክታል። ወንድ እና ሴት ሰውነታቸውን በሚያዋህዱበት ጊዜ *መላው ሁለንተናቸው ይካተታል።* ወሲብ ከራሱ ጋር ጥልቅ እና ዘላቂ ውጤቶችን ይዞ የሚመጣ በጣም ሥር የሰደደ «የአንድነት» ልምምድ አለው። ጳውሎስ ሰው በአካሉ ሊፈጽመው ከሚችለው ኃጢአት ሁሉ የወሲብ ኃጢአት እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን ያስጠነቅቃል። ምክንያቱም ሁለንተናን (ቁ. 8) የሚያካትት ተግባር በመሆኑ ነው። ወሲብ በአንድ የሰውነት አካል ላይ ብቻ የሚፈጸም ተግባር አይደለም። «ወንድ»ና «ሴት» መሆን መላ አካልን ያካትታል። የወሲብ ልምምድ በመላ ሁለንተና ላይ የሚሰራጭ መዘዝ አለው ማለት ነው።

*ጋብቻ ራስን የመስጠት* ነገር ስላለበት፥ ጳውሎስ ከአመንዝራ ጋር በሥጋ መተባበር ከጋብቻ ጋር እኩል ነው የሚል አሳብ አልነበረውም። ወንድና ሴት አዲሱን ጎጆአቸውን ለመመሥረት የወላጆቻቸውን ቤት ይለቅቃሉ። መሠረቱ የእርስ በርስ መስጠት ስለሆነ *በጋብቻ ውስጥ የሚደረግ ወሲብ* የሚያንጽ የእድገት ልምምድ እንዳለው እንድናስተውል ይህ ይረዳናል። ሁለት ሰዎች ፍቅራቸውንና ታማኝነታቸውን በቃል ኪዳን ሲያጸኑ፥ የሚገነቡበትን ጠንካራ

መሠረት ይጥላሉ። ጋብቻ ወሲብን በመካከል እርስ በርስ የተሰጣጡ ጣምራዎች፥ በዚህ አስደናቂ ልምምድ እንዲያድጉ ያስችላቸዋል።

*እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን አሰቡ (6፡19–20)።* እግዚአብሔር አብ ሰውነታችንን ፈጠረ፤ እግዚአብሔር ወልድ ደግሞ ተቤዥቶት የራሱ አካል ክፍል አደረገው፤ እግዚአብሔር መንፈስ በሰውነታችን ውስጥ በመኖር የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያደርገዋል። ሰውነታችንን አግባብ ለሌለው ወሲባዊ ተግባር በማጋለጥ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የምናረክሰው እንዴት ነው?

*የእናንተ* የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን፥ ነገር ግን *ሰውነት* እና *ቤተመቅደስ* ነጠላ ቁጥር ናቸው (ቁ. 19)። እዚህ ላይ ጳውሎስ እየገለጸ ያለው ስለ ግለሰብ አማኝ ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ጭምር ነው። እያንዳንዱ የአጥቢያ ጉባኤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተጣመሩ ሰዎች «ኅብረት» ነው። የእያንዳንዱ ግለሰብ አማኝ ፀባይ አጠቃላዩን የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ይነካል።

በሁለቱም ነጥቦች ትምህርቱ ግልጽ ነው። «በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ!» የሚል ነው። መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስን ለማክበር ነበር (ዮሐ. 16፡14)። መንፈስ ቅዱስ እርሱ እንዲከብር እና እንዲታይ ብልቶቻችንን ሊጠቀም ይችላል (ፊልጵ. 1፡20–21)። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ልዩ ግንኙነት በራሱ ልዩ ኃላፊነት ያመጣል።

ስለዚህ በብልቶቻችን የምናደርገው ማንኛውም ነገር እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል። የእግዚአብሔርን ሕግ የምንጥስ ከሆንን ቅጣቱን መክፈል ይገባናል።

ይህን ክፍል በምትከልስበት ጊዜ የወሲብ ኃጢአት ሁለንተናን እንደሚነካ ትመለከታለህ። *ስሜትን* በመውረር ወደ ባርነት ይመራል (ቁ. 12)። *ሥጋን* ከአግባብ ውጭ ለሆነ ወሲብ መጠቀም እንዴት ሰውን እንደሚገዛ እና ለአጥፊ ልማዶች ባሪያ በማድረግ መላ ሕይወትን እንደሚያረክስ ማየት የሚያስፈራ ነገር ነው። ደግሞም ሰውን *በአካልም* ይጎዳል (ቁ. 18)። ዘማዊ እና አመንዝራ፥ እንዲሁም ግብረ ሰዶማዊያን፥ ኃጢአታቸውን ሊረሱት ይችላሉ፤ *ነገር ግን ኃጢአቶቻቸው አይረሱአቸውም።*

መጋቢ ሆኜ በምሰጠው የምክር አገልግሎቴ፥ ግንኙነታቸው በቅድመ–ጋብቻ እና ከጋብቻ ውጭ በሆነ ወሲብ ትዳራቸው እየፈረሰባቸው ያሉትን ባል እና ሚስቶች መርዳት ነበረብኝ። በሥጋ

የሚዘራ ዘር ፍሬው ቢዘገይም አይቀሬ ነው (ገላ. 6፡7-8)። ይቅርታን ካገኘንባቸው ኃጢአቶች መዘዞች ጋር መኖር ምንኛ አሳዛኝ ነው።

ይህን ሁሉ ካልን በኋላ፥ ወሲባዊ ኃጢአት የሚለማመዱ ዘላለማዊ መዘዞች እንደሚጠብቁአቸውም መገንዘብ አለብን። ከ9-10 ባሉት ቁጥሮች፥ ጳውሎስ እንዲህ ያሉ ኃጢአቶችን የሚለማመዱ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ ሁለቴ ተናግሮአል። አንድ ክርስቲያን እንደ ዳዊት በእነዚህ ኃጢአቶች ሊወድቅ እና ይቅርታ ሊያገኝ ይችላል፤ ነገር ግን ማንም ክርስቲያን እንዲህ ያሉትን ኃጢአቶች አይለማመድም (1ኛ ዮሐ. 3፡1-10)።

በማጠቃለያም፥ ከወሲባዊ ኃጢአቶች ሌላ ሌሎች ኃጢአቶች እንዳሉም በቅንነት ማስተዋል አለብን። በሆነ ምክንያት፥ ቤተ ክርስቲያን የአባካኙን ልጅ ኃጢአት ማውገዙ ላይ ስትረባረብ የታላቅ ወንድሙን ኃጢአት ትረሳዋለች (ሉቃ. 15፡11-32ን ተመልከት)። የመንፈስ እንዲሁም የሥጋ ኃጢአቶች አሉ-ጳውሎስ በቁጥር 10 ላይ አንዳንዶቹን ይዘረዝራቸዋል። ዝሙት በቀላሉ ሰውን ወደ ገሃነም ሊሰድድ እንደሚችል ሁሉ ገንዘብን መመኘትም እንዲሁ ያደርጋል።

የእግዚአብሔር ጸጋ የኃጢአተኛውን ሕይወት ሊለውጥ እንደሚችል ማስታወስ አለብን። «ከእናንተም አንዳንዶቻችሁ እንደነዚሁ ነበራችሁ» (ቁ. 11)። እምነት አንድን ኃጢአተኛ በክርስቶስ «አዲስ ፍጥረት» እንዴት እንደሚያደርግ ሲታሰብ በጣም ያስደንቃል (2ኛ ቆሮ. 5፡17-21)። የእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት አንዱ አካል ሆነን መኖር አስፈላጊያችን ነው። እኛ የራሳችን አይደለንም። ያበጀን የእግዚአብሔር አብ፥ የተቤዠን የእግዚአብሔር ወልድ፥ እና በእኛ ውስጥ የሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ንብረት ነን። ደግሞም የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ የቤተ ክርስቲያን ንብረትም ነን፥ ስለሆነም ኃጢአታችን ምስክርነቷን ሊያዳክም ኅብረቷንም ሊበክል ይችላል።

«እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛ ጴጥ. 1፡16)።

# 6

# ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻ . . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 7*

እስከዚህ ነጥብ ድረስ፥ ጳውሎስ ይገልጽ የነበረው በቆሮንቶስ ጉባኤ እንደሚገኙ የሚነገርላቸውን ኃጢአቶች ነበር። አሁን ግን ስለ ጋብቻ (7:1፥25)፥ ለጣዖት ስለተሠዋ መብል (8:1)፥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች (12:1)፥ ስለ ሙታን ትንሣኤ (15:1) እና ለአይሁድ ስለሚደረግ ሚሲዮናዊ መዋጮ (16:1) በጽሑፍ የጠየቁትን ጥያቄ ያነሣል።

1ኛ ቆሮንቶስ 7ን በምታጠናበት ጊዜ፥ ጳውሎስ ምላሽ እየሰጠ ያለው ለተወሰኑ ጥያቄዎች መሆኑን ልብ በል። በአንድ ምዕራፍ የተሟላ የጋብቻ «ሥነ መለኮትን» እየገለጸ አይደለም። ይህን ተፈላጊ ርእስ በተመለከተ የተቀረው መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ማየት ተገቢ ነው።

አንዳንድ ነፃ ሐያስያን ጳውሎስን የጋብቻና የሴቶች ተቃዋሚ ነው በማለት ከስሰውታል። በእርግጥ እነዚህ ክሶች ከእውነት የራቁ ናቸው። በቁጥር 6፥10፥12 እና 25 ላይ ስለጻፋቸው ነገሮች ጳውሎስ መለኮታዊ ምሪት ነበረኝ አላለም። ይልቁኑ፥ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ወዳስተማረው ያመለክት ነበር (ማቴ. 19:1–12፤ 5:31–32፤ ማር. 10:1–12፤ ሉቃ. 16:18)። ኢየሱስ ጭራሽ ያላነሣቸውን አንዳንድ ጥያቄዎች ጳውሎስ መመለስ ነበረበት። ነገር ግን ጌታ ቀደም ብሎ ባስተናገደው ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲነሣ፥ ጳውሎስ የጌታን ቃል አጣቅሶአል። መለኮታዊ ምሪት እንዳጣ መናገሩ ሳይሆን፥ ጳውሎስ የገለጸው የጻፈው ነገር በሥልጣን ኢየሱስ ካስተማረው ጋር እኩል መሆኑን ነው።

ጳውሎስ ክርስቲያናዊ ጋብቻን አስመልክቶ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ገልጾአል፤ ምክሩንም ለሦስት የተለያዩ የአማኞች ቡድኖች አስተላልፎአል።

## የትዳር ጓደኛሞች ሁለቱም ክርስቲያኖች ሲሆኑ (1ኛ ቆሮ. 7:1–11)

ቤተ ክርስቲያን ትጠይቃቸው ከነበሩት ጥያቄዎች አንዱ፥ «አለማግባት ከጋብቻ የበለጠ መንፈሳዊነት አለው ወይ?» የሚል ይመስላል።

ጳውሎስ ሲመልስ፥ ወንድ ወይም ሴት ሳያገቡ የመኖር ስጦታ ቢያገኙ ጥሩ ነው፤ አለማግባት ግን ከጋብቻ የተሻለ አይደለም፤ ለሁሉም ሰው የሚሆን የላቀ ደረጃም አይደለም ብሏል። ዶክተር ኬንት ወስት የጳውሎስን ምላሽ ሲተረጉሙ «በጽናት ሳያገቡ መኖር ለሰው ተገቢ፥ ክብሩ፥ እና ግብረገባዊ ብቃት ያለው ነው» ብለዋል።

ቁጥር 6 ሳያገቡ መኖር የተፈቀደ እንደሆነ፥ ነገር ግን ትእዛዝ እንዳይደለ ይገልጻል፤ ቁጥር 7 ደግሞ ሁሉም ሳያገቡ የመኖር ስጦታ እንደሌላቸው ይነግረናል። ይህ ጌታችን በማቴዎስ 19፡ 10–12 ካስተማረው ትምህርት ጋር ይተሳሰራል፤ «ጃንደረቦች» የሚለው የሚያመለክተው ከጋብቻ የሚታቀቡትን ነው። «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» (ዘፍ. 2፡18) በአጠቃላይ ለብዙ ሰዎች የሚሠራ እውነት ነው፤ ነገር ግን ጥቂቶች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሳያገቡ ሊኖሩ የተጠሩ ናቸው። አለማግባታቸው «ያነሰ መንፈሳዊነት» ወይም «የላቀ መንፈሳዊነት» አይደለም። በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የሚወሰን ነው።

የጋብቻ አንዱ ዓላማ «ከዝሙት ለመራቅ ነው»። ቁጥር 2 እግዚአብሔር በዚህ ጋብቻን ወይም ግብረ ሰዶማዊ «ጋብቻ»ን እንደማይደግፍ ግልጽ ያደርጋል። ከመጀመሪያው የነበረው የእግዚአብሔር ምሳሌ እና ትእዛዝ አንድ ሴት ለአንድ ወንድ መጋባቷ ነው። ይሁንና፥ ባል እና ሚስት ጤናማ የጋብቻ አካል የሆነውን የወሲብ ፍቅር መብታቸውን ያለ አግባብ መጠቀም የለባቸውም። የሚስት ሰውነት ለባል ነው፥ እንደዚሁ የባል ሰውነትም ለሚስት ነው፤ ደግሞም እያንዳንዱ ለሌላው አሳቢ መሆን ይገባዋል። ወሲባዊ ፍቅር ውብ የመተናነሻ መሣሪያ እንጂ የመጠፋፊያ ጦር ዕቃ አይደለም። አንዱ ለሌላው ወሲብን መከልከሉ ንጥቂያ ማካሄድ (1ኛ ተሰ. 4፡6ን ተመልከት) እና የትዳር ጓደኞች ለእርካታቸው ወደ ውጭ እንዲመለከቱ የሚያደርግ ነው።

ለሁሉም ነገር መሆን እንዳለበት ሁሉ መንፈሳዊው ሥጋዊውን መግዛት አለበት፤ ምክንያቱም ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነውና። ባል እና ሚስት ሙሉ ፍላጎታቸውን ለጸሎት እና ለፆም ለመስጠት (7፡5) ከወሲብ ይታቀቡ ይሆናል፤ ሆኖም ግን ይህንን ለረጅም ጊዜ መለያየት እንደ ምክንያት ሊጠቀሙበት አይገባም። ጳውሎስ ክርስቲያን ባለ ትዳሮች በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም ነገር እርስ በርስ ስምምነት እንዲኖራቸው ያበረታታል።

ከቁጥር 8–9 ባለው፥ ጳውሎስ በቁጥር 1 ስላላገቡት እና ስለ መበለቶች የተገለጸውን መርህ በማዛመድ ራሳችሁን መቆጣጠር የማትችሉ ከሆነ አግቡ ይላል።

ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችው ሳያገቡ ስለመኖር ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ስለ መፋታትም ጳውሎስን ጠይቃለች። ኢየሱስ ይህን ጥያቄ አስተናግዶት ስለነበር፥ ጳውሎስ የእርሱን ትምህርት ጠቀሰ፡- ባል እና ሚስቶች መፋታት የለባቸውም (ቁጥር 39ን ተመልከት)። ፍቺ የሚፈጠር ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሳያገቡ መኖር አለባቸው ወይም እርቅ መፈለግ አለባቸው።

ለጋብቻ በጣም ተገቢው ይህ ነው። ኢየሱስ ከዚህ የሚወጣ አንድ ነገር አድርጎአል። ከሁለቱ ወገኖች አንዱ የዝሙት ወንጀለኛ ከሆነ፥ ይህ ለፍቺ መሠረት ይሆናል። ከዚህ በጣም የሚሻለው ንስሐ መግባት፥ ይቅርታ እና እርቅ መፍጠሩ ነው፤ ነገር ግን እነዚህ ከጥያቄ ውጭ ከሆኑ፥ ጥፋተኛ ያልሆነው ወገን ሊፈታ ይችላል። ይሁንና፥ ፍቺ የመጨረሻ አማራጭ ነው፤ በመጀመሪያ በተገኘው መንገድ ሁሉ ጋብቻውን መልሶ ለማቆም መፍትሔ መፈለግ አለበት።

ባል እና ሚስት ለጌታ ራሳቸውን የሰጡ ሲሆን እና በጋብቻ ግንኙነታቸው አንዳቸው ሌላቸውን ለማስደሰት ሲጥሩ፥ ጋብቻው በጣም አርኪ ከመሆኑ የተነሣ ከሁለቱ ወገን የትኛውም በእርካታ ወደ ሌላ እንደማይቀላውጥ በመጋቢነት ልምምዴ የደረስሁበት እውነት ነው። አንድ ክርስቲያን አማካሪ አንድ ጊዜ፥ «በጋብቻ ውስጥ የወሲብ ችግሮች የሉም»፥ ያሉት ችግሮች «የወሲብ ችግርን እንደ አንድ ምልክታቸው አድርገው የሚከሰቱ የምልዐተ ባሕርያት ውዝግቦች ናቸው» አለኝ። ዛሬ በክርስቲያኖች (በቀሳውስቱ እንኳን ሳይቀር) እያሻቀበ ያለው አስፈሪ የፍቺ አዝማሚያ የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳዝን ነው።

## ክርስቲያን ካልሆኑት የተጋቡ ክርስቲያኖች (1ኛ ቆሮ. 7፡12-24)

አንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ከጋብቻ በኋላ የዳኑ ነበሩ፤ ነገር ግን የትዳር ጓደኞቻቸው ገና ያልተለወጡ ነበሩ፤ አንዳንዶቹ በቤት ውስጥ ችግር እንደነበረባቸው የሚያጠራጥር አይደለም፤ በመሆኑም ጳውሎስን፥ «ካልዳኑ የትዳር ጓደኞቻችን ጋር በትዳር መቀጠል አለብንን? የእኛ መለወጥ ነገሮችን አይቀይርምን?» በማለት ጠየቁ።

ጳውሎስም ሲመልስላቸው የትዳር ጓደኞቻቸው አብረው ለመኖር እስከፈቀዱ ድረስ ካልዳኑ የትዳር ጓደኞቻቸው ጋር በትዳር መቀጠል እንዳለባቸው አሳሰበ። ደኅንነት የጋብቻን አቋም አይቀይርም፤ ሊያደርገው የተገባ ነገር ቢኖር፥ የጋብቻን ግንኙነት ማሻሻል ነው። (ጴጥሮስ በ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡1-6 ያልዳኑ ባሎች ለነበሩአቸው ሚስቶች

የሰጠውን ምክር ልብ በል)። ጋብቻ በመሠረቱ ሥጋዊ ግንኙነት ስለሆነ («አንድ ሥጋ ይሆናሉ» – ዘፍ. 2፡24)፥ ሊቋረጥ የሚችለውም በሥጋዊ ምክንያት ነው። ዝሙት እና ሞት እንዲህ ያሉ ሁለቱ ምክንያቶች ናቸው (ቁ. 39)።

እያወቁ ያልዳነን ሰው ማግባቱ ለክርስቲያን ሰው አለመታዘዝ ነው። (በቁ. 39 «በጌታ ይሁን እንጂ» የሚለውን እና 2ኛ ቆሮ. 6፡14 ላይ ያለውን ልብ በል)። ነገር ግን አንድ ሰው ከጋብቻው በኋላ ክርስቲያን ከሆነ፥ ችግሮችን ለማስወገድ ሲል ብቻ ጋብቻውን ማቋረጥ የለበትም። እንዲያውም፥ ጳውሎስ ክርስቲያን የሆነው ወገን ባልዳነው ላይ መንፈሳዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል አጽንኦት ሰጥቶበታል። እያንዳንዱ ሰው ለክርስቶስ የግሉን ውሳኔ ማድረግ ስላለበት ቁጥር 14 ያልዳነው ወገን በአማኙ ወገን አማካኝነት ይድናል ብሎ አያስተምርም። ይልቅ፥ አማኙ በቤት ውስጥ የሚያሳድረው መንፈሳዊ ተጽዕኖ ያልዳነውን ወገን ወደ ደኅንነት ሊመራ ይችላል ነው።

የልጆችስ ሁኔታ እንዴት ነው? እንደገና ትኩረቱ የተሰጠው መንፈሳዊ ሰው በሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ ነው። አማኝ የሆኑት ባል ወይም ሚስት ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም። በተከፋፈለ ቤት ውስጥ ራሳቸውን የሰጡ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ በመኖራቸው ምክንያት ከጊዜ በኋላ ፍቅረኞቻቸው አዳኝን ሲያምኑ ለማየት መብቃታቸውን በግል አገልግሎቴ ተመልክቼአለሁ።

ደኅንነት የጋብቻን አቋም አይቀይርም። የሚስት ክርስቲያን መሆን ጋብቻውን ተቀባይነት የሚያሳጣው ከሆነ፥ በቤት ያሉ ልጆች ሕጋዊነትን ያጣሉ «ርኩሳን» በቁጥር 14)። በሌላ መልኩ ክርስቲያኑ ወገን ለጌታ ታማኝ ከሆነ፥ እነዚህ ልጆች አንድ ቀን ሊጸኑ ይችላሉ።

በክርስቲያናዊ እምነት ውስጥ «ለኖርን» ይህ አዲስ ዶክትሪን በሮማውያን ዓለም ላይ የነበረውን ጫና ለመገንዘብ ያዳግተናል። ይህ የዘር እና የማኅበራዊ አቋምን ሳይለይ፥ ለሁሉም ሰው ሊሆን የሚችል ትምህርት ነው። በሮማ ግዛት ባሪያዎችና ጨዋዎች፥ ወንዶችና ሴቶች፥ ሀብታምና ድሀ በእኩልነት የሚያመልኩበት ጉባኤ ቢኖር ምናልባት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች (ገላ. 3፡28)። ይሁንና ይህ አዲስ እኩልነት ከራሱ ጋር አንዳንድ ግራ መጋባቶችንና ችግሮችን አመጣ፤ ከእነዚህም አንዳንዶቹን ጳውሎስ ከቁጥር 17–24 ባለው ክፍል መፍትሔ ሰጥቶባቸዋል።

ጳውሎስ ያስቀመጠው መርህ ይህ ነው፡– ምንም እንኳ ሁሉም ክርስቲያኖች በክርስቶስ አንድ ቢሆኑም፥ እያንዳንዱ ጌታ ሲያድነው በነበረው ጥሪ መቆም ወይም መቀጠል አለበት። አይሁድ አማኞች

አሕዛብ ለመሆን ጥረት ማድረግ የለባቸውም (የቃል ኪዳኑን ሥጋዊ ምልክት በመፋቅ)፤ አሕዛብ ደግሞ አይሁድ ለመሆን መጣር አልነበረባቸውም (በመገረዝ)። ባሪያዎች በክርስቶስ ካገኙት እኩልነት የተነሣ ብቻ ከክርስቲያን አሳዳሪዎቻቸው አርነትን መጠየቅ ተገቢያቸው አልነበረም። ይሁንና ክርስቲያን ባሪያዎች ከተቻላቸው አርነታቸውን ለማግኘት እንዲጥሩ መክሮአቸዋል። ምናልባት ይህ በግዝ የሚገኝ ሳይሆን አልቀረም። ይህ መርህ ራሱ ካልዳኑ ወገኖች ጋር ለተጋቡ ክርስቲያኖችም ተግባራዊ ነው።

ነገር ግን ያላመነው ወገን ለቅቆ ቢሄድስ? ቁጥር 15 መልስ አለው። ክርስቲያኑ ወገን በአንድ ለመሆን አይገደድም። የተጠራነው ለሰላም ነው፤ በሰላም ለመኖር የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን (ሮሜ 12፡18)፤ ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታ ሰላም የማይቻልበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል። ያልዳነው ወገን ቢለይ ወይም ብትለይ፥ ክርስቲያን ከመጸለይ ና ለጌታ ባለው ታማኝነት ከመጽናት ያለፈ የሚያደርገው ብዙ ነገር የለውም።

መለየቱ ለክርስቲያኑ ወገን የመፋታትን እና እንደገና የማግባትን መብት ይሰጠዋልን? ጳውሎስ አላለም። ያላመነው ወገን ከሌላ የትዳር ጓደኛ ጋር መኖር ከጀመረስ? ያ ዝሙት ስለሆነ ለፍቺ ምክንያት ይሰጣል። ነገር ግን በዚህ ጊዜም እንኳ፥ ከቁጥር 10–11 የተጻፈው የሚያበረታታው ይቅርታንና የትዳርን ተመልሶ ማቆም ነው። ጳውሎስ ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን በሙሉ አላነሣም። ያስቀመጠው መንፈሳዊ መርህን እንጂ ዝርዝር ትእዛዛትን አይደለም።

የሁኔታዎች መለዋወጥ ሁልጊዜም ለችግሩ መልስ ነው ብለን ወደ ማሰቡ እናዘነብላለን። ነገር ግን የሁሉም ችግር ሥር፥ በልብ ውስጥ ያለ ችግር ነው። ብዙ ጊዜ ችግሩ በውስጣችን እንጂ በዙሪያችን አይደለም። የትዳር ጓደኛሞች በፍቺ አልፈው በአዲስ ሁኔታዎች ደስታን ሲሹ፥ ዳሩ ግን በመጨረሻ ችግራቸውን ተሸክመው የሚዞሩ መሆናቸውን ወደ መገንዘቡ ብቻ ሲደርሱ መታዘብ ችዬአለሁ። አንድ ክርስቲያን ጠበቃ አንድ ጊዜ እንዲህ አለኝ፥ «ከፍቺ የሚጠቀሙ ሰዎች ቢኖሩ ጠበቆች ብቻ ናቸው!»

## ያላገቡ ክርስቲያኖች (1ኛ ቆሮ. 7፡25–40)

ጳውሎስ ቀደም ሲል በቁጥር 8–9 ላይ ለዚህ ቡድን አጠር አድርጎ ተናግሮ ነበር፤ ነገር ግን በዚህ በመዝጊያ ምዕራፍ ላይ፥ በዝርዝር ያቀርበዋል። የእነርሱ ጥያቄ፥ «ክርስቲያን ማግባት አለበት ወይ? በቤተ ክርስቲያን ሳያገቡ እያረጁ ያሉ ሴቶችስ ዕጣ ፈንታ እንዴት ነው?» የሚል ነበር። (ቁጥር 36ን ተመልከት።) ምናልባት ጳውሎስ ይህን

የሚናገረው ለዓቅመ-ሔዋን ለደረሱ ልጃገረዶች ወላጆች ሳይሆን አይቀርም። ኢየሱስ በዚህ ርእስ ላይ ምንም ዓይነት የተለየ ትምህርት ስላልሰጠ፥ ጳውሎስ ከጌታ እንደተማረ ሰው ምክሩን ሰጥቶአል። ለጋብቻ ውሳኔ በሚያደርጉበት ጊዜ ብዙ ሁኔታዎችን እንዲያጤኑ አሳሰባቸው።

*በመጀመሪያ ያለህበትን ሁኔታ አጢን* (7፡25-31)። ወቅቱ ዓለም በለውጥ ውስጥ የምታልፍበት (ቁ. 31) የጭንቀት (ቁ.26) ጊዜ ነበር። ጌታን ለማገልገል የጊዜ ውጥረት ነበር (ቁ. 29)። መረጃ ባይኖረንም በቆሮንቶስ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ውጥረት ነበር ማለት ያስችላል። ከችግሮቹ አኳያ ሲታይ፥ ሰው ባያገባ የሚመረጥበት ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ እንዲህ ሲባል ያገቡ ሰዎች ፍቺ ይፈልጉ ማለት አልነበረም (ቁ. 27)። የጳውሎስ ምክር ያተኮረው ላላገቡት ነበር።

ይህም ማለት ማንም አያግባ የሚል ሳይሆን፤ ነገር ግን የሚያገቡ ሰዎች ከጋብቻው ጋር አብረው የሚመጡትን ፈተናዎች ለመቀበል የተዘጋጁ መሆን አለባቸው ማለት ነው (ቁ.28)። እንዲያውም፥ የተጋቡት እንኳ እንዳልተጋቡ ሆነው ለመኖር እስኪገደዱ ሁኔታው ከፍቶ የነበረ ይመስላል (ቁ. 29)። ምናልባት ጳውሎስ የሚናገረው ከኑሮ ጫና ወይም ከስደት የተነሣ እየተለያዩ ያሉትን ባል ና ሚስት ሳይሆን አልቀረም።

ሁኔታዎችን ማጤን ዛሬ ለተጫጩ ሰዎች መልካም ምክር ነው። የመጀመሪያ ጊዜ ተሞሽ ራዎች አማካይ እድሜ እያሻቀበ ነው፤ ይህም እጮኞሞች ለመጋባት ብዙ መጠበቅ እንዳለባቸው ይጠቁማል። በመጋቢነት አገልግሎቴ በምሰጠው ቅድመ-ጋብቻ ምክር፥ ለእጮኞሞች የማሳስበው በሠርግ በጣም ርካሹ ነገር የጋብቻ የምስክር ወረቀት መሆኑን ነው። ከዚያ በኋላ የሁሉም ነገር ዋጋ ይንራል!

*ሁለተኛ፥ ኃላፊነቶችን በቅንነት ቅረባቸው* (7፡32-35)። በዚህ ስፍራ አጽንኦት ያረፈበት ቃል ሳትባክኑ የሚል ሲሆን፥ «ሳትጨነቁ፥ ከመጠበብ የተነሣ ሳትበጣጠቁ» ማለት ነው። ሁለት ሰዎች አንድ ወይም ሌላ ዓይነት ሸክም ሳይጫናቸው አብረው መኖር አይችሉም፤ ነገር ግን ወደ ጋብቻ ውስጥ ተደናብሮ በመግባት የባሰ ችግር መፍጠር አያስፈልግም። ጋብቻ የብስለት መለኪያን ይፈልጋል፤ ዕድሜ ደግሞ ለብስለት ዋስትናን አይሰጥም።

አሁንም እንደገና፥ ጳውሎስ ለጌታ መኖርን በአጽንኦት አሳሰበ። ወንድ ወይም ሴት አግብተው እግዚአብሔርን በተገቢው መንገድ ማገልገል አይችሉም የሚል አሳብ አልሰጠም፤ ምክንያቱም ይህ የተቻላቸው እጅግ ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ነገር ግን የገባው

የእግዚአብሔር አገልጋይ ጓደኛውን ወይም ጓደኛዋን እንዲሁም እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ልጆች ማሰብ አለባቸው፤ ይህ ደግሞ የአሳብ መከፋፈልን ያመጣል። ጆን ዌስሊ እና ጆርጅ ዋይትፊልድ ሁለቱም ባያገቡ ኖሮ በጣም የተሻለ ሁኔታ ላይ መገኘታቸው የታሪክ እውነታ ነው፤ የዌስሊ ባለቤት መጨረሻ ላይ ጥላው ሄዳለች፤ ዋይትፊልድ በጣም ይጓዝ ስለነበር ባለቤቱ ለረጅም ጊዜ በብቸኝነት ትኖር ነበር።

ለክርስቶስ የተሰጠህና ቃሉን የምትታዘዝ ከሆነ ጌታንና የትዳር ጓደኛህን ማስደሰት ትችላለህ። ብዙዎቻችን ደስተኛ ቤተሰብና አርኪ ጋብቻ በክርስቲያናዊ የአገልግሎት ውጣ ውረዶች አስደናቂ መጽናኛ ሆነው አግኝተናል። ዝነኛው የስኮቲሽ ሰባኪ በአንድ ጉዳይ ላይ ከወሰደው አቋም የተነሣ የሕዝብ ተቃውሞ በጣም አስቸጋሪት ነበር፥ በየቀኑ ለማለት ይቻላል በጋዜጦች ላይ ጎጂ ዘገባ ይቀርብበት ነበር። አንድ ጓደኛው አንድ ቀን አገኘውና «በዚህ ሁሉ ተቃውሞ ውስጥ እንዴት ልትቆም ቻልክ?» ሲል ጠየቀው። እርሱም ዝግ ብሎ «በቤቴ ደስተኛ ስለሆንኩ ነው» በማለት መለሰ።

እግዚአብሔርን ለማገልገል ጥሪ እንዳላቸው የሚሰማቸው ያላገቡ አማኞች ጋብቻ አገልግሎታቸውን ይደግፍ ወይም ያስተጓጉል እንደሆነ ለማየት የራሳቸውን ልብ መመርመር ያስፈልጋቸዋል። ተመሳሳይ ጥሪ ያላቸውን የትዳር ጓደኛ ለመምረጥም ጠንቃቃ መሆን አለባቸው። እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ስጦታና ከእግዚአብሔርም ጥሪ ስላለው ለቃሉ መታዘዝ አለበት።

*ሦስተኛ፥ እያንዳንዱ ሁኔታ ልዩ ነው* (7፡36–38)። ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ላላገቡ ልጃገረዶች አባቶች ነው። በዚያን ዘመን፥ ጋብቻን የሚያቀናጁት ወላጆች፥ በተለይም አባቶች ነበሩ (2ኛ ቆሮ. 11፡2)። ጳውሎስ በቁጥር 35 ላይ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ ሁሉም ሊከተለው የሚገባ «ብረት ለበስ» ሕግ እንደማያስቀምጥ ተናግሮአል። አሁን ደግሞ አባት ሴት ልጁን ለጋብቻ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ነፃ ፈቃድ እንደነበረው አብራራ።

ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኖች ጋብቻዎች በ«ጣምራ» ሲመጡ አስተውያለሁ። አንዱ ጣምራ ትጭጭት እንደተፈጸመ ብዙ ሳይቆይ አራቱ ይከተላሉ። እነዚህ ሁሉ ትጭጭቶች በእግዚአብሔር ፈቃድ የሆኑ ከሆነ በጣም አስደሳች እና ድንቅ ልምምድ ነው፤ ነገር ግን እኔ የምፈራው አንዳንዶቹ የሚተጫጩት ባልንጀሮቻቸውን ለመምሰል ያህል እንዳይሆን ነው። አንዳንዴ በክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ያሉ እጮኛሞች «የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ጭንቀት» ብዬ በምጠራው

ሁኔታ ውስጥ ይገቡና ወዲያው እንደተመረቁ ከትጭጭት ተላቅቀው በጋብቻ ይቆራኛሉ። ይህን የሚያደርጉት «በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመጠባበቅ» እንዳይዳረጉ በማሰብ ነው። የሚያሳዝነው ከእነዚህ ጋብቻዎች የሚሳካላቸው የተወሰኑ ናቸው።

ምንም እንኳ ዘመናዊ የትጭጭትና የጋብቻ አካሄዳችን ለቆሮንቶሳውያን ባዕድ ቢሆንም፥ ጳውሎስ ለእነርሱ የሰጠው ምክር ዛሬም ይሠራል። እጮኛሞች ከወላጆቻቸውና ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መመካከራቸው ብልህነት ነው፤ አለበለዚያ በኋላ ወደሚጸጸቱበት ነገር ውስጥ ይዘፈቃሉ።

ጳውሎስ በቁጥር 36 ላይ «ማግባት ወደሚገባ ዕድሜ» (የዕድሜ አበባ) የሚለውን በጠቀሰ ጊዜ ቁልፍ የሆነ ችግርን ነበር የመታው። ይህ ልጃገረዲቱ እያረጀች ናት የሚል ጥንቃቄ የሚያስፈልገው አነጋገር ነው። ዶክተር ኬነት ወስት አባባሉን «የወጣትነት አበባዋን ያሳለፈች» በማለት ይተረጉሙታል። ይህች ሴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ባለቤት የለሽ በረከቶች» አንዱ ወደመሆን ጉዞ ጀምራለች ማለት ነው። አደጋው ቆሞ መቅረትን ለማስቀረት ስትል ብቻ ጋብቻ ውስጥ ዘልላ ስለምትሰጥም፥ ስሕተት ትሠራ ይሆናል የሚል ነው። አንድ መጋቢ የሆነ ጓደኛዬ ለእጮኛሞች «በተጣመመ ጋብቻ ውስጥ ከመኖር፥ በብቸኝነት ላጤ ሆኖ መኖር ይሻላል!» ይል ነበር።

እያንዳንዱ ሁኔታ ልዩ ስለሆነ፥ ወላጆችና ልጆች የጌታን ፈቃድ መሻት አለባቸው። ደስተኛ ጋብቻን ለማምጣት ከሁለት በላይ ክርስቲያን ሰዎችን ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነ ብቻ ክርስቲያናዊ ጋብቻ ሁሉ ለዛ አለው ማለት አይደለም።

*በመጨረሻም፥ ጋብቻ የዕድሜ ልክ መሆኑን አስታውስ* (7፡39–40)። የጋብቻ ትስስር ዘላቂ፥ የሕይወት ዘመን ውሳኔ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በክርስቲያናዊ ጋብቻ ውስጥ «የሙከራ ጋብቻ» የለም፤ በሌላ በኩል «አምልጦ መውጣት» የሚል አመለካከትም አይኖርም። «ይህ አመለካከት የማያዋጣን ከሆነ፥ ምን ጊዜም ፍቺ እንፈጽማለን» የሚል ነው።

በዚህ ምክንያት፥ ጋብቻ ከመልክ፥ ከገንዘብ፥ ከስሜታዊ እርካታና ከማኅበራዊ ተቀባይነት ይልቅ ጠበቅ ባለ ነገር ላይ መመሥረት አለበት። ክርስቲያናዊ መሰጠት፥ ፀባይ እና ብስለት መኖር አለባቸው። ለማደግ፥ እርስ በርስ ለመማማር፥ ይቅርታ ለማድረግና ለመርሳት፥ እርስ በርስ ለመገላገል ፈቃደኝነት መኖር አለበት። ሁለት ሕይወቶችን በአንድ ለማጣበቅ የሚያስፈልገው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ.13 የገለጸው ዓይነት ፍቅር ነው ።

ጳውሎስ ባል የሞተባቸው ሴቶች «በጌታ ይሁን እንጂ» (ቁ. 39) ለማግባት ነፃ መሆናቸውን በመንገር ይህንን ክፍል ደመደመው። ይህም ማለት አማኞች ማግባት ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ማግባት አለባቸው ማለት ነው። (ከላይ በተሰጡት ምክንያቶች) የጳውሎስ ምክር ሳያገቡ እንዲቆዩ ነው፤ ሆኖም ግን ውሳኔውን ለራሳቸው ትቶላቸዋል።

እግዚአብሔር በጋብቻ ዙሪያ «ግድግዳ» ያቆመው እስር ቤት ሊያደርገው ፈልጎ ሳይሆን አስተማማኝ ምሽግ እንዲሆን ነው። ጋብቻን እስር ቤት አድርጎ የሚያስብ ሰው ማግባት የለበትም። ሁለት ሰዎች በፍቅርና በደስታ እርስ በርስ ሲሰጣጡና ለጌታም ሲሰጡ የጋብቻ ሕይወት መተናነጫና መልሚያ ይሆናል። አብረው ያድጋሉ፥ ደግሞም እንደ አንድ «ቡድን» በቤታቸውና በቤተ ክርስቲያን ጌታን የማገልገልን ብልጽግና ያገኛሉ።

ይህን ምዕራፍ በምትከልስበት ጊዜ ጋብቻ ምን ያህል ጽኑ እንደሆነ ሳታደንቅ አታልፍም። የጳውሎስ ምክር ግልጽ የሚያደርገው እግዚአብሔር ጋብቻን አክብዶ እንደሚመለከትና ይህን ቃሉን ጥሰን ከኀጢ ጦስ እንደማናመልጥ ነው። ጳውሎስም ሆነ ኢየሱስ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ፍቺ እንደሚኖር ቢያመለክቱም፥ ይህ ለባለትዳሮች ፈጽሞ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ምርጫ አይሆንም። እግዚአብሔር መፋታትን ይጠላል (ሚል. 2፡14-16)። ስለዚህ ሁሉም የእርቅ ጎዳናዎች ታስሰው ሳያልቁ ማንም አማኝ በእውነቱ ፍቺን ማሰብ የለበትም።

ምንም እንኳ ፍቺ የገጠመው ሰው በመጋቢነት እና በድቁና ለማገልገል እቀባ ቢኖርበትም (1ኛ ጢሞ. 3፡2፥12)፥ በሌሎች አቅጣጫዎች ከማገልገል መከልከል የለበትም። ያወቅሁአቸው ከፍተኛ ሰው አጥማጆች ከመለወጣቸው አስቀድሞ በአሳዛኝ የፍቺ ሣንካ ያለፉ ሰዎች ናቸው። ሰው አገልግሎት እንዲኖረው የድቁና ወይም የመጋቢነት ሥራ ብቻ አይደለም የሚጠብቀው።

በማጠቃለያም፥ እያንዳንዱ ሰው ጋብቻን የሚያስብ ከሆነ፥ የሚከተሉትን ነጥቦች ራሱን መጠየቅ አለበት።

1. ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ ስጦታ ምንድን ነው?
2. የማገባው (የማገባት) አማኝ ነው (ናት)?
3. ጋብቻ እንዳደርግ ሁኔታዎች ይፈቅዳሉ?
4. ጋብቻ ለክርስቶስ የምሰጠውን አገልግሎት የሚነካው እንዴት ነው?
5. ወደዚህ ኅብረት ስገባ ዕድሜ ልክ ልቆይበት ተዘጋጅቻለሁን?

# 7

# ስለ ክርስቲያናዊ አርነት . . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 8፤10*

ስለ ጋብቻ ያነሷቸውን ጥያቄዎቻቸውን ከመለሰ በኋላ፥ ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በተላከው ደብዳቤ ውስጥ ከሚገኙት አንዱ ወደሆነው ጉዳይ፥ «ክርስቲያኖች ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ሊበሉ ይችላሉ?» ወደሚለው ፊቱን አዞረ። ያን ዓይነት ችግር ስለማናይ ይህ ጥያቄ በቀጥታ ለዛሬው አማኞች ብዙም ቁም ነገር ያለው አይመስልም። ነገር ግን ሰፋ ያለው «ክርስቲያናዊ አርነት» እኛንም ይመለከተናል፤ ምክንያቱም ጳውሎስ አይቶአቸው የማያውቃቸውን ጥያቄዎች እኛ ዛሬ እየተፋጠጥን ነው። ለክርስቲያን ቴአትር ማየት ትክክል ነውን? አማኝ በቤቱ ቴሌቪዥን ሊኖረው ይገባልን? ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፈው እስከ ምን ደረጃ ነው?

በምዕራፍ 8–10፥ ጳውሎስ በክርስቲያናዊ ሕይወት ዙሪያ «ጥያቄ ስለሚያስነሡ» ጉዳዮች ውሳኔ አወሳሰዱን በተመለከተ አማኞችን የሚመሩ አራት መሠረታዊ መርሆችን በሚገባ አብራርቶአል። እነዚህ አራት መርሆች የሚከተሉት ናቸው።

*እውቀት ከፍቅር ጋር መጣጣም አለበት (ምዕ. 8)።*

*ሥልጣን ከሥነ ሥርዓት እርምጃ ጋር መጣጣም አለበት (ምዕ. 9)።*

*ልምምድ ከጥንቃቄ ጋር መጣጣም አለበት (ምዕ. 10፡1–22)።*

*አርነት ከኃላፊነት ጋር መጣጣም አለበት (ምዕ. 10፡23–33)።*

ጳውሎስ በመጀመሪያ በቤተ ክርስቲያን ለሚገኙ ብርቱ ክርስቲያኖች፥ መንፈሳዊ እውቀትና ልምምድ ወደነበራቸውና በክርስቶስ ያላቸውን ሥልጣንና አርነት ወዳወቁት ፊቱን ሲመልስ መመልከት ትችላለህ። ለደካማው መጠንቀቅ ያለበት ብርቱው ነው (ሮሜ 14–15)።

ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ የሚነሣው ጥያቄ የተስተናገደው በምዕራፍ 8 እና 10 ስለሆነ፥ እኛም በዚሁ ምዕራፍ ላይ እንመረምረዋለን። በ 1ኛ ቆሮ. 9 ጳውሎስ ይህን ትክክለኛ የሥልጣን አጠቃቀምን መርህ

የገዛ ራሱን የገንዘብ አጠቃቀም መመሪያ አስደግፎ ይገልጸዋል፤ በመሆኑም በሚቀጥለው ጥናታችን ያንኑ እናጤናለን።

## እውቀት ከፍቅር ጋር መጣጣም አለበት (1ኛ ቆሮ. 8፡1–13)

በጥንቱ ዓለም የሥጋ ምንጮች ሁለት ነበሩ። ተለምዶአዊ ገበያ (ባለ ከፍተኛ ዋጋ) እና የአካባቢው ቤተ መቅደስ (የመሥዋዕት ሥጋ ሁልጊዜ የሚገኝበት)። የቤተ ክርስቲያኒቱ ብርቱ አባላት ጣዖታት ምግብን ለማርከስ እንደማይችሉ ያውቁ ስለነበር በቤተ መቅደስ የነበረውን ሥጋ በመሸመት ገንዘባቸውን ይቆጥቡ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ፥ ያላመኑ ወዳጆቻቸው የመሥዋዕት ሥጋ ወደሚቀርብበት በሚጋብዙአቸው ጊዜ በቤተ መቅደስም ይሁን በቤት ውስጥ ይበሉት ነበር።

ይህ ሁሉ ደካሞቹን ክርስቲያኖች አሳዘናቸው። ብዙዎቻቸው ድነው የወጡት ከሃይማኖት–የለሽ ሥርዓተ ጣዖት ስለነበር አማኝ ወዳጆቻቸው ለጣዖት ከተሠዋ ሥጋ ጋር ንክኪ እንዲኖራቸው ለምን እንደፈለጉ ሊገባቸው አልቻለም ነበር። (በሮሜ 14–15 ደካማ ክርስቲያኖች ሥጋንና የበዓላት ቀናትን በተመለከተ ችግር ነበረባቸው። ይሁንና ይህም ቢሆን ሥረ መሠረቱ ያው ነው።) በቤተ ክርስቲያን ክፍፍል አንዣብቦ ስለነበር መሪዎች ጳውሎስን ጠሩት።

ጳውሎስ ሦስት ዐበይት ነጥቦችን ወደ አትኩሮታቸው ስቦአል።

*እውቀት* (8፡1–6)። ቆሮንቶሳውያን በመንፈሳዊ እውቀት የበለጸጉ (1፡5) እና ይልቁንም በድሎቻቸው የሚመኩ ነበሩ። ጣዖት፥ በሚያመልኩት ሰዎች የጨለመ አእምሮ ውስጥ የሚገኝ የውሸት አምላክ አምሳል እንጂ ምንም እንዳልሆነ ያውቁ ነበር። በቤተ መቅደስ ውስጥ የጣዖቱ መገኘት አምላኩ ለመኖሩ በቂ ማረጋገጫ አይደለም። (በኋላ ጳውሎስ አምልኮተ ጣዖት አምልኮተ አጋንንት መሆኑን አመልክቶአል።) የሌለ አምላክ ለእርሱ በተዘጋጀው መሠዊያ የቀረበውን ምግብ ሊያረክስ አይችልም የሚለው ምክንያታዊ አቀራረባቸው ትክክል ነበር።

እስከዚህ ድረስ ሲታሰብ ብርቱዎች ክርስቲያኖች የግንባር ቀደምትነት ስፍራ አላቸው። አቋማቸው የሚያስኬድ ሆኖ ሳለ፥ ለምንድን ነው ደካሞች ክርስቲያኖች የተበሳጩባቸው? ለዚህ መልሱ ማንኛውም ችግር ሁልጊዜ በምክንያታዊ አቀራረብ መፈታት አለመቻሉ ነው። ጨለማውን የፈራ ሕፃን ልጅ ምክንያት ሲደረድሩለት ሊረጋጋ አይችልም፤ በተለይ አዋቂው (ታላቅ ወንድሙ) ለትላልቆች እንደሚደረግ ያለ አመለካከት ቢያንጸባርቅ የማያስኬድ ነገር ነው። እውቀት አጠቃቀምን መሠረት አድርጎ የጠብ ወይም የግንባታ

*መሣሪያ ሊሆን ይችላል።* «የሚያስታብይ» ከሆነ «ሊያንጽ» አይችልም።

ሁሉን አውቃለሁ የሚል አመለካከት ያለማወቅ ማረጋገጫ ነው። በትክክል እውነትን የሚያውቅ ሰው ምን ያህል እንደማያውቅ በጥልቀት ወደ መረዳት ብቻ ነው የሚደርሰው። ከዚህም በተጨማሪ፥ *ዶክትሪን* (አስተምህሮን) ማወቅ አንድ ነገር ሲሆን *እግዚአብሔርን* ማወቅ ግን ፈጽሞ ሌላ ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያደጉ ሆኖ፥ በጸጋ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር በግል ግንኙነት አለማደግ ይቻላል። መመዘኛው ጳውሎስ በሁለተኛ ደረጃ ያወሳው ፍቅር ነው።

*ፍቅር* (8:1–3)። ፍቅር እና እውቀት በአንድነት መሄድ አለባቸው፤ «እውነትን በፍቅር እየያዝን» (ኤፌ. 4:15)። «እውቀት ያለ ፍቅር ጭካኔ፥ ነገር ግን ፍቅር ያለ እውቀት ግብዝነት» መሆኑ በትክክል የተነገረ አባባል ነው። እውቀት ኃይል ስለሆነ በፍቅር መገራት አለበት። ነገር ግን ፍቅር ሁልጊዜ በእውቀት ቁጥጥር ሊደረግበት ያስፈልጋል (የጳውሎስን ጸሎት ከፊልጵ. 1:9–11 ተመልከት)። በቤተ ክርስቲያን የነበሩ ብርቱ ክርስቲያኖች እውቀት ነበራቸው፤ ነገር ግን እውቀታቸውን በፍቅር አይጠቀሙትም ነበር። ደካማ ቅዱሳንን በማነጽ ፈንታ፥ ራሳቸውን በትዕቢት ይወጥሩ ነበር።

የጳውሎስ ጭንቀት ደካማዎቹ ቅዱሳን ከደካማነታቸው ወጥተው ማደግ እንዲችሉ ብርቱዎቹ ቅዱሳን እንዲረዱአቸው ነበር። አንዳንድ ሰዎች *ብርቱ* ክርስቲያኖች በሕግጋትና በደንቦች የሚኖሩና ሌሎች በክርስቶስ ያላቸውን አርነት ሲጠቀሙ የሚኳዱበት ናቸው የሚል አሳብ አላቸው፤ ነገሩ ግን እንዲህ አይደለም። የሕግን ጥበቃ የሚፈልጉትና በክርስቶስ ያላቸውን አርነት ለመጠቀም የሚፈሩት ናቸው *ደካማ* ክርስቲያኖች። በብርቱ ክርስቲያኖች ላይ የሚፈርዱ ና የሚተቹ በሚያደርጉትም የሚደናቀፉት *ደካማ* ክርስቲያኖች ናቸው። በእርግጥ ብርቱዎች ቅዱሳን ለደካማዎቹ ወንድሞችና እኅቶች እንዳያገለግሉ ችግር የሚፈጥረው ይህ ነው።

እዚህ ላይ ነው ፍቅር መምጣት ያለበት፥ ምክንያቱም «ፍቅር ያንጻል»፥ ሌሎችንም ያስቀድማል። መንፈሳዊ እውቀት በፍቅር ሲጠቀሙት፥ ብርቱው ክርስቲያን ደካማው ክርስቲያን በክርስቶስ ያለውን አርነት እንዲደሰትበት እጁን ይዞ እንዲቆምና እንዲራመድ ለመርዳት ያስችለዋል። *ጨቅላ ክርስቲያኖችን በግድ በመመገብ ወደ ግዙፍነት ልንለውጣቸው አንችልም።* እውቀት ከፍቅር ጋር መቀየጥ አለበት፤ አለበለዚያ ቅዱሳኑ የሰፉ ልቦች ከመሆን ይልቅ «ትልልቅ ጭንቅላት» ሆነው ይቀራሉ። አንድ ታዋቂ ሰባኪ፥ «አንዳንድ

ክርስቲያኖች ያድጋሉ፤ ሌሎች ዝም ብለው ያብጣሉ» የሚል አነጋገር ነበረው።

እውቀትና ፍቅር ሁለት ጠቃሚ ነጥቦች ናቸው፤ ምክንያቱም ክርስቲያናዊ አርነታችንን በትክክለኛው መንገድ መጠቀም ካለብን እውቀት ከፍቅር ጋር መጣጣም አለበት። ይሁን እንጂ ሦስተኛም ነጥብ አለ።

ሕሊና (8፡7—13)። ሕሊና የሚለው ቃል በቀላል አነጋገር «ማወቂያ» ማለት ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ 32 ጊዜ በአገልግሎት ላይ ውሎአል። ሕሊና ድርጊቶቻችን ተመርምረው ትክክለኝነታቸው የሚጸናበት ወይም የሚኮነንበት የውስጥ ችሎት ነው (ሮሜ 2፡14—15)። ሕሊና ሕግ አይደለም፤ ለእግዚአብሔር የሥነ ምግባር ሕግ ምስክርነት የሚሰጥ እንጂ። ነገር ግን አስፈላጊው ነገር ይህ ነው። ሕሊና የሚደገፈው *በእውቀት ላይ ነው።* ብዙ መንፈሳዊ እውቀት ሲኖረንና ስንተገብረው ሕሊናችን ይጠነክራል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች በቅርቡ የዳኑ ስለሆነና ለማደግም ዕድል ስላልነበራቸው ደካማ ሕሊና አላቸው። በቤት ውስጥ እንዳሉ ሕፃናት በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው። ሌሎች ቅዱሳን ደካማ ሕሊና ያላቸው *ስለማያድጉ* ነው። መጽሐፍ ቅዱሳቸውንና ክርስቲያናዊ ኅብረትን ስለሚተዉ በሕፃንነት ደረጃ ላይ ይቀራሉ (1ኛ ቆሮ. 3፡1—4፤ ዕብ. 5፡11—14)። ይሁንና ሌሎች አማኞች ደካማ የሚሆኑት አርነትን ስለሚፈሩ ነው። ዕድሜው ለትምህርት ደርሶ ሳለ ቤቱን ትቶ መሄድ እንደፈራና በየቀኑ እናቱ ትምህርት ቤት እንደምታደርሰው ልጅ ናቸው።

የደካማ ክርስቲያን አእምሮ በቀላሉ ይረከሳል (ቁ. 7)፥ ይቆስላል (ቁ. 12)፥ ደግሞም ይጎዳል (ቁ. 13)። በዚህ ምክንያት፥ ብርቱዎቹ ቅዱሳን ለደካማዎቹ ቅዱሳን ተሸንፈው የሚጎዳቸውን ምንም ነገር ከማድረግ መታቀብ አለባቸው። ጣዖት በሚመለከበት ቤተ መቅደስ ማዕድ መካፈል ለብርቱው ክርስቲያን የሚጎዳው ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ደካማውን ወንድሙን ሊጎዳው ይችላል። ቁጥር 10 ጨቅላው አማኝ ብርቱውን ወንድሙን ለመኮረጅ ይወስንና ወደ ኃጢአት ሊገባ ይችላል በማለት ያስጠነቅቃል።

ብርቱው አማኝ ለደካማው አማኝ በፍቅር የሚሸነፍለት *እንዲጸና ለመርዳት ብቻ መሆኑን* ልብ ማለት አስፈላጊ ነው። ሊያንጸው፥ እንዲያድግ ሊረዳው ይፈልጋል እንጂ «እሽሩሩ አይለውም»። አለበለዚያ *ሁለቱም* ደካሞች ይሆናሉ።

በክርስቶስ ነፃ ነን፤ ነገር ግን መንፈሳዊ እውቀታችን በፍቅር የለዘበ እንዲሆን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፥ ደግሞም ደካማው ክርስቲያን ከሕሊና ውጭ እንዲወጣ ልንፈትነው አይገባም። እውቀት ከፍቅር ጋር በሚጣጣምበት ቦታ፥ ብርቱው ክርስቲያን ለደካማው ክርስቲያን አገልግሎት ይኖረዋል፥ እናም ደካማው ክርስቲያን አድጎ ብርቱ ይሆናል።

## ልምምድ ከጥንቃቄ ጋር መጣጣም አለበት (1ኛ ቆሮ. 10፡1–22)

ጳውሎስ በእምነታቸው ጠንካራ የነበሩ በልምድ የዳበሩ ክርስቲያኖች፥ ፈተናን ድል በማድረግ ችሎታቸውን ከሚገባው በላይ እንዳይተማመኑ ያሳስባቸዋል። «ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (ቁ. 12)። ጳውሎስ በሳል አማኞች ልምዳቸውን ከጥንቃቄ ጋር እንዲያጣጥሙ ሊያስጠነቅቅ የእስራኤልን ሕዝብ እንደ ምሳሌ ተጠቀመ። ለዚህም ሦስት ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥቶአል።

*በመጀመሪያ፥ ልዩ መብት ወይም ጥቅሞች ለስኬት ዋስትና እንዳልሆኑ አስጠነቀቀ (10፡1–4)።* ልክ እስራኤል በእግዚአብሔር ኃይል ከግብጽ አርነት እንደወጣች ሁሉ ክርስቲያን አማኝም ከኃጢአት አርነት ይወጣል። (በ5፡7–8፥ ጳውሎስ ቀደም ሲል ደኅንነትን ከፋሲካ ጋር አያይዞታል።) እስራኤል በቀይ ባሕሩ «ጥምቀት» ከሙሴ ጋር አንድ እንደሆነች ሁሉ፥ ቆሮንቶሳውያንም በክርስቲያናዊ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ። እስራኤላውያን ከሰማይ የመጣ መና እንደበሉ እና እግዚአብሔር የሰጠውን ውኃ እንደ ጠጡ ሁሉ፥ ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር የሚሰጠውን መንፈሳዊ ማዕድ ራሳቸውን ይመግባሉ (ዮሐ. 6፡63፥68፤ 7፡37–39)። ሆኖም እነዚህ ልዩ መብቶች እና ጥቅሞች አይሁድን በኃጢአት ከመውደቅ አልከለከሉአቸውም።

ለብስለትም ሆነ ላለመብሰል አደጋዎች አሉ። ከእነዚህም አንዱ ከሚገባው በላይ በራስ መተማመን ነው። ብርቱ የሆንን ሲመስለን ደካማ መሆናችንን እንደርስበታለን። በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚበላው ብርቱ አማኝ ከዓቅሙ እጅግ ከላቀ ጠላት ጋር ሲታገል ራሱን ያገኘዋል።

ምንም እንኳ አንዳንድ የአይሁድ ሃይማኖት አለቆች ቢያስተምሩትም፥ አይሁድ በምድረበዳ ጉዞአቸው እውነተኛ ድንጋይ ይዘው እንደዞሩ ጳውሎስ በቁጥር 4 ላይ አይጠቁምም። ያኔ ያስፈለጋቸውን ነገር ያቀረበላቸው መንፈሳዊው ድንጋይ፥ እርሱም ክርስቶስ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ከድንጋይ (ዘጸ. 17፡1–7፤ ዘኁ. 20፡7–

11) በሌሎች ጊዜያት ከጉድጓድ (ዘኍ. 21፡16–18) ውኃ ይወጣ ነበር። ውኃውን የሰጠው እግዚአብሔር ነው።

*ጳውሎስ ሁለተኛውን ማስጠንቀቂያ ሰጠ፡፡ መልካም ጅማሬዎች ለመልካም ፍጻሜ ዋስትና አይሰጡም (10፡5–12)፡፡* አይሁድ የእግዚአብሔርን ተአምራት የተለማመዱ ቢሆኑም፥ በምድረበዳ በተፈተኑበት ጊዜ ግን ተሸነፉ። ልምዱ ሁልጊዜ ከጥንቃቄ ጋር መጣጣም አለበት፥ ምክንያቱም በክርስቲያናዊ አካሄዳችን ከፈተና እና ከውድቀት አደጋ ነፃ ወደሚኮንበት ደረጃ ከቶውንም ልንደርስበት አንችልም። ኢያሱ እና ካሌብ ሲቀሩ 20 ዓመት እና ከዚያም በላይ የሆኑ ሁሉ፥ የሞቱት በመቅበዝበዝ ዘመናቸው በምድረበዳ ውስጥ ነው (ዘኍ. 14፡26)።

አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች «ያ ታሪያ ከእኛ ጋር ምን ግንኙነት አለው ሲሉ ልንሰማ እንችላለን። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አይሁዶች ከፈጸሙት ጋር አንድ ዓይነት ኃጢአቶችን የመፈጸም ተጠያቂነት እንዳለባት ጳውሎስ አመለከተ። ለክፉ ነገሮች ከነበራቸው ምኞት የተነሣ፥ ቆሮንቶሳውያን በዝሙት (ምዕ. 6)፥ በጣዖት አምልኮ (ምዕ. 8፡10) እና እግዚአብሔር ላይ በማንጎራጎር (2ኛ ቆሮ. 12፡20–21) ተጠያቂ ነበሩ። ልክ እንደ እስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ይፈታተኑትና እንዲሠራ «ያደፋፍሩት» ነበር።

ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ያለ ጥርጥር ያውቅ ነበር፥ አንባቢያኑም ደግሞ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ያውቁ ነበር። «ጉምጅት» በዘኍል. 11፡4፥ ጣዖትን ማምለክ በዘጸ. 32፥ እና ዝሙት በዘኍል. 25 ይገኛሉ። እስራኤላውያን ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ይፈታተኑት ነበር፥ ምናልባት ጳውሎስ በአእምሮው የያዘው ማጣቀሻ ዘኍል. 21፡4–6 ሊሆን ይችላል። ለማጉረምረማቸው ዘኍል. 14 እና 16ን ተመልከት።

ይህ ዓይነቱ ኃጢአት ከባድ ስለሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ የተገባው ነው። ከእነዚህ ዓመፀኞች አንዳንዶቹ ወዲያውኑ የሞቱ (1ኛ ቆሮ. 11፡29–31ን ተመልከት) ብቻ ሳይሆን፥ የተረፉትም የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ አልተፈቀደላቸውም። ከግብጽ የዳኑ ቢሆንም፥ ነገር ግን የበለጸገ ውርሳቸውን ለመቀዳጀት አልቻሉም። ጳውሎስ የሚታገለው አንባቢያኑ ደኅንነታቸውን እንዲያጡ ሳይሆን፥ ነገር ግን አንዳንዶቻቸው «የተጣሉ» (9፡27)፥ እግዚአብሔር የተዋቸው እና ምንም ዋጋ የማያገኙ እንዳይሆኑ ነው።

«የቅዱሳን ኃጢአት» በሚል ተከታታይ ስብከት ስለሰጠ አንድ መጋቢ ሰምቼ ነበር። ወቀሳው የተመለከታት ይመስላል፥ አንዲት የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል «ምንም ቢሆን እኮ በክርስቲያን ሕይወት የሚከሰት

ኃጢአት ባልዳነ ሰው ሕይወት ከሚከሰተው የተለየ ነው» በማለት መጋቢውን፥ ትምህርትህ ውድቅ ነው አለችው።

መጋቢውም በመመለስ፥ «አዎን የተለየ ነው፥ በክርስቲያን ሕይወት የሚከሰት ኃጢአት *የባሰ ነው!*» አላት።

አይሁድ በሕግ ቀንበር ሥር ስለነበሩ የእነርሱ ኃጢአት ከእኛ የተለየ በመሆኑ ከበድ ባለ ሁኔታ ይስተናገዳል ብለን ማሰብ የለብንም። በዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን ኃጢአት እጅግ የከፋ ነው፤ ምክንያቱም ትምህርት የሚሆነን የእስራኤል ምሳሌ በፊታችን ስላለን እና «በዘመን ፍጻሜ» ስለምንኖር ነው። በሕግ ላይ ኃጢአት መሥራት አንድ ነገር ነው፤ በጸጋ ላይ ኃጢአት መሥራት ግን በጣም የተለየ ነው።

*የጳውሎስ ሦስተኛ ማስጠንቀቂያ ቃሉን አጥብቀን ከፈለግን እግዚአብሔር ፈተናን እንድናሸንፍ ያስችለናል የሚል ነበር (10:13-22)።* እግዚአብሔር እንድንፈተን የሚፈቅደው ዓቅማችንን ስለሚያውቅም ነው፤ ደግሞም እርሱን የምንተማመን ከሆነና ፈተናውን በበጎ አመለካከት የምንቀበል ከሆነ ሁልጊዜም መውጫውን ያዘጋጅልናል። በራሱ ሊቆም እንደሚችል የሚያስብ አማኝ ይወድቃል፤ ከሚፈትን ነገር የሚርቅ አማኝ ግን መቆም ይችላል።

ጳውሎስ አንባቢያኑን ቀደም ሲል «ከዝሙት ሽሹ» ብሎ ነግሮአቸው ነበር (6:18)፤ የአሁኑ ማስጠንቀቂያው፥ «ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ» (10:14) የሚል ነው። ጣዖት በራሱ ምንም እንዳይደለ፥ ነገር ግን የሰይጣን መሣሪያ በመሆን ለምን ወደ ኃጢአት ሊመራህ እንደሚችል ምክንያቱን አብራራ። አምልኮተ ጣዖት አጋንንታዊ [ዘጸአ. 32:17፤ መዝ. (106):37] ነው። በጣዖት ማዕድ መቀመጥ ከአጋንንት ጋር ኅብረት (አንድነት፥ ተካፋይነት) ማድረግ ሊመስል ይችላል። ጳውሎስ ከኃጢአት የመለየትን ጠቃሚ ዶክትሪን እንደገና ያጸና ነበር (2ኛ ቆሮ 6:14-7:1)

የጌታን እራት እንደ ምሳሌ ተጠቅሞአል። በጌታ እራት ጊዜ አማኙ ከጽዋውና ከኅብስቱ በሚጋራበት ጊዜ፥ በመንፈሳዊ መንገድ፥ ከክርስቶስ ሥጋና ደም ጋር ኅብረት ማድረጉ ነው። የክርስቶስን ሞት በማስታወስ፥ አማኙ ከተነሣው ጌታ ጋር አንድነት ውስጥ ይገባል። በቁጥር 18፥ የቤተ መቅደስ መሠዊያንና መሥዋዕትን የዚህ እውነት ሌላኛው ምሳሌ አድርጎ ያቀርበዋል። ተዛምዶው ግልጽ ነው:- አንድ አማኝ ራሱን ለአደጋ ሳያጋልጥና ጌታን ሳያስቆጣ የጌታን ማዕድ (የብሉይ ኪዳኑ መሥዋዕት፥ የአዲስ ኪዳኑ እራት) ተካፋይ ሊሆን አይችልም።

«እኛስ ከእርሱ ይልቅ እንበረታለንን?» (ቁ. 22) የሚለው ሐረግ የተነጣጠረው ምንም ጉዳት ሳያገኘው በጣዖት አምላኪዎች ቤተ መቅደስ አርነቱን ሊደሰትበት እንደሚችል እርግጠኛ በሆነው ብርቱ ክርስቲያን ላይ ነው። «ከደካማው ወንድምህ የበረታህ ትሆን ይሆናል»፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የበረታህ አይደለህም!» በማለት ጳውሎስ እንደ ምሥጢር አድርጎ ተናገረ። በኃጢአት መጫወት እና እግዚአብሔርን መፈታተን አደገኛ ነው።

## አርነት ከኃላፊነት ጋር መጣጣም አለበት (1ኛ ቆሮ. 10:23–33)

በክርስቶስ ያለውን ልዩ መብትና ጥቅም እንዳይደሰትበት ጳውሎስ የበሳሉን ክርስቲያን አርነት የካደበት ጊዜ የለም። «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» – *ነገር ግን* ሁሉም የሚጠቅም አይደለም፥ ደግሞም አንዳንዶቹ ነገሮች ወደ ባርነት የሚወስዱ ናቸው (6:12)። ሁሉም ነገር ይጠቅማል»– *ነገር ግን* አንዳንዶቹ ድርጊቶች ደካማው ወንድምህ እንዲሰናከል ያደርጉታል (8:11–13)። በሌላ አነጋገር አርነታችንን ከኃላፊነት ጋር ስናጣጥም የብስለት ምልክት ነው፤ አለበለዚያ አርነት መሆኑ ይቀርና ሥርዓተ አልበኝነትና ሕገወጥነት ይሰፍናል።

ቀድሞ ነገር፥ በቤተ ክርስቲያን ላሉት ወገኖቻችን እኮ ኃላፊነት አለብን (ቁ. 23–30)። ሌሎችን በእምነት የመገንባት ና ጥቅማቸውንም የመፈለግ ኃላፊነት አለብን። ፊልጵስዩስ 2:1–4 አንድ ዓይነት ማስጠንቀቂያ–አዘል ምክር ይሰጠናል። በክርስቶስ አርነት ያለን ቢሆንም ሌላውን አማኝ ለመጉዳት ነፃ አይደለንም።

ጳውሎስ ይህን እውነት ሊመጣ ካለው ለጣዖት የተሰጠ ሥጋ ጥያቄ ጋር አዛመደው። አማኝ *በገሃድ* በጣዖት አምላኪዎች ማዕድ እንዳይሳተፍ ቀደም ሲል አስጠንቅቆአል (8:9–13)፥ በመሆኑም በዚህ ደረጃ የግል ማዕድን አስመልክቶ ተናገረ። ከቁጥር 25–26 ባለው፥ ለገዛ ቤታቸው አገልግሎት ከገበያ ስለተገዛ ሥጋ ጥያቄ እንዳያነሡ አማኞችን አዝዞአል። ቀድሞ ነገር፥ ሁሉም ነገር የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው [መዝ. (24):1ን ጠቀሰ] ደግሞም ሁሉም ምግብ ለአማኙ የተፈቀደ ነው (ማር. 7:14–23፤ የሐዋ. 10: 9–16፥ 28፤ 1ኛ ጢሞ. 4:3–5ን ተመልከት)። ብርቱው አማኝ ለጣዖት የታረደውን ሥጋ እንኳ በገዛ ቤቱ ሊበላው ይችላል። በመደበኛው ገበያ የተገዛው ሥጋ መጀመሪያ የተገኘበት ምንጭ ከቤተ መቅደስ ቢሆንም (ብዙውን ጊዜ ነው) እንኳ፥ አይጎዳበትም።

ነገር ግን አማኙ በማያምኑት ሰዎች ቤት እንግዳ በሚሆንባቸው ጊዜያትስ? ጳውሎስ ይህን ችግር ከቁጥር 27–30 አስተናግዶታል።

ክርስቲያኑ የፈለገውን ማድረግ ከተሰማው (ጳውሎስ ይህን ውሳኔ እንደ ትልቅ ነገር አልቆጠረውም) ከፊቱ የቀረበውን ማንኛውንም ነገር ጥያቄ ሳያነሣ መብላት አለበት። (ሉቃ. 10፡8፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡17ን ተመልከት።) ይሁን እንጂ፥ በግብዣው ላይ ለጣዖት የታረደ ሥጋ ለመብላት የማይፈልግና ሥጋውም ከዚህ ውጭ አለመሆኑን የደረሰበት፥ ከደካማ ወንድሞች ወይም እኅቶች አንዱ ተገኝቶ ይሆናል። ይህ ደካማ ቅዱስ ሰው ብርቱውን ክርስቲያን ይህ ሥጋ ለጣዖት የቀረበ ነው ቢለው፥ ያኔ ብርቱው ቅዱስ ሰው መብላት የለበትም። ከበላው፥ ደካማው አማኝ እንዲሰናከልና ምናልባትም ኃጢአት እንዲሠራ ሰበብ ይሆናል።

ጳውሎስ የሚከተለው ዓይነት ተቃውሞ እንደሚነሣ ከወዲሁ አይቶአል። «የማመሰግንበትን ምግብ የማልበላው ለምንድን ነው?» በሌላ ሰው ደካማ ሕሊና የተነሣ የእኔ አርነት የሚገደበው ለምንድን ነው?» ለእነዚህ የሚሰጠው ምላሽ በሁለተኛ ደረጃ የሚኖረንን ኃላፊነት ያስተዋውቃል። *ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር ለማድረግ ኃላፊነት አለብን* (ቁ. 31)። ሌላው ክርስቲያን እንዲሰናከል ሰበብ እየሆንን እግዚአብሔርን ልናከብር አንችልም። በአንዳንድ ተግባራት ሳንሳተፍ ተካፋይ እስከምንሆን ድረስ ሕሊናችን ብርቱ ሊሆን እንደሚችል እርግጠኞች ነን። ነገር ግን በክርስቶስ ያገኘነውን አርነት ክርስቲያን ወገናችንን ሊጎዳ በሚችል በምንም ዓይነት መንገድ መጠቀም የለብንም።

ይሁንና፥ ከመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጋር የሚተሳሰር ሦስተኛ ኃላፊነት አለ። *የጠፋውን ለመመለስ የመፈለግ ኃላፊነት አለብን* (ቁ. 32-33)። አይሁድ ወይም አሕዛብ ጌታን እንዳያምኑ ወይም ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ለጌታ እንዳይመሰክሩ ችግር መፍጠር የለብንም። የገዛ ጥቅማችንን ብቻ ለመፈለግ ሳይሆን፥ ነገር ግን ይድኑ ዘንድ የሌሎችንም ጥቅም መሻት አለብን።

ጳውሎስ፥ «በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ» ብሎ ሲጽፍ (ቁ. 33)፥ አቋሙን የሚያደራድር አድር ባይ ወይም ሰውን ለማስደሰት የቆመ መሆኑን ማመልከቱ አልነበረም (ገላ. 1፡10ን ተመልከት)። ሕይወቱ እና አገልግሎቱ ራሱን እና ፍላጎቶቹን ለማራመድ ሳይሆን ሌሎችን ለመርዳት የቆሙ የመሆናቸውን እውነት እያጸና ነበር።

ይህን ጠቃሚ ክፍል ከመሰናበታችን በፊት፥ ጳውሎስ ክርስቲያናዊ የአኗኗር መርሁን ላልተገነዘቡት ምናልባት ተለዋዋጭ መስሎ ሳይታይ እንዳልቀረ ልብ ልንል ይገባል። አንዳንድ ጊዜ አሕዛብ የሚበሉትን

ይበላ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ፥ ከአይሁድ ጋር «ኮሸር» ምግብ ይመገብ ነበር። ተለዋዋጭ ከመሆን ይልቅ፥ በእነዚህ ምዕራፎች ባስቀመጣቸው መርሆች መሠረት በአንድ አቋም ይኖር ነበር። የአየር ሁኔታ አመልካች ቀስት አንዴ በአንድ አቅጣጫ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ሲያመለከት የሚለዋወጥ ይመስላል። ሆኖም የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያው ቀስት ሁልጊዜ ጽኑ ነው። ሁልጊዜ የሚያመለክተው ነፋስ ወደሚነፍስበት አቅጣጫ ነው። ጠቃሚ መሣሪያ የሚያደርገውም ይኸው ነው።

ብርቱው ክርስቲያን በአደባባይ የማያደርገው ሆኖ በቤቱ ውስጥ በግሉ የሚያደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ ወይ? አዎን፥ እርሱን የማይጎዳና እርሱም ጌታውን የማይፈታተንበት እስከሆነ ድረስ። ልጆቻቸው ትንንሾች ሳሉ፥ ካርታ የመሳሰሉ መጫዎቻዎችን ከቤታቸው ያራቁ ባልና ሚስትን አውቃለሁ። በኋላ ልጆቻቸው ወደ እውቀት ዕድሜ ሲደርሱ፥ እነዚያኑ መጫዎቻዎች እንዲጫወቱባቸው ፈቀዱላቸው።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን አርነት አለን። ይህ አርነት ለእኛ የተገዛው በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ በጣም ውድ ነው። አርነት የሚመጣው ከእውቀት ነው «እውነትን ታውቃላችሁ፥ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐ. 8፡32)። ለምሳሌ ስለ አቶም ባወቅን መጠን በብልሃት ለመጠቀም የበለጠ አርነት ይኖረናል። ሆኖም ግን፥ እውቀት ከፍቅር ጋር መጣጣም አለበት፤ አለበለዚያ ያፈራርሳል እንጂ አይገነባም።

ብርቱው ክርስቲያን እውቀት ብቻ ሳይሆን ልምድም አለው። ወደኋላው፥ ወዳለፉት ዓመታት ዘወር ብሎ እግዚአብሔር እንዴት ከእርሱ ጋር እንደተገናኘ ማየት ይችላል። ነገር ግን ልምድ ከጥንቃቄ ጋር መጣጣም ስላለበት መጠንቀቅ አለበት። ተጠንቀቅ አለበለዚያ ትወድቃለህ!

ብርቱው ክርስቲያን ይህ አርነት እንዳለው ያውቃል፤ ነገር ግን አርነት ኃላፊነትንም እንደሚያካትት ይገነዘባል። ለምሳሌ፥ መኪናዬን ከጋራዤ አውጥቼ በአውራ ጎዳናው ላይ የመንዳት ነጻነት አለኝ፤ *ነገር ግን ኃላፊነት በተሞላው መንገድ መንዳት አለብኝ።* በተፈቀደልኝ መስመር በፈለግሁት ፍጥነት መንዳት አልችልም፤ በመንገዱ ያሉትንም የትራፊክ ምልክቶች ችላ ልላቸው አልችልም።

ከእነዚህ ምዕራፎች ለግል ውሳኔዎቻችንና ተግባሮቻችን የሚሆኑ በርካታ መመዘኛዎች ይመነጫሉ።

«ሁሉም ነገሮች የተፈቀዱ ናቸው፥» ነገር ግን–

1. የሚመሩት ወደ አርነት ወይስ ባርነት? (6፡12)
2. የሚሆኑልኝ የመሰናከያ ድንጋይ ነው ወይስ የመረማመጃ ደረጃ? (8፡13)
3. ያንጹኛል ወይስ ያፈራርሱኛል? (10፡23)
4. እኔን ብቻ የሚያስደስቱኝ ናቸው ወይስ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ናቸው? (10፡31)
5. ያልዳኑት ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ ይረዳሉ ወይስ ያርቁአቸዋል? (10፡33)

የአርነት አጠቃቀማችንና ለሌሎችም የምናዛምድበት አካሄዳችን በክርስቶስ ያደግን ወይም ያላደግን መሆናችንን ያሳያል። ብርቱ ና ደካማ ክርስቲያኖች አንዱ ሌላውን ለማነጽና ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስከበር በፍቅር በአንድነት መሥራት አለባቸው።

# 8

# ስለ ግላዊ ቀዳማዊ ጉዳዮች. . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 9*

ይህ ምዕራፍ ስለ ጳውሎስ የገንዘብ እርዳታ መመሪያ የሚያወሳ ሲሆን፥ «ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ» በሚናገርበት በዚህ ስፍራ መቅረቡ ጣልቃ የገባ ነገር ሊመስል ይችላል። እውነቱ ግን፥ ጣልቃ ሳይሆን በምዕራፍ 8 እና 10 ለሚያቀርባቸው መርሆዎች መግለጫ ነው። ጳውሎስ የበሰለ የእርነት አጠቃቀምን ለመግለጽ ራሱን በምሳሌነት ተጠቅሞአል፡- ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ድጋፍን ለመጠቀም መብት ነበረው፤ ሆኖም ግን የላቀ ግብ ላይ ለመድረስ ሲል ያን መብቱን ወደ ጎን አስቀመጠ።

በአብዛኛው ግሪኮች የጉልበት ሥራን እንደሚንቁ ልብ በል። የግሪክ ዜጎች የጉልበት ሥራ የሚሠሩላቸው ባሪያዎች ስለነበሩአቸው፥ በስፖርት፥ በፍልስፍና ና በመዝናኛዎች ይደሰቱ ነበር። አይሁድ በእርግጥ ጥሩ ገቢ እስካስገኘ ድረስ ሥራን ያከብሩ ነበር። የተማሩ የሃይማኖት መሪዎቻቸውም (ራቢዎች) እንኳ ሳይቀሩ ንግድን ይለማመዱ እና «ልጁን እንዲሠራ የማያስተምር፥ ሌባ እንዲሆን ያስተምረዋል» በማለት ትምህርት ይሰጡ ነበር። ጳውሎስ የድንኳን ሥራን ና የቆዳ ሥራን ጥበብ የተማረ ነበር።

ክርስቲያናዊ የግል መብት አጠቃቀም በምሳሌ ለመግለጽ፥ ጳውሎሱ እንደ ክርስቶስ አገልጋይነቱ ስለሚከተለው ባለ ሁለት ገጽታ የገንዘብ ፖሊሲው መከላከያን አቀረበ።

## ድጋፍ ለመቀበል መብቱ መከላከያን አቀረበ (1ኛ ቆሮ. 9፡1-14)

በዚህ ምዕራፍ አጋማሽ ላይ፥ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብት እንደነበረው አረጋገጠ። ይህን አሳቡን ለመደገፍ አምስት መከራከሪያ ነጥቦችን አስቀምጧል።

*ሐዋርያነቱ (9፡1-6)።* *ሐዋርያ* ማለት «በሹመት የተላከ» ማለት ሲሆን በቀዳሚነት የሚያመለክተው አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት እና ጳውሎስን ነው። እነዚህ ሰዎች ከአዲስ ኪዳን ነቢያት ጋር የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ለመጣል (ኤፌ. 2፡20) ልዩ ተልዕኮ ነበራቸው።

ሐዋርያ የመሆን አንዱ መመዘኛ የተነሣውን ክርስቶስ በግል ማየት ነበር (የሐዋ. 1፡21–22)። ጳውሎስ ጌታን ያየው ክርስቲያኖችን ለማሰር ወደ ደማስቆ በሚሄድበት ወቅት ነበር (የሐዋ. 9፡1–9)። ሐዋርያት የክርስቶስ ትንሣኤ ምስክሮች ነበሩ (የሐዋ. 2፡32፤ 3፡15፤ 5፡32፤ 10፡39–43)።

የሰበኩትን መልእክት ለማስረገጥ ሐዋርያት ተአምራትንና ድንቆችን የመሥራት ልዩ ችሎታ ተሰጥቶአቸው ነበር (ዕብ. 2፡4)። ጳውሎስ እንዲህ ያሉ ተአምራቶችን በቆሮንቶስ አገልግሎቱ (2ኛ ቆሮ. 12፡12) ፈጽሞአል። እንዲያውም፥ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን በጣም ልዩ የሆነች የአገልግሎቱ «ማኅተም» (ማረጋገጫ) አድርጎ ቆጥሮአት ነበር። ቆሮንቶስ ለማገልገል በጣም አስቸጋሪ ከተማ ብትሆንም፥ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ኃይል ታላቅ ሥራ ሠርቶአል (የሐዋ. 18፡1–17ን ተመልከት)።

በመሆኑም፥ እንደ አንድ ሐዋርያ ጳውሎስ ካገለገላቸው ሰዎች ድጋፍ የማግኘት ኃይል ነበረው። (በዚህ ምዕራፍ ኃይል የሚል ቃል በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶአል፤ ይህም «ሥልጣን» ማለት ነው)። ሐዋርያው የክርስቶስ ወኪል ነበር፤ ስለሆነም ሊስተናገድ ና ክብካቤ ሊደረግለት የተገባው ነበር። ጳውሎስ ያላገባ ሰው ነበር፤ ነገር ግን ሚስት ኖሮት ቢሆን ኖሮ፥ እርሷም በቤተ ክርስቲያን የመረዳት መብት ይኖራት ነበር። ጴጥሮስ ያገባ ሰው ነበረ (ማር. 1፡30)፥ እናም ሚስቱ ከእርሱ ጋር ትጓዝ ነበር። ጳውሎስም ይኸው መብት የነበረው ሲሆን አልተጠቀመበትም።

ጳውሎስ ሙሉ ጊዜውን ለቃሉ አገልግሎት የመመደብ መብትም ነበረው። ድንኳን መሥራት አልነበረበትም። ሌሎች ሐዋርያት ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ለቃሉ አገልግሎት ስለ ሰጡ ራሳቸውን ለመደገፍ መሥራት አልነበረባቸውም። ይሁን እንጂ፥ ጳውሎስ ና በርናባስ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ከእነርሱም ጋር አብረው የሚደከሙትን ለመደገፍ በገዛ እጆቻቸው ይሠሩ ነበር።

*ሰብአዊ ልምምድ (9፡7)።* አንድ ሠራተኛ ለሥራው የሆነ ጥቅም ማግኘት እንዳለበት የየዕለቱ ልምምድ ያስተምረናል። አንድ ሰው ለውትድርና ከተመለመለ፥ መንግሥት ደመወዙን ይከፍለዋል፤ የተወሰኑ አቅርቦቶችንም ይሰጠዋል። እረኛ ወይም አርቢ ከእንስሳቱ ወተታቸውን የመጠቀም መብት እንዳለው ሁሉ፥ ወይን የሚተክል ሰውም ፍሬውን መብላት አለበት።

ምናልባት ጳውሎስ በ«አእምሮው ጓዳ» ውስጥ፥ ቤተ ክርስቲያንን ከጦር ሠራዊት፥ ከወይን እርሻ ና ከመንጋ ጋር ያነጻጸረ ይመስላል።

ለዋርያ እንደ መሆኑ መጠን ጳውሎስ በጦር ሜዳው ግንባር መስመር ላይ ነበር። ቀደም ብሎ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን ከለማ ማሣ (3፡6-9) አነጻጽሮ ነበር። ጌታም ራሱ የወይን ግንድንና ቅርንጫፍን ምሳሌ (ዮሐ. 15)፥ እንደዚሁም የመንጋን ምሳሌ (ዮሐ. 10) ተጠቅሞአል። ትምህርቱ ግልጽ ነበር። ክርስቲያን ሠራተኛ ለሥራው ጥቅምን የመጠበቅ መብት አለው። ይህ በ«ግላዊው» ዓለም እውነት ከሆነ በመንፈሳዊው ዓለምም እውነት ነው።

*የብሉይ ኪዳን ሕግ (9፡8-12)*። ብሉይ ኪዳን የጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን «መጽሐፍ ቅዱስ» ነበር፤ ምክንያቱም አዲስ ኪዳን ገና በመጻፍ ሂደት ላይ ነበር። ምንም እንኳ የሕግን ትእዛዛት ከመታዘዝ ነፃ የወጡ ቢሆኑም የመጀመሪያዎቹ አማኞች በሕግጋቱ መንፈሳዊ መርሆች ይመሩ ነበር። ቅዱስ አውግስቲን እንዲህ ብለዋል፥ «አዲስ በብሉይ ውስጥ የተደበቀ፥ ብሉይ በአዲስ የተገለጠ ነው»።

ጳውሎስ አሳቡን ለማስረገጥ ዘዳግም 25፡4ን ጠቀሰ። (ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ ና ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮቿን በበቂ ሁኔታ ደመወዝ እንድትከፍል ባበረታታበት ወቅት ይኸንኑ ነው የጠቀሰው፥ 1ኛ ጢሞ. 5፡17-18።) በሬዎች ስለማያነብቡ ይህ ጥቅስ የተጻፈው ለእነርሱ አይደለም። ገበሬ የበሬዎቹን አፍ በማሰር በፊታቸው ካለው እህል እንዳይበሉ ቢያደርግ ጭካኔ ነው። እንደ እውነቱማ ሥራውን እኮ የሚሠራው በሬው ነው።

ጳውሎስ ለሠራተኛው ደመወዙ ይገባዋልና በሚለው ትእዛዝ ውስጥ በትክክል መንፈሳዊ መርህን አይቶአል። መሬቱን ለዘሪ ያዘጋጀው በሬ አሁን ደግሞ የተመረተውን ምርት በእግሩ እየረገጠ ነበር። ጳውሎስ የቆሮንቶስን አፈር አርሶአል፤ ሌት ተቀንም ደክሞአል። ከዘራው ዘር የተገኘውን መከርም አይቶአል። ከዚያ መከር አንዳንዶቹን ፍሬዎች መጠቀም መብቱ ነበር።

ቁጥር 11 የክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረታዊ መርህን በግልጽ ያስቀምጣል። *መንፈሳዊ* በረከቶችን ከተቀበልን በምላሹ *ቁሳዊ* በረከቶችን ማካፈል ይገባናል። ለምሳሌ፥ አይሁድ ለአሕዛብ መንፈሳዊ በረከትን ይሰጡ ነበር፤ በመሆኑም አሕዛብ ቁሳዊ በረከቶችን ለአይሁድ የማካፈል ግዴታ ነበረባቸው (ሮሜ 15፡25-27)። ቃሉን የሚያስተምሩን እንድንደግፋቸው ከእኛ ሊጠብቁ መብት አላቸው (ገላ. 6፡6-10)።

ጳውሎስ ከሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች የገንዘብ ድጋፍ መቀበሉን ለማመን ምክንያት አለን። ወደ ተሰሎንቄ በሄደ ጊዜ የፊልጵስዩስ አማኞች ሁለት ስጦታዎችን ልከውለት ነበር (ፊልጵ. 4፡15-16)። «እናንተን ለማገልገል ደመወዝ እየተቀበልሁ ሌሎችን አብያተ

ክርስቲያናት ዘረፍሁ» (2ኛ ቆሮ. 11:8) በማለት ጳውሎስ ቆሮንቶሳውያንን አሳሰበ። ሌሎች አገልጋዮች ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ የተቀበሉ ይመስላል (1ኛ ቆሮ. 9:12)፤ ነገር ግን ጳውሎስ «የክርስቶስን ወንጌል እንዳንከለክል» በማለት ከዚህ ዓይነት ድጋፍ እራሱን ነፃ አድርጎ መቆየትን መረጠ። ለሌሎች አማኞች የላቀ ምሳሌ ለመሆን ፈለገ (2ኛ ተሰ. 3:6-9)።

*የብሉይ ኪዳን ልምምድ (9:13)።* ካህናት ና ሌዋውያን የሚኖሩት ወደ ቤተ መቅደስ በሚመጣው መሥዋዕት እና ስጦታዎች ነበር። የሚቀበሉአቸውን ስጦታዎች እና ልዩ አሥራቶችን በተመለከተ የወጡት ደንቦች በዘኁልቁ 18:8-32፥ በዘሌዋውያን 6:14-7:36፥ እና 27:6-33 ላይ ይገኛሉ። የዚህ ተዛምዶ ግልጽ ነው። በሕግ ሥር የነበሩ የብሉይ ኪዳን አገልጋዮች በሚያገለግሉት ሕዝብ ይደገፉ ከነበረ፥ በጸጋ ሥር ሆነው የሚያገለግሉ የእግዚአብሔር ባሪያዎችስ መደገፍ የለባቸውምን?

*የኢየሱስ ትምህርት (9:14)።* ጳውሎስ ያጣቅስ የነበረው በሉቃስ 10:7-8 እና በማቴዎስ 10:10 ላይ ያሉትን የጌታ ቃላት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ቆሮንቶሳውያን የሚያጣቅሱባቸው ከሁለቱ ወንጌሎች የየትኛውም ቅጂ አልነበራቸውም። ነገር ግን የጌታ ትምህርት በሐዋርያት ይተላለፉ የነበረው አፍአዊ ትውፊት አካል በመሆን ተሰጥቶአቸው ነበር። ቤተክርስቲያን ችላ ልትለው የማይገባት መሠረታዊ መርህ ***ሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል*** የሚል ነው።

ጳውሎስ ያለጥርጥር አሳቡን አስመስክሮአል። አምስቱ መከራከሪያዎቹ በማጠቃለያ የሚያረጋግጡት አብሮአቸው በነበረበት ወቅት በአገልግሎቱ ይደግፉት ዘንድ ከቆሮንቶስ አማኞች መጠበቅ መብቱ እንደሆነ ነው። እንዲሁም ሆኖ ድጋፋቸውን ሆን ብሎ ሳይቀበል ቀረ። ለምን? ይህንን በመከላከያው ሁለተኛ ክፍል ላይ ያብራራል።

## ድጋፍን ያለመቀበል መብቱን ተከላከለ (1ኛ ቆሮ. 9:15-27)

ጳውሎስ ቁሳዊ ድጋፍን የመቀበል ሥልጣን (መብት) ነበረው፤ ነገር ግን እንደ አንድ በሳል ክርስቲያን ሥልጣኑን ከሥነ ሥርዓት ጋር አጣጣመው። በክርስቶስ የነበረውን አርነት የመተው መብት አልነበረውም፤ ነገር ግን መብቶቹን የመተው አርነት ነበረው። አሁን ለምን እንደዚህ እንደጻፈ ይገባናል። ለቆሮንቶስ አማኞች ስለሚጽፋቸው መርሆች ሕያው ምሳሌ ለመስጠት ነበር። በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ብርቱ አማኞች ለደካሞች ቅዱሳን ሲሉ

መብቶቻቸውን ወደ ጎን መተው አይገባቸውምን? ሥጋን መብላት ቤተ ክርስቲያንን ከማነጽ የበለጠ ተፈላጊ ነበርን?

ጳውሎስ ይናገር የነበረው በሕይወታችን በእርግጥ አስፈላጊ ናቸው ስለምንላቸው *ተቀዳሚ ጉዳዮች ነው።* አንዳንድ ክርስቲያኖች ግላዊ ቀዳሚ ጉዳዮቻቸው ስለሚምታቱባቸው የክርስቶስን *ሥራ* ሲያውኩ ማየት የሚያሳዝን ነው። እያንዳንዱ ማቴዎስ 6:33ን የሚለማመድ ቢሆን ኖሮ፥ ለወንጌል መልእክተኞች በርካታ ገንዘብ፥ በአገልግሎት በርካታ የሰው ኃይል በተገኘ ና የጌታ *ሥራም* በሰፋ ነበር። ነገር ግን ማቴ 6:33ን የሚለማመድ ሁሉም ክርስቲያን አይደለም።

አንዲት ሴት በቤቷ ያለውን የኤሌትሪክ ውኃ ማሞቂያ በመዝጋት ለዚህ የምታወጣውን ገንዘብ አጠራቅማ ለአገልግሎት ስጦታ አድርጋ ላከች። የጌታን *ሥራ* የበለጠ መርዳት እንድትችልም ዕለታዊ ጋዜጣ መግዛትን አቆመች። ገላዋን ለመታጠብ ስትፈልግ ውኃውን በምድጃ ላይ ታሞቅ ነበር። ጌታ ሁላችንንም ለዚህ ዓይነት መሥዋዕትነት ላይጠራን ቢችልም የእርሷ ምሳሌ ክቡር ነው!

ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ለምን እንዳልተቀበለ የሚያብራሩ ሦስት ምክንያቶችን ሰጠ።

*ለወንጌል ሲባል* (9:15–18)። ጳውሎስ «የክርስቶስን ወንጌል ለመከልከል» አልፈለገም ነበር (ቁ. 12)። በዚያን ዘመን የግሪክ ከተሞች ገንዘብ ለማፍራት ብለው ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በሚያስተምሩ ና በሚሰብኩ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች የተሞሉ ነበሩ። ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች ይጠቀሙ የነበሩትን ዓይነት ንግግር ና ክርክር (2:1–5) ለመጠቀም አሻፈረኝ ማለቱ ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ካገለገላቸው ገንዘብ መቀበልንም እምቢ አለ። የወንጌሉ መልእክት ለጠፉ ኃጢአተኞች አእምሮ ከማንኛውም ዓይነት መሰናክልና እንቅፋት ነፃ እንዲሆን ፈለገ።

ለዚያውም፥ ጳውሎስ «እንዲህ እንዲሆንልኝ ይህን አልጻፍሁም» (9:15) ሲል እርሱን መደገፍ ይገባቸው እንደነበር «መጠቆሙን» አንባቢያኑ አሳቡን አላገኙትም ነበር!

ጳውሎስ ወንጌልን ለመስበክ ከእግዚአብሔር የተጠራ ስለነበር ለአገልግሎቱ ምንም ዓይነት ዋጋን አለኝታ አላደረገም ነበር። «ግድ ደርሶብኛ ነው እና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ!» (ቁ. 16) እግዚአብሔር የመለኮታዊ መጋቢነትን «ልዩ ፈቃድ» ሰጥቶት ነበር። ደግሞም «በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል» (1ኛ ቆሮ. 4:2)። የጳውሎስ ደመወዝ ጉዳይ በእግዚአብሔር ኃላፊነት ሥር

ነበር («ዋጋ»–በሉቃስ 10:7 ደመወዝ ተብሎ ከተተረጎመው ጋር አንድ ቃል ነው)።

የጳውሎስ ዋጋ ምን ነበር? ወንጌልን ያለ ክፍያ የመስበክ ሐሴት! ይህም ማለት የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች በሚያካፍልበት ጊዜ፥ ሽረኛ አቋመ ልቡና ወይም ዘዴ አለው ብሎ ሊከስስ የሚችል ማንም አልነበረም ማለት ነው።

ለገንዘብ ከመጠን ያለፈ አጽንኦት ከመስጠቱ የተነሣ አንዳንዴ የወንጌል አገልግሎት መደናቀፍ አሳዛኝ ክስተት ነው። ያልዳነው ዓለም፥ አብዛኞቹን ሰባኪያን ና ሚሲዮናውያንን፥ ከየዋህ ሰዎች ገንዘብን በመሰብሰብ «ሃይማኖታዊ ምዝበራ» ለማካሄድ እንደተሰለፉ አድርጎ ያምንበታል። ሃይማኖታዊ «ንዋየ መዝባሪዎች» ዛሬም በዓለም መኖራቸው ጥርጥር የለውም (1ኛ ጢሞ. 6:3–16)፥ እነዚህ ሃይማኖትን ሌሎችን ለመበዝበዣ ና ለመቆጣጠሪያ «የሚጠቀሙ» ናቸው። እኛ በእርግጥ ከእነዚህ ዓይነቶቹ በዓላማም ሆነ በተግባር አንስማማም። በገዛ አገልግሎቶቻችን የምናደርገው ምንም ነገር ከእነርሱ ጋር የሚያስፈርጀንን ገጽታ እንደማያንጸባርቅ እርግጠኞች መሆን አለብን።

በገንዘብ ላይ የሚደረግ የተሳሳተ አመለካከት ከጥንት የቤተ ክርስቲያን ዘመናት አንሥቶ እስካሁን ድረስ ለወንጌል ዕንቅፋት ሆኖአል። ሐናኒያ ና ሰጲራ እውነትን ከሚወዱት በላይ ገንዘብን ስለወደዱ፥ እግዚአብሔር ቀሰፋቸው (የሐዋ. 5)። ጠንቋዩ ሲሞን የመንፈስ ስጦታን ገንዘብ የሚገዛ መሰለው (የሐዋ. 8:18–24)። ስሙ ዛሬ በእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተካትቶአል። ሲሞኒ (simony) የሃይማኖት ሹመቶችን እና ጥቅሞችን የመግዛት እና የመሸጥ ተግባር ነው።

ዶክተር ኤች. ኤ. አይረንሳይድ ለ 18 ፍሬያማ ዓመታት በቺካጎ የሙዲ ቤተ ክርስቲያንን በመጋቢነት አገልግለዋል። መባ እንዲሰበሰብ ሲያውጁ ስሰማ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፥ አሁን ሁኔታውን አስታውሰዋለሁ። እንዲህ አሉ፥ «የእግዚአብሔር ሕዝብ በልግሥና እንዲሰጥ እንጠይቃለን። በኢየሱስ ክርስቶስ የማታምን ከሆነ እንድትሰጥ አንጠይቅህም። እኛ ለአንተ ስጦታ አለን–ይኸውም በክርስቶስ በኩል የሚገኝ የዘላለም ሕይወት ነው!» መባ መስጠት ለአማኞች መሆኑን በግልጽ አሳወቁ፤ ይህም በጉባኤው የነበሩ ሰዎች በገንዘብ ምክንያት ተሰናክለው ወንጌልን እንዳይተዉት ነው።

*ለኃጢአተኞች ሲባል* (9:19–23)። ምንኛ የሚጋጭ ነገር ነው። ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆን፥ ለሰው ሁሉ ባሪያ ነኝ! ስለ

ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን» (2ኛ ቆሮ. 4:5)። እርነት የወጣ ስለነበር፥ ጳውሎስ ሌሎችን ለማገልገል ና ስለ እነርሱ ሲል መብቱን ለመተው ቻለ።

«ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ» (ቁ. 22) የሚለው ሐረግ ጳውሎስ ለማለት ከፈለገው ውጭ ና ያለ አግባብ በዓለም ጥቅም ላይ ሲውል መታየቱ አሳዛኝ ነገር ነው። ጳውሎስ መልእክቱን ና ዘዴዎቹን ከእያንዳንዱ አዲስ ሁኔታ ጋር የሚቀያይር እስስት አልነበረም። አድማጮቹን ለማስደሰት ሲል መልእክቱን የሚያመቻምች አድርባይም አልነበረም። አምባሳደር እንጂ ፖለቲከኛም አልነበረም!

ጳውሎስ ለራሱ ሕዝብ ታላቅ ሸክም የነበረው አይሁዳዊ ነው (ሮሜ 9:1–3፤ 10:1)። ነገር ግን የእርሱ ልዩ ጥሪ አሕዛብን ማገልገል ሆነ (ኤፌ. 3:8)። ወደ ከተማ በሄደ ቁጥር (ሁልጊዜም ወንጌል ወዳልተሰበከበት ይሄድ ነበር– ሮሜ 15:20)፥ ምኵራብ በአካባቢው ካለ በቀጥታ ወደዚያው ያመራና በድፍረት ወንጌልን ያካፍል ነበር። አይሁዶች የማይቀበሉት ከሆነ ወደ አሕዛብ ፊቱን ያዞር ነበር።

በዚያን ዘመን አይሁዶችን ና አሕዛብን የሚለያየው ምን ነበር? ሕግ ና ቃል ኪዳን ናቸው (ኤፌ. 2:11–15)። በግል ሕይወቱ ጳውሎስ አይሁድንም ሆነ አሕዛብን ሳያስቀይም ኖሮአል። እርነቱን በአይሁድ ፊት ለታይታ አላሽሞነሞነውም፤ በአሕዛብ ላይም ሕግን አልጫነም።

ጳውሎስ አቋሙን የመቀያየር ባሕርይ ነበረውን? ለተለያዩ ቡድኖች በሚስማማ ሁኔታ አቀራረቡን አስተካከለ እንጂ በእርግጥ እንዲህ ያለ ባሕርይ አልነበረውም። በሐዋርያት ሥራ ስብከቶቹን በምታነብበት ጊዜ ይህን ከሁኔታዎች ጋር የማጣጣም ብልህ ስልቱን ታያለህ። ለአይሁድ በሚሰብክበት ጊዜ፥ በብሉይ ኪዳን አባቶች ይጀምራል፤ ነገር ግን ለአሕዛብ በሚሰበክበት ጊዜ፥ በፍጥረት አምላክ ይጀምራል። ጳውሎስ ሁኔታዎችን ሳያገናዝብ ሁልጊዜ የሚጠቀምበት አንድ የተወሰነ ስብከት አልነበረውም።

ጌታችንም የነበረው አቀራረብ ይኸው እንደነበረ ማስታወሱ ጠቃሚ ነው። ከከበረ ሐረግ ለተመዘዘው አይሁዱ ኒቆዲሞስ፥ ስለ መንፈሳዊ ልደት አወሳለት (ዮሐ. 3)፤ ነገር ግን ለሳምራዊቷ ሴት፥ ስለ ሕያው ውኃ ተናገረ (ዮሐ. 4)። ኢየሱስ ግትርነት የማያጠቃው ና ሁኔታዎችን የሚያጣጥም ነበር፤ ጳውሎስም የተከተለው የእርሱን ፈለግ ነበር። ኢየሱስም ሆነ ጳውሎስ ድርቅ ያለ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የሚሠራ «የወንጌል ቀመር» አልነበራቸውም።

ግንኙነት መፍጠር ብልሃትን ይጠይቃል። የምመሰክርላቸው ሰዎች ስለ ሥርዓተ ቅበላ (አንድ ሰው የአንድ ክርስቲያናዊ ቤተ እምነት ሙሉ አባል የሚደረግበት ሥነ ሥርዓት) ልምምዳቸውን በሚነግሩኝ ጊዜ፥ እኔም በዚያ ውስጥ ያለፍሁ መሆኔን እነግራቸዋለሁ። በዚያን ወቅት ላስተማረኝ ና ለጸለየልኝ መጋቢ አድናቆቴን እገልጽላቸዋለሁ። ከዚያም «ሥርዓተ ቅበላን ካለፍሁ ከአንድ ዓመት በኋላ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን በግሌ ተገናኝቼ ዳግም ተወለድሁ» እላቸዋለሁ። ጥሩ ምስክር ድልድይን እንጂ ግድግዳን ለመገንባት አይጥርም።

ላልበሰሉ ሰዎች የጳውሎስ የሕይወት ዘይቤ ምናልባት ተለዋዋጭ ይመስል ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እርሱ በጣም አቋመ-ጽኑ ሰው ነበር፤ ዓቢይ ዓላማው ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ነበር። አንድ ሰው በሰው ሠራሽ ደንቦች ና መለኪያዎች ታስሮ ለማገልገል ነጻነት እስከሚያጣ ድረስ አቋመ-ጠባቃና ለሕግ አጎብዳጅ ሊሆን ይችላል። ይህ በሳዖል ልብስ ውስጥ ሆኖ ለመዋጋት እንደሞከረው ወጣት ዳዊት ነው።

ጳውሎስ ያሰኘውን ሁሉ የመብላት መብት ነበረው፤ ነገር ግን አይሁዶችን ይማርክ ዘንድ ያን መብቱን ተወ። ጳውሎስ ሕግን አከበረ (ሮሜ 7፡12ን ተመልከት)። የጠፉትን አሕዛብ ይደርስ ዘንድ ግን ሕግን ወደ ጎን አደረገ። ይህ አቋምን የመሸቃቀጥ ነገር ሳይሆን ለላቀው የፍቅር ሕግ ሲሉ ፍጹም ራስን መተው ነው። ጳውሎስ የአዳኙን ምሳሌ በመከተል የሁሉም አገልጋይ ለመሆን ራሱን ዝቅ አደረገ።

*ስለ ራሱ ሲል (9፡24-27)።* ጳውሎስ የሩጫ (የአትሌትክስ) ምሳሌዎችን ይወድድ ነበርና ብዙ ጊዜ በመልእክቶቹ ውስጥ ተጠቅሞባቸዋል። ቆሮንቶሳውያን ከግሪክ የኦሎምፒክ ጨዋታዎች እና ከራሳቸው ኢስሚያን ጨዋታዎች ጋር የሚተዋወቁ ነበሩ። ጳውሎስ ይህን በማወቁ ከልምምዳቸው ጋር በጣም የሚቀራረብ ዘይቤያዊ አገላለጽን ተጠቀመ።

አንድ ሯጭ የሽልማቱ ባለቤት ለመሆን ከፈለገ ለሥነ ሥርዓት ራሱን ማስገዛት አለበት። ሥነ ሥርዓት ማለት ከሁሉ ለላቀው መልካሙን ና የተሻለውን መተው ነው። ሯጭ አመጋገቡን ና ጊዜውን መቆጣጠር አለበት። ሰዎች የሚያወፍሩ ምግቦችን ና የረፋድ ሌሊት ፓርቲዎችን ሲጋብዙት ፈገግ ብሎ «የለም፥ አመሰግናለሁ» ማለት መቻል አለበት። ምግብና መዝናኛ ችግር አለባቸው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ከከፍተኛ ግቦችህ ጋር የሚጋጩ ከሆነ፥ ያኔ ዕንቅፋቶች እንጂ ደጋፊዎች አይሆኑም።

ክርስቲያን ሩጫውን የሚሮጠው መንግሥተ ሰማይ ለመድረስ አይደለም፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመኑ ምክንያት ያለው በሩጫ ውስጥ ነው። በዘመኑ በጨዋታዎች መሳተፍ የሚችሉት የግሪክ ዜጎች ብቻ ነበሩ፤ እነርሱም በሥልጠናውም ሆነ በውድድሩ ወቅት የሚታዘዙአቸው ሕጎች ነበሯቸው። የሥልጠና ሕጎችን የሚጥስ ማንኛውም ተወዳዳሪ ወዲያውኑ ውድቅ ይደረግ ነበር። ዝነኛው የሕንድ አትሌት፥ ጂም ቶርፔ ቀደም ሲል ለፕሮፌሽናል ቡድን መጫወቱን ኮሚቴው ስለደረሰበት የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያውን መመለሱ የሚታወስ ነው።

ጳውሎስ መብቱን በመተውና የጠፉትን ሰዎች በማዳን እርካታን ለማግኘት ሲል ራሱን ለሥነ ሥርዓት አስገዛ። የዚህ ምዕራፍ አጠቃላይ አጽንኦትም ይህ ነው፡— ሥልጣን (መብቶች)ና ሥነ ሥርዓት መጣጣም አለባቸው። ጌታን ለማገልገል እና ከእርሱም ዋጋን ና ተቀባይነትን ለማግኘት፥ መሥዋዕትነት መክፈል አለብን።

*የተጣልሁ* የሚለው ቃል (ቁ. 27) የግሪክ ጨዋታዎችን ለሚያውቁት ቴክኒካዊ ቃል ነው። «ውድቅ የሆነ፥ ተቀባይነት ያጣ» ማለት ነው። በግሪክ ውድድሮች የውድድሩን ሕጎች፥ የተወዳዳሪዎችን ስሞች ና የአሸናፊዎችን ስሞችና ከተሞች የሚያውጅ ለፋፊ ሰው ነበር። ውድቅ የተደረጉትን ተወዳዳሪዎች ስምም ይለፍፍ ነበር።

ጳውሎስ ራሱን እንደ «ለፋፊ»ም እንደ «ሯጭ»ም አድርጎ ቆጠረ። በሩጫው ሌሎችን ለመርዳት በመጣር ከሚገባው በላይ ተጠምዶ ራሱን ውድቅ ሆኖ እንዳያገኝ በጣም ይጨነቅ ነበር። እንደገና፥ ይህ የግል ደኅንነትን የማጣት ጉዳይ አልነበረም። (ውድቅ የተደረገው የግሪክ አትሌት ዜግነቱን አላጣም፤ ያጣው ሽልማት የማግኘት ዕድልን ነው።) አጠቃላይ አጽንኦቱ በዋጋው ላይ ነበር፤ ስለሆነም ጳውሎስ *ዋጋውን* ለማጣት አልፈለገም።

በግሪክ ጨዋታዎች የወይራ አክሊልን መሸለም የሚችለው አንድ ሯጭ ብቻ ነበር፤ ነገር ግን ማንኛውም አማኝ ከክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በሚቀርብበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ሊያገኝ ይችላል። ይህ አክሊል ክርስቶስን በማገልገል እና የጠፉ ሰዎችን ለመመለስ ሲሉ ራሳቸውን ለሥነ ሥርዓት ለሚያስገዙ የሚሰጥ ነው። እነዚህ ሰዎች ሰውነታቸውን ከቁጥጥር ሥር አውለው ዓይኖቻቸውን በግባቸው ላይ ያደርጋሉ።

በቅርብ ዓመታት ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በአንድ በኩል የግል ሥነ ሥርዓት፥ በሌላ በኩል ደግሞ በሥነ ሥርዓት የተገዛ ሰውነት ና በመንፈስ የተሞላ ሕይወትን አስቀምጠው ሲያጤኑአቸው በመካከላቸው

ስላለው ግንኙነት አዲስ ግንዛቤን ጨብጠዋል። በእርግጥ ጽንፎችን ማስወገድ ይገባናል። በአንድ በኩል ሃይማኖታዊ ብህትውና (ተድላን ና ምቾትን ለራስ ነፍጎ ተራ ሕይወት መምራት–የግድ ገዳም መግባትን አያመለክትም) ጤናማ ያልሆነና ምንም መንፈሳዊ እሴት የሌለው ነው (ቆላ. 2፥18–23)። ነገር ግን፥ በሌላ ወገን ሥርዓት ለጠበቀ አመጋገብ፥ የሰውነት እንቅስቃሴ፥ ዕረፍት እና በመንፈስ ለሚመራ ሚዛናዊ ሕይወት ጥቂት የሚባል አለ። ሲጋራ ስለማናጤስ ወይም አልኮሆል ስለማንጠጣ በኩራት ራሳችንን እናሞጋግሳለን፤ ነገር ግን ከመጠን በላይ መብላታችን ና መወፈራችን እንዴት ይታያል? አንዳንድ ክርስቲያኖች ጊዜአቸውን በሥነ ሥርዓት መጠቀም ስለማይችሉ የማይዋዥቅ የጥሞና ሕይወት ና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ የላቸውም።

ጳውሎስ በሕይወቱ አንድ ትልቅ ዓላማ ነበረው፤ የጠፉትን በማዳን ና ቅዱሳንን በማነጽ ጌታን ማክበር። ወደዚህ ዓላማ ለመድረስ ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር። *የገዛ መብቱንም እንኳ ለመተው ፈቃደኛ ነበር!* ጊዜአዊውን ጥቅም ለዘላለማዊው ዋጋ፥ ጊዜአዊውን ምቾት ለዘላለማዊ ደስታ ሠዋ።

ሰማዕቱ ጂም ኤሊዮት የሚከተለውን ማለቱ ትክክል ነበር፦ «ለማስንበት የማይቻለውን፥ ሊያጣው ለማይችለው የሚሠዋ ሰው ሞኝ አይደለም።»

# 9

# ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት. . .

# ጠቢብ ሁን

*1ኛ ቆሮንቶስ 11*

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ወደ ኋላ የሚላቸው አሉታዊ ነገሮች ስለነበሩት፥ ቤተ ክርስቲያንን በማወደስ በአዎንታዊ ቃል ጀመረ። ውዳሴ የሚገባቸው በተለይ ሁለት ነገሮች ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን አስታውሳዋለች፥ አድንቃውማለች። በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን ትምህርት ለመጠበቅ ታማኝ ነበረች። ሕጎች የሚለው ቃል «ትውፊቶች»፥ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፉ ትምህርቶች (2ኛ ጢሞ. 2:2) ማለት ነው። የሰዎች ትውፊቶች መወገድ አለባቸው (ማቴ. 15:2–3፤ ቆላ. 2:8)፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተሰጡት ትውፊቶች መጠበቅ ይገባቸዋል።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩ ችግሮች አንዱ በጉባኤዎች መካከል የሚታይ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ነበር። አንዳንዶቹ ሴቶች ገደብ–ዘለል አርነት ተጸናውቶአቸው ነበር፤ በጌታ እራት ወቅት የሥርዓት ጉድለት ይታይ ነበር፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በመጠቀም ረገድም ውዥንብር ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ *በመንፈሳዊ ስጦታዎች* እጅጉን የበለጸገች ብትሆንም መንፈሳዊ *ጸጋ* ይጎድላቸው ነበር።

ጳውሎስ እነዚህን ችግሮች ሐዋርያዊ ቀላጤ በማውጣት ለመፍታት በሞከረ ነበር፤ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ለቤተ ክርስቲያን አስተምሮ የነበሩትን ትምህርቶች የሚደግፍ መርሆችን አቅርቦ በትዕግሥት አብራራቸው። መከራከሪያዎቹን የመሠረተው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነበር።

ጳውሎስ የጉባኤ አምልኮአቸውን ሦስት የውዥንብር አቅጣጫዎች አጤነ።

## የሚጸልዩ ና ትንቢት የሚናገሩ ሴቶች (1ኛ ቆሮ. 11:3–16)

የክርስትና እምነት ለሴቶች፥ ለልጆችና ለባሪያዎች አርነትን እና ተስፋን አመጣ፡ ሁሉም ሰዎች፥ ከዘር ወይም ከፆታ ባሻገር በፈጣሪያቸው ፊት እኩል መሆናቸውንና ሁሉም አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ መሆናቸውን (ገላ. 3:28) አስተማረ። ቀደም ብለን እንደገለጽነው፥ በሮማ መንግሥት ሁሉንም ሰዎች፥ ከብሔራቸው፥

ከማኅበራዊ አቋማቸው፥ ከዖታቸው፥ ወይም ከኢኮኖሚ ይዞታቸው ውጭ የምታስተናግድ ኅብረት ብትኖር ምናልባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነበረች።

ይህን አዲስ የተገኘውን አርነት ከልክ አልፈው የሚሄዱ አንዳንድ ሰዎች እንደሚኖሩ የተጠበቀ ነበር። አዲስ ንቅናቄ ምንጊዜም ከጠላቶቹ ይልቅ በተከታዮቹ ምክንያት የበለጠ ይሠቃያል፤ በቆሮንቶስም የነበረው እውነት ይህ ነው። ከሴቶች አንዳንዶቹ በጉባኤ በሚሳተፉበት ወቅት ራሳቸውን ባለመሸፈን «አርነታቸውን» መመጻደቂያ አደረጉት።

ጳውሎስ እነዚህ ሴቶች እንዳይጸልዩ ወይም ትንቢት እንዳይናገሩ አልከለከለም። (ትንቢት መናገር ከእኛው «ስብከት» ወይም «የቃል ገለጣ» ጋር አንድ አይደለም። የትንቢት ስጦታ የነበረው ሰው የእግዚአብሔርን መልእክት እንደተሰጠው ወዲያው በመንፈስ ይናገራል። ዘመናዊው ሰባኪ ቃሉን በማጥናት መልእክቱን ያዘጋጃል።) አዲስ ኪዳን የሴት ሽማግሌዎችን የሚፈቅድ ባይመስልም (1ኛ ጢሞ. 3:2)፥ በቀደሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ሴቶች የትንቢት ስጦታዎቻቸውን ይለማመዱ ነበር። በጉባኤ ላይም እንዲጸልዩ ይፈቀድላቸው ነበር። ሆኖም ግን፥ የወንዶችን ሥልጣን መንጠቅ (1ኛ ጢሞ. 2:11-15) ወይም የሌሎችን ነቢያት መልእክት መፍረድ (1ኛ ቆሮ. 14:27-35) አልነበረባቸውም። ጥያቄዎች ከነበሩአቸው፥ ባሎቻቸውን (ወይም ሌሎች ወንዶችን) ከቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ውጭ መጠየቅ ይችሉ ነበር።

ምሥራቃዊ ማኅበረሰብ በዚያ ዘመን በሴቶቹ በጣም ይቀና ነበር። የቤተ መቅደስ ዘማውያን ካልሆኑ በቀር ሴቶች ፀጉራቸውን በረጅሙ ያሳድጉና በአደባባይም ራሶቻቸውን ይሸፍፉኑ ነበር። (ጳውሎስ እዚህ ላይ ዓይን ርግብ ማለቱ አልነበረም፤ ይህ በፊት ላይ የሚደረግ ሽፋን ነው። ሴቶች ተለምዶአዊውን ሽፋን በራሳቸው ላይ ያደርጉ ነበር፤ ይህ ሽፋን የመገዛታቸው እና የንጽሕናቸው መለያ ነበር።) በሕዝብ ፊት ፀጉርን ሳይሸፈኑ መጸለይ ና ቃሉን ማንበብ ቀርቶ እንዲህ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መታየቱ ድፍረት ና ጸያፍ ነበር።

ጳውሎስ ለቆሮንቶሳውያን እግዚአብሔር በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነትን እንደ ፈጠረ፥ በእርሱ ምጣኔ እያንዳንዱ የራሱ ስፍራ እንዳለው በማሳሰብ ሥርዓት እንዲመለስ ፈለገ። እነዚህን ግንኙነቶች የሚያንጸባርቁ እና በመለኮታዊ አወቃቀር ውስጥ ሁለቱም ወንዶች ና ሴቶች ያሉአቸውን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳስቡ አግባብ ያላቸው ባሕሎችም ነበሩ። ጳውሎስ *ልዩነት እኩል አለመሆን ወይም ዝቅተኛነት* ነው ብሎ ማሰብ ቀርቶ አዝማሚያውንም አላሳየም። በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ ሰላም (15፡33) እንዲኖር ከተፈለገ፥ የሆነ ዓይነት ሥርዓት መኖር አለበት፤ ሥርዓት ደግሞ የተዋረድን ቀዳሚነት ይፈልጋል። ቢሆንም፥ *ተዋረድ* እና *ብቃት* ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ካፒቴን ከተራ ወታደር የላቀ ማዕረግ ነው፤ ነገር ግን ተራው ወታደር የተሻለ ሰው ሊሆን ይችላል።

በቤተ ክርስቲያን የሚገኝ የእግዚአብሔር ሥርዓት በሦስት ፍሬ አሳቦች ላይ የተመሠረተ ነው። ጳውሎስ እነዚህ ፍሬ አሳቦች ራስ-ገለጽ ናቸው ይላል።

*ቤዛነት (11፡3-7)።* በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወሰነ «ራስነት» አለ። አብ የክርስቶስ ራስ ነው፥ ክርስቶስ የወንድ ራስ ነው፥ ወንድም ደግሞ የሴት ራስ ነው። አንዳንዶች ራስ የሚለውን «መነሻ» ወይም «ምንጭ» ብለው ይተረጉሙታል፤ ነገር ግን ይህ አብ ክርስቶስን እንዳመነጨ ይመስላል- ይህ ደግሞ የማንቀበለው ነው። ምንም እንኳ ከአብ ጋር እኩል ቢሆንም (ዮሐ. 10፡30፤ 14፡28) በመቤዠት አገልግሎት፥ ወልድ ለአብ ተገዢ ነበር። ምንም እንኳ ሴት በክርስቶስ ከወንድ እኩል ብትሆንም ለወንድ ትገዛለች (1ኛ ቆሮ. 3፡21-23፤ ገላ. 3፡28፤ ኤፌ. 5፡21-33)።

ጳውሎስ ይጽፍ የነበረው *በአጥቢያ ጉባኤ ውስጥ ያለውን ግንኙነት* እንጂ በመላው ዓለም ያለውን እንዳልሆነ ልብ በል። በቤት ውስጥ እና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፥ ወንዶች በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ሥር ሆነው የራስነት ስፍራ እንዲለማመዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

አስፈላጊው ነጥብ ይህ ነው። ሁለቱም ወንዶች እና ሴቶች እነዚህን የራስነት ምልክቶች የሆኑትን-ፀጉር እና የራስ ሽፋንን አክብሮ በመያዝ ጌታን ከፍ ከፍ ማድረግ አለባቸው። አንዲት ሴት በጉባኤ በምትጸልይበት ወይም ትንቢት በምትናገርበት ማንኛውም ጊዜ ፀጉሯን ለቅቃ እና ራሷን ተሸፍና መሆን አለበት። ወንድ ፀጉሩ አጭር ሆኖ በራሱ ላይ ምንም ሽፋን ማድረግ የለበትም። (ይህ ለጳውሎስ መለወጥ ነው፤ ምክንያቱም አክራሪ የአይሁድ ወንዶች በሚጸልዩበት ጊዜ በራሳቸው ላይ ኮፍያ ያደርጉ ነበር።) ወንድ ራሱን ባለመሸፈን የእርሱን ራስ (ክርስቶስን) ያከብራል፤ ሴት ግን ራሷን በመሸፈን የእርሷን ራስ (ወንድን) ታከብራለች። ለእግዚአብሔርም ሆነ ለወንድ መገዛቷን ማሳየቷ ነው።

ራሳቸውን ሳይሸፍኑ በጉባኤ ላይ ይገኙ የነበሩ የቆሮንቶስ ሴቶች እንደ እውነቱ ከሆነ ያደርጉት የነበረው ራሳቸውን ወደ ቤተ መቅደስ ዘማዊነት ደረጃ ቁልቁል ማውረድ ነበር። ዘማዊ ሴቶች ፀጉራቸውን ይቆረጡ፥ በአደባባይም በራሳቸው ላይ ምንም ሽፋን አያደርጉም ነበር።

የፀጉር አሠራራቸው እና ሁኔታቸው ማን እንደሆኑ እና ምን እያቀረቡ እንዳሉ ለሌሎች አዋጅ የሚናገር ነበር። ጳውሎስ ሲጽፍ፥ «ራሳችሁን የማትሸፍኑ ከሆነ ለምን እስከነጭራሹ አትቆረጡትም?» አላቸው።

በአይሁድ ባሕል በዝሙት የተወነጀለች ሴት ፀጉሯን ትቆረጥ ነበር (ዘኁ. 5፡11–31)። ጳውሎስ ከቁጥር 5–6 ባለው ሁለት የተለያዩ ቃላትን ተጠቅሞአል። *መላጨት* ማለት ፀጉርን ሙሉ በሙሉ ጠርጎ ማስወገድ ሲሆን፥ *መቆረጥ* ማለት «መከምከም» ነው። የትኛውም ቢሆን ለሴት አሳፋሪ ነበር።

ሁለቱም ወንድ ና ሴት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር አምሳል እና ለእግዚአብሔር ክብር ነው፤ ነገር ግን ሴት ከወንድ ስለተሠራች (ዘፍ. 2፡18–25)፥ እርሷ «የወንድ ክብርም» ናት። ለእግዚአብሔር ትእዛዝ በመገዛት እና በጉባኤ አምልኮ ወቅት ራሷን በመሸፈን እግዚአብሔርን ታከብራለች፤ ለወንድም ክብርን ታመጣለች። እንግዲህ፥ ጳውሎስ አካባቢአዊ ባሕልን ና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን አንዱ ወደ ሌላው እንዲያመለክት አድርጎ ሁለቱንም አስተሳሰራቸው።

*ፍጥረት (11፡8–12)።* ይህን እውነት ቀደም ብለን በአጭሩ ነካክተነዋል። የእግዚአብሔር ሥርዓት ወንድ አስቀድሞ መፈጠሩ (1ኛ ጢሞ. 2፡13)፥ እና ሴቲቱ የተፈጠረችው ለወንድ በመሆኑ እውነታ ላይ የተመሠረተ ነው። እንደገና፥ ቅደም ተከተል ዝቅተኛነትን አያመለክትም፤ ምክንያቱም ጳውሎስ ከ11–12 ላይ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ *ጉድኝነት* እና ራስነት እንዳሉ ግልጽ አድርጓል። ወንድም ሆነ ሴት በመንፈሳዊው ረገድ በጌታ አንድ ሲሆኑ (ገላ. 3፡28) አንዱ ያለ ሌላው ሊሆን አይችልም። በተጨማሪ፥ ከመነሻው ሴት ከወንድ የተገኘች ቢሆንም፥ ነገር ግን ዛሬ ከሴት የሚወለደው ወንድ ነው። ወንድ እና ሴት አንዱ የሌለው እና እርስ በርስ ተፈላላጊ ናቸው።

ጳውሎስ በቁጥር 10 መላእክትን ያመጣው ለምንድን ነው? ይከራከር የነበረው ከፍጥረት አኳያ ስለሆነ እና መላእክቱም የዚያ ፍጥረት አካል ስለነበሩ ነው። መላእክት ስፍራቸውን የሚያውቁ ስለሆነ በሚያመልኩበት ጊዜ ፊታቸውን በመሸፈን ክብርን ይሰጣሉ (ኢሳ. 6፡2)። በመጨረሻም፥ በሆነ ልዩ መንገድ፥ መላእክት በቤተ ክርስቲያን የጉባኤ አምልኮ ይካፈላሉ፤ ከቤተ ክርስቲያንም ይማራሉ (ኤፌ. 3፡10፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡12)። የጉባኤ አምልኮ፥ መላእክትም ስለሚገኙበት ከባድ ነገር ነው፤ በመሆኑም *በመንግሥተ ሰማይ እንዳለን አድርገን* ሥርዓት መያዝ ይገባናል።

*ተፈጥሮ (11:13-15)*። በጥቅሉ ሲታይ ተፈጥሮ ለሴቶች ረጅም ፀጉር፥ ለወንዶች አጭር ፀጉር ማደሉ እውነት ነው። ሮማውያን፥ ግሪኮች እና አይሁዶች (ናዝራውያን ካልሆነ በቀር) ይህንኑ ባሕል ይከተሉ ነበር። ፀጉራችን ምን ያህል ረጅም መሆን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ የትም ስፍራ ላይ አይነግረንም። የፆታ ግራ መጋባት እንዳይኖር በወንዶች ፀጉር እና በሴቶች ፀጉር ርዝማኔ መካከል የሚታይ ልዩነት መኖር አለበት። (ይህ መርህ «አንድ ፆታ» የሚባለውን ዘይቤ ያስወግዳል።) ለወንድ ሴትን መምሰል፥ ወይም ለሴት ወንድን መምሰል አስነዋሪ ነው።

የሴት ረጅም ፀጉር ክብሯ ነው፥ «በሽፋኑ ፈንታም» የተሰጣት ነው (ቀጥታ ትርጉም)። በሌላ አነጋገር የአካባቢው ባሕል የራስን መሸፈን የሚያስገድድ ካልሆነ በቀር፥ ረጅሙ ፀጉሯ ሽፋን ሊሆንላት ይችላል። ጳውሎስ በሁሉም ባሕል ሥር ያሉ ሴቶች ራሳቸውን ይሸፋፍኑ ማለቱ አይመስለኝም፤ ነገር ግን ረጁሙን ፀጉራቸውን እንደ ሽፋን ና ለእግዚአብሔር ሥርዓት የመገዛታቸው ምልክት እንዲያደርጉት ይጠብቅባቸው ነበር። ይህም ማንም ሴት ልታደርገው የምትችለው ነው።

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በነበረኝ አገልግሎት የራስነት መርህ በሁሉም መሥራቱን አይቻለሁ፤ ነገር ግን የሚገለጽባቸው መንገዶች ከቦታ ቦታ ይለያያሉ። ዋናው ነገር ልብን ለጌታ ማስገዛት ና ለእግዚአብሔር ሥርዓት በገሃድ ታዛዥነትን መግለጽ ነው።

## ራስ ወዳድነት በ«ፍቅር ግብዣዎች» (1ኛ ቆሮ. 11:17-22)

ከቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ጀምሮ፥ አማኞች አንድ ላይ መብላታቸው የተለመደ ነበር (የሐዋ. 2:42፥46)። ይህ በኑሮ አቋማቸው ደከም ካሉት ጋር አብሮ ለመሆን ና ለማካፈል ዕድል የሚሰጥ ነበር። የጌታን እራት በሚያስቡበት ጊዜ ይህን አብሮ የመብላት ነገር ወደ ከፍተኛ ደረጃ አድርሰውት ነበር። ዋናው አጽንኦት አብሮ በመከፋፈል ለቅዱሳን ፍቅርን ማሳየት ስለነበር ይህን ማዕድ «የፍቅር ግብዣ» ብለው ሰየሙት።

የ«አጋፔ ግብዣ» (ለፍቅር የተሰጠው የግሪክ ቃል) በቆሮንቶስ የነበረው አምልኮ አንዱ አካል ነበር። ሆኖም ግን አንዳንድ ከመስመር የወጡ ነገሮች ሾልከው እየገቡ ነበር። ከዚህም የተነሣ፥ የፍቅር ግብዣዎቹ ለቤተ ክርስቲያን ከሚሰጡት ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነ ነበር። አንደኛው ችግር፥ በቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ቡድኖች የነበሩ ሲሆን፥ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን መላው ቤተሰብ ጋር ኅብረት ከማድረግ ፈንታ ከገዛ «አቻዎቻቸው» ጋር አብረው ይበሉ ነበር።

ጳውሎስ ይህን ራስ ወዳድ ተግባር ቢያወግዝም፥ ለውጤቶቹ ግን አዎንታዊ አመለካከት ነበረው። ይኸውም እግዚአብሔር ሁኔታውን እውነተኛዎቹን አማኞች ለመግለጥ ተጠቅሞባቸዋል የሚል ነበር።

ሌላው ጉድለት ስስት ነበር። ሀብታሞቹ ሰዎች ለራሳቸው ብዙ ምግብ ሲያመጡ ድሆቹ ይራቡ ነበር። «የአጋፔ ግብዣ» መነሻ አሳብ ፍቅርን መከፋፈል ሲሆን፥ ያ አሳብ ግን ጠፋ። ከአባላት አንዳንዶቹ ይሰክሩ ነበር። ሳምንታዊው «የአጋፔ ግብዣ» አንዳንድ ደሀ አባላት አዘውትረው የሚያገኙት ብቸኛው ደህና ምግብ የነበረ ይመስላል፤ በመሆኑም በሀብታሞቹ ወገኖች በንቀት መታየቱ የጎዳው ሆዳቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ክብራቸውንም ጭምር ነበር።

በእርግጥ፥ በማዕድ የሚደረጉ ክፍፍሎች በቤተ ክርስቲያን የነበሩትን ጥልቅ ችግሮች የሚያመለክቱ ነበሩ። ቆሮንቶሳውያን ራሳቸውን የተራመዱ አማኞች አድርገው ቢቆጥሩም፥ ሐቁ ግን እንደ ሕፃን የሚያደርጋቸው መሆናቸው ነው። ጳውሎስ ግብዣውን እንዲተዉት ሳይሆን፥ ወደ ትክክለኛው ትርጉም እንዲመልሱት አሳሰበ። «ሀብታሞች ከራባቸው በቤታቸው ይብሉ። እንደ እናንተ ያልደላቸውን ያለ አግባብ ስታንገላቱአቸው፥ ቀጥታ ቤተ ክርስቲያንን መናቃችሁ እኮ ነው!» የ«አጋፔ ግብዣ» ለመተናነጫ ዕድል መሆን ሲገባው፥ የመቃቃሪያ ጊዜ አድርገው ተጠቀሙበት።

ገና ወጣት ልጅ እያለሁ በእሑድ/በሰንበት ትምህርት ቤት ሽርሽር የሆነው ነገር ትዝ ይለኛል። በሽርሽር ቦታ ኃላፊ የነበረችው ሴት ጨዋታ አዘጋጅታ ነበር የመጣችው። ከዚያም ልጆቿን በቡድን አደረገች። በሁለት ረድፍ እየተያየን እንድንቆም አደረገችን። ጨዋታው ግንባር ለግንባር የሚተያዩ ልጆች እንቁላል እየተወራወሩ መቀባበል ሲሆን፥ ቅብብሎሹን በምናካሄድበት ጊዜ ወደ ኋላችንም ማፈግፈግ ነበረብን። በዚህ ዓይነት ሁኔታ እየተራራቅን በሄድን መጠን እንቁላሎቹን በኃይል መወርወር ስለሚጠይቅ ጨዋታው በጣም አስደሳች ወደ ሚሆንበት ጫፍ ይደርስ ነበር።

ይሁንና፥ ሁለት የእሑድ/የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንቁላሎችን በታላቅ ጉጉት ሲመለከቷቸው አንዳንዶቻችን ተመለከትን። እነዚህ ልጆች መግዛት ስለማይችሉ ምናልባት እንቁላል አልፎ አልፎ ከሚበሉ ደሀ ቤተሰቦች የመጡ ነበሩ። ትንሿ ልጃገረድ ጨዋታውን ወደምትመራው ሴት ሄደችና፥ «የተረፉ እንቁላሎች ካሉ፥ ወንድሜና እኔ ወደ ቤት እንድንወስድ ይፈቀድልናል?» ስትል ጠየቀች። ሴትየዋም ጨዋታው ከማለቁ በፊት በጥበብ አስቂኝ፥ ሽልማቶቹን ከሰጠች በኋላ እንቁላሎቹን በሙሉ ለሁለቱ ልጆች

ሰጠች። ሌሎች እየተከሉ አንዳንድ ቅዱሳን የመዝናኛ ጊዜ ማድረጋቸው ስሕተት መሆኑን አወቀች።

«የጠጪዎች ማኅበር» ይዞ ለጌታ እራት መዘጋጀት ጥሩ አካሄድ ነው ለማለት አያስደፍርም። ለኃጢአተኞች ሁሉ፥ ለሀብታሙም ለድሀውም የሞተውን አዳኝ ለማስታወስ ሌሎችን መናቅ ጭራሽ መንገዱ አይደለም። ወደ ጌታ እራት በምንቀርብበት ጊዜ ልባችንን ማዘጋጀቱ ምንኛ ተገቢ ነው!

## በጌታ ራት የነበሩ ፈር የለቀቁ ድርጊቶች

## (1ኛ ቆሮ.11፡23–34)

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ እንዲጠብቁአቸው ያቆሙአቸውን ሁለት ሥርዓቶች ይቀበላሉ– ጥምቀት እና የጌታ እራት። (የጌታ እራት በ 1ኛ ቆሮ. 10፡ 16 ላይ እንደተጠቀሰው፥ *ኅብረት* በመባልም ይታወቃል። እንደዚሁም *ዩካሪስት* «አቅርቦተ ምስጋና» ተብሎም ይጠራል)። ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋውን ና እንጀራውን አነሣ– እነዚህ በዘመኑ አንድ ማዕድ ተዋጽኦዎች ናቸው። ከዚያም እነዚህን ሁለት ነገሮች ለአማኞች ትርጉም ወደሚሰጡ ልምምዶች ቀየራቸው። ይሁንና የልምምዱ እሴት የሚወሰነው በተሳታፊዎች የልብ ሁኔታ ላይ ነው፤ በቆሮንቶስ የነበረው ችግርም ይኸው ነው።

ባልተዘጋጀ ልብ ወደ ኅብረቱ መምጣት ከባድ ነገር ነው። በግድየለሽነት መንፈስም የጌታን እራት መቀበል ከባድ ነገር ነው። ቆሮንቶሳውያን በጌታ እራት አቀባበላቸው ኃጢአት ያደርጉ ስለነበር እግዚአብሔር ቀጥቶአቸዋል። «ስለዚህ በእናንተ መካከል የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል [ሞተዋል]» (ቁ. 30)።

በትክክለኛ ልብ ከቀረበው የጌታ እራት ለመንፈሳዊ እድገት ና ባርኮት ድል ይሰጠናል። ይህ እራት ቅጣት ሳይሆን በረከት እንዲያመጣልን ምን እናድርግ?

*በመጀመሪያ፥ ወደ ኋላ መመልከት አለብን (11፡23–26)።* የተቆረሰው እንጀራ ለእኛ የተሰጠውን የክርስቶስ ሥጋ ያሳስበናል፤ ጽዋውም የፈሰሰውን ደሙን ያስታውሰናል። ኢየሱስ ተከታዮቹ ሞቱን እንዲያስታውሱ መፈለጉ ያልተለመደ ነገር ነው። ብዙዎቻችን የወደድናቸው እንዴት እንደ ሞቱ ለመርሳት እንጥራለን፤ ነገር ግን ኢየሱስ እንዴት እንደ ሞተ እንድናስታውስ ይፈልጋል። ለምን?

ምክንያቱም ክርስቲያን እንደመሆናችን ያለን ነገር በሙሉ ማዕከል የሚያደርገው ይህን ሞቱን ነው።

መሞቱን ማስታወስ ያለብን፥ የወንጌል መልእክት አንዱ ክፍል ስለሆነ ነው። «ክርስቶስ. . . ሞተ፥ ተቀበረም. . .» (15:3–4)። ኃጢአተኞችን የሚያድነው የጌታችን ሕይወት፥ ወይም ትምህርቶቹ ሳይሆኑ ሞቱ ነው። በዚህን ምክንያት ለምን እንደ ሞተ እናስታውሳለን። ክርስቶስ ስለ ኃጢአተኞች ሞተ፤ ልንከፍለው የማንችለውን ዕዳ በመክፈል፥ እርሱ የእኛ ምትክ ሆነ (ኢሳ. 53:6፤ 1ኛ ጴጥ. 2:24)።

እንዴት እንደ ሞተም ማስታወስ አለብን–በፈቃደኝነት፥ በየዋህነት፥ ፍቅሩን ለእኛ በመግለጥ ነው (ሮሜ 5:8)። *ሥጋውን ለከፉዎች እጅ አሳልፎ ሰጠ*፤ በሰውነቱም የዓለምን ኃጢአት ተሸከመ።

ይሁንና ይህ «ማስታወስ» ታሪካዊ እውነታዎችን እንዲያው ማስታወስ አይደለም። በመንፈሳዊ እውነታዎች ውስጥ መሳተፍ ነው። በጌታ እራት ወቅት እየዞርን የምናደንቀው ሐውልት የለም። ልባችን በእምነት ሲዘረጋ ሕያው ከሆነ አዳኝ ጋር ኅብረት እናደርጋለን።

*ሁለተኛ፥ ወደፊት መመልከት አለብን (11:26)።* ይህን እራት «እርሱ እስኪመለስ ድረስ» እንወስደዋለን። የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ የቤተ ክርስቲያን ና የእያንዳንዱ ክርስቲያን የተባረከ ተስፋ ነው። ኢየሱስ ለእኛ የሞተ ብቻ ሳይሆን እንደገና በመነሣት ወደ ሰማይ አርጓል፤ እናም አንድ ቀን ተመልሶ መጥቶ ወደ ሰማይ ይዞን ይሄዳል። ዛሬ መሆን የሚገባንን ሁሉ አልሆንንም፤ ነገር ግን እርሱን በምናይበት ጊዜ፥ «እርሱን እንመስላለን» (1ኛ ዮሐ. 3:2)።

*ሦስተኛ፥ ወደ ራሳችን መመልከት አለብን (11:27–28፥ 31–32)።* ጳውሎስ የጌታን እራት ለመውሰድ *ብቁ ሆነን መገኘት* አለብን ማለቱ ሳይሆን፥ *ብቃት ባለው ሁኔታ* ወይም መንገድ መውሰድ አለብን ማለቱ ነው። በስኮትላንድ በተደረገ የጌታ እራት አገልግሎት ከምእመናኑ አንዲት ሴት ከሽማግሌው እጅ እንጀራውን እና ጽዋውን መቀበል ትታ ቁጭ ብላ ስታለቅስ መጋቢው አስተዋላት። መጋቢው ማዕዱን ትቶ ሄደና አጠገቧ ሆኖ « ውሰጂው የእኔ እመቤት፥ *ይህ እኮ ለኃጢአተኞች ነው!»* አላት። በእርግጥም ነው፤ ነገር ግን፥ በእግዚአብሔር ጸጋ የዳኑ ኃጢአተኞች ይህን እራት ኃጢአታዊ በሆነ ሁኔታ ማስተናገድ የለባቸውም።

ክቡር በሆነ መንገድ መካፈል ካለብን፥ የገዛ ልባችንን መመርመር፥ በኃጢአቶቻችን መፍረድ እና ለጌታ መናዘዝ አለብን። በሕይወታችን

ንስሐ ያልገባነው ኃጢአት ይዘን ወደ ማዕዱ መቅረብ የክርስቶስ ሥጋ እና ደም ተጠያቂ መሆን ነው፤ ምክንያቱም እርሱን በመስቀል ላይ የቸነከረው ኃጢአት ነው። ኃጢአቶቻችንን ራሳችን ካልፈረድንባቸው፥ ንስሐ ገብተን እስከምንተዋቸው ድረስ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ፍርዱን ና ቅጣቱን ያመጣል።

ቆሮንቶሳውያን ራሳቸውን መመርመሩን ችላ ብለው ሌላውን ሁሉ በመመርመሩ ረቀቁበት። ቤተ ክርስቲያን በምትሰባሰብበት ጊዜ የራሳቸውን ኃጢአት ማወቅ ተስኖአቸው እያለ የሌሎችን እንደሚከታተሉ «ሃይማኖታዊ መርማሪዎች» መሆን የለብንም። ክብር በጎደለው መንገድ ብንመገብ ና ብንጠጣ፥ የምንበላው ና የምንጠጣው ፍርድን ነው፤ ይህ ደግሞ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም።

ቅጣቱ እግዚአብሔር ወንድ ና ሴት ልጆቹን እንዲጠነክሩ የሚያበረታታበት የፍቅር አያያዝ ነው (ዕብ. 12፡ 1–11)። እርሱ በወንጀለኛ ላይ የሚፈርድ ዳኛ ሳይሆን፥ የማይታዘዙ (ምናልባትም የደነደኑ) ልጆቹን የሚቀጣ አፍቃሪ አባት ነው። ቅጣት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያረጋግጥልናል፤ ከተባበርነው ደግሞ ቅጣት የእግዚአብሔርን ሕይወት በእኛ ውስጥ ይሠራል።

በመጨረሻም፥ *ወደ ዙሪያችን መመልከት አለብን (11፡33–34)።* ዙሪያችንን መመልከት ያለብን ሌሎች አማኞችን ለመተቸት ሳይሆን፥ ነገር ግን የጌታን ሥጋ ለመለየት ነው (ቁ. 29)። ይህ ምናልባት ጣምራ ትርጉም ይሰጣል። ሥጋውን በእንጀራው ውስጥ፥ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች ደግሞ በዙሪያችን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለየት አለብን። «አንድ እንጀራ ስለሆነ፥ እኛ ብዙዎች አንድ ሥጋ ነን» (1ኛ ቆሮ. 10፡17)። የጌታ እራት የቤተ ክርስቲያን ኅብረት መገለጫ መሆን ነበረበት፤ ነገር ግን በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ኅብረት አልነበረም። እንዲያውም፥ የጌታን እራት ማክበራቸው ለክፍፍላቸው መግለጫ ሆኖ ነበር።

የጌታ እራት የአንድ ቤተሰብ ማዕድ ነው። የቤተሰቡ ባለቤትም ልጆቹ እርስ በርስ እንዲዋደዱ ና አንዱ ለአንዱ እንዲጠነቀቅ ይፈልጋል። ከአማኝ ወገኖቹ ተለያይቶ እያለ በዚሁ ጊዜ ደግሞ ወደ ጌታ መጠጋት ለእውነተኛ ክርስቲያን ሊሆንለት አይችልም። እርስ በርስ ሳንዋደድ እንዴት አድርገን የጌታን ሞት እናስባለን? «ወዳጆች ሆይ፥ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል» (1ኛ ዮሐ. 4፡11)።

ማንም እውነተኛ አማኝ ያልሆነ ወደ ማዕዱ መምጣት የለበትም። ይህ ብቻ ሳይሆን እውነተኛው አማኝም ቢሆን ልቡ ከእግዚአብሔር

እና ከክርስቲያን ወገኖቹ ጋር ትክክል ካልሆነ ወደ ማዕዱ መቅረብ የለበትም። ከተካፋዮቹ ማንም በራሳቸው ላይ ቅጣትን እንዳይጋብዙ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የጌታን እራት ከመካፈላቸው በፊት መንፈሳዊ ዝግጅት የሚያደርጉት ለዚህ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ወደ እኔ ቀርቦ ስለደረሰበት ግላዊ ሽንፈት ያጫወተኝ ትዝ ይለኛል። ችግሩ መንፈሳዊ ሕይወቱን ከመጉዳት አልፎ በሌሎችም ዘንድ «በመለፈፉ» በእርሱ እና በቤተ ክርስቲያን ላይ ነቀፋን ሊያመጣ የተቃረበ ነበር።

«ይህን ለማስተካከል ምን ላድርግ?» አለኝ። ሁኔታው በእርግጥ ኃጢአቱን እንደፈረደበት እና ንስሐ እንደገባበት አሳመነኝ። በተከታዩ ሳምንት የጌታን እራት እንደምናዘጋጅ ነገርሁትና የጌታን ምሪት እንዲጠይቅም አሳሰብሁት። በምሽቱ የጌታ እራት ላይ፥ ከዚህ ቀደም አድርጌው በማላውቀው መንገድ አገልግሎቱን ጀመርሁ። «ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሆነ ነገር ለመካፈል የሚያስብ ሰው አለ?» ብዬ ጠየቅሁ። ንስሐ የሚገባው ወዳጄ ተነሥቶ በእግሩ ቆመና ወደፊት ተራምዶ እማዕዱ ቦታ ተገናኘኝ። በተረጋጋ፥ አጠር ባለ ቃል፥ ኃጢአት እንደሠራ እና ቤተ ክርስቲያንን ይቅርታ እንደሚጠይቅ ተናገረ። ከመንፈስ የመጣ የፍቅር ማዕበል በጉባኤው ላይ ሲወርድ ተሰማን። ሰዎችም በግልጽ ያለቅሱ ነበር። በዚያን ምሽት የጌታ እራት መታሰቢያ፥ በትክክል የጌታን ሥጋ ለይተን አወቅን።

ምንም እንኳ የኃጢአት ንስሐ አስፈላጊ ቢሆንም፥ የጌታ እራት የኃጢአት መንሥኤ መንፈሳዊ የመመርመሪያ እና የልቅሶ ጊዜ እንዲሆን አይጠበቅም። የምስጋና እና ጌታን ለማየት በሐሴት የምንጠባበቅበት ጊዜ መሆን አለበት! ሥቃይ ና ሞት እየጠበቀው ቢሆንም እንኳ ኢየሱስ ምስጋናን አቀረበ። እኛም እንዲሁ ምስጋና እንስጥ።